# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 058 ጥቅምት 28 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ - አዩብ ተፈሪ

# ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ ስታሸንፍ የምታሸንፈው አፍሪካ ናት ሲሉ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ተናገሩ

## - አዲስ አበባ በዓለም አቀፍ መድረክ ተሸላሚ እንድትሆን ላደረጉ አካላት እውቅና ተሰጥቷል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ ስታሸንፍ የምታሸንፈው አፍሪካ ናት ሲሉ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ገለጹ። አዲስ አበባ በብራዚል ሪዮ ዴጄኔሮ የ8ኛው የሚላን የከተማ ምግብ ፖሊሲ ስምምነት የ‹‹MUFPP›› ዓለም አቀፍ መድረክ ላይ ተሸላሚ እንድትሆን ላደረጉ ባለድርሻ አካላት ትናንት በሚሊኒየም አዳራሽ እውቅና ተሰጥቷል።

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ትናንት በዚሁ ወቅት ባስተላለፉት መልዕክት፤በመንግስትና በሕወሓት መካከል

ኢትዮጵያ በዓለም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ዳኜ አበራ

# «ሕዝብን ሲያክም፣ ቁስልን ሲያስሽር የሚያስችል ስራ መስራት ይገባል»

## - ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ህዝብን ሲያክም ቁስልን ሲያስሽር የሚያስችል ስራ መስራት ይገባል ሲሉ ኡስታዝ አቡበከር አሕመድ ተናገሩ። ኡስታዝ አቡበከር በፌደራል መንግስትና በሕወሓት መካከል በተደረገው የሠላም ስምምነት ለመላው ኢትዮጵያውያን የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ኡስታዝ አቡበከር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በፌደራል መንግስትና በሕወሓት መካከል ከተደረገው የሠላም ስምምነት በኋላ ህዝብን ሲያክም፣ ቁስልን ሲያስሽር የሚያስችል ስራ መስራት ይገባል።

“በጦርነቱ አትራፊ የለም፤ ሁላችንም ከስረናል” ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ ጉዳቱ እንዲታከም ስራ መስራት ያስፈልጋልም ብለዋል።

በቀጣይ በሚደረጉ ተግባራት ላይ የህዝብ ቁስል የሚታከምበት ሀገር የምትካስበትን መንገድ

«ሕዝብን ሲያክም፣ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል








# «ከስምምነቱ ጋር ተያይዘው የሚወጡ መረጃዎችን የሚቆጣጠር የሚዲያ ፎረም ሊቋቋም ይገባል»

- ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዚዳንት

ገጽ 4

# የሠላም ስምምነቱ አፍሪካውያን ዳግማዊ አድዋን ያረጋገጡበት ድል ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ መንግስትና በሕወሓት መካከል የተደረገው ስምምነት አፍሪካውያን ዳግማዊ አድዋን ያረጋገጡበት ድል መሆኑን በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር አቶ እንዳለ ንጉሴ አስታወቁ።

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር አቶ እንዳለ ንጉሴ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ቀደም ሲል ዋናውን የቅኝ ግዛት አሸንፋ ለጥቁሮች ምሳሌ የሆነች አገር ናት። ከሰሞኑን በኢትዮጵያ መንግስትና በሕወሓት መካከል የተደረገው ስምምነት ኢትዮጵያ ዳግማዊ አድዋን አረጋግጣለች፤ በመጣው ውጤት መላ አፍሪካውያን ደስተኞች ናቸው።

አቶ እንዳለ እንደገለጹት፤ ድርድሩን ከአፍሪካ እጅ ለማስወጣት ያልተደረገ ጥረት የለም፤ ነገር ግን

የሠላም ስምምነቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ - ሃዱሽ አብርሃ







ዜና

# ማሕበረሰቦችና ተቋማት በግላቸው ውሃ የሚያለሙበት ዕድል ይመቻቻል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት ማሕበረሰቦች እና ተቋማት በግላቸው ውሃ የሚያለሙበት ሁኔታ እንደሚመቻች የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ገለፀ።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስትሩ ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ኢተፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የንፁህ መጠጥ ውሃ ተደራሽነትን በመንግሥት አቅም ብቻ ማረጋገጥ አዳጋች ነው። በመሆኑም በ2015 በጀት ዓመት ነባር የውሃና ውሃ ነክ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማሻሻል ማሕበረሰቦች እና ተቋማት በግላቸው ውሃ የሚያለሙበት ሁኔታ ይመቻቻል።

ማሕበረሰቡና የግል ተቋማት በግላቸው ውሃ የሚያለሙበትን ዕድል መፍጠር በተለይ በከተሞች ያሉ የመጠጥ ውሃ ተቋማት አቅማቸው ከፍተኛ እንዲሆን ይረዳል ያሉት ሚኒስትሩ፣ ንፁሕ የመጠጥ ውሃ ብክነት እንዲቀንስም እንደሚረዳና ስለውሃ ጉዳይ ያገባኛል ብሎ ሁሉም ሰው እንዲንከባከብ ማድረግ የሚያስችል መሆኑን ገልፀዋል። በመሆኑም በ2015 በጀት ዓመት ጀምሮ ሕብረተሰቡ እና የግል ተቋማት የመጠጥ ውሃ ግንባታ ላይ እንዲሳተፉ የሚያደርግ አስቻይ ሁኔታዎች ሥራ ይጀመራል ሲሉ ተናግረዋል።

አስቻይ ሁኔታ በመፍጠሩ ሂደትም ለረጅም ዓመታት ሲያገለግል የቆየውና የሀገሪቱን አሁናዊ ሁኔታ የማይመጥነው የውሃና ኢነርጂ ፖሊሲ የሚከለስ ይሆናል ብለዋል።

ፖሊሲው ሲስተካከል ባለሃብቶች፣ ተቋማትና ሕዝቡ በዘርፉ መሳተፍ የሚችሉበት ዕድል በመፍጠር መሰረት የሚጥል ይሆናልም ነው ያሉት። የፖሊሲው መከለስ በቀጣይ ለብዙ ዓመታት የኢትዮጵያን የውሃ ችግር የሚፈታበት ይሆናልም ሲሉ አብራርተዋል።

ከዚህ ጎን ለጎን የሀገሪቱን በተበታተነ መልኩ የተቀመጠ የውሃ ሃብት መረጃ በአንድ ቋት በማሰባሰብ ሀብቱን በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል ይሆናል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ሀብቱ ተመዝግቦ አለመቀመጡ በአግባቡ ለመጠቀም እንዳይቻል አድርጎ መቆየቱን ጠቁመዋል።

እንደ ሚኒስትር ሀብታሙ ገለፃ፤ የኢትዮጵያ የውሃ ሃብት መረጃ በጣም የተበታተነ በመሆኑ ከ2015 በጀት ዓመት ጀምሮ ከቀበሌ ጀምሮ ያሉ የውሃ ተቋማትን የሚያሳይ ዘመናዊ የውሃ መረጃ በሀገር አቀፍ ደረጃ ይደራጃል። የተቋማቱን የብልሽትና የአገልግሎት ሁኔታ፤ ውሃ የማምረት አቅምና ሌሎችም መረጃዎች በዚህ አማካኝነት የሚያዙ ይሆናል። በዚህ መልኩ የኢነርጂ ተቋማትም በአግባቡና በዘመናዊ መረጃቸው እንዲያዝ ይደረጋል።

የውሃ ሃብት መረጃዎች በአግባቡ እንዲያዙ መደረጉ ሃብቱን በአግባቡ ለመጠቀም እንዲቻል እንደሚያደርግም ዶክተር ኢንጂነር ሀብታሙ ተናግረዋል።

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ የንፁሕ መጠጥ የውሃ አቅርቦት እንዲኖር የሀብት ማፈላለግ ሥራ ይሠራል ያሉት ሚኒስትሩ፤ በተለያዩ ቦታዎች ያሉ የንፁሕ መጠጥ ውሃ እጥረቶችን ለመፍታትም ያሉ የውሃ ተቋማትን የማሻሻል ሥራዎች እንደሚሠሩም አብራርተዋል።

በተለያዩ አካባቢዎች የተጀመሩ የውሃ ፕሮጀክቶች ላይ ክትትል እየተደረገ መሆኑን ሚኒስትሩ ተናግረው፤ በ2015 በጀት ዓመት የቦንጋ የውሃ ፕሮጀክት የሚጠናቀቅ መሆኑን ጠቅሰዋል። በሌላ በኩል በአዳማና ዘዋይ አካባቢ የተጀመሩ የውሃ ፕሮጀክቶች በበጀት ዓመቱ በግንባታ ደረጃ እያሉ የውሃ አቅርቦት እንዲሰጡ ይደረጋል ብለዋል።


አርሶ አደር አለኸኝ ደምለው


አርሶአደር ሽፈራው ክንዴ


አቶ መኳንንት አዳሙ


ወጣት መለሰ ቢልልኝ

# የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ከምድረ በዳነት የታደጋት ብራቃት

**አዲሱ ገረመው**

የአማራ ክልል ርዕሰ መዲና ከሆነችው ባህር ዳር ከተማ 55 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። የሰሜን ሜጫ ወረዳ ብራቃት ቀበሌ። ከባድ ዝናብ ከሚያገኙት አካባቢዎች አንዷ ናት። ክረምት በመጣ ቁጥር ሰቀቀን የሚገባቸው አርሶ አደሮቿ የዘሩት ሁሉ የጎርፍ ሲሳይ እየሆነ ካስቸገራቸው ዓመታት ነጉደዋል። በአካባቢው የመሬት ናዳው ከጀመረ በርካታ ዓመታትን አስቆጥሯል።

በዚህ አካባቢ በሥነ ምህዳር መጎሳቆል ምክንያት እንኳንስ ሰው እንስሳቱ የሚበሉትን በማጣታቸው ጉዳት ሲደርስባቸው ቆይቷል። የእርሻ መሬታቸው ጎርፍ ጠራርጎ ሰብሉን ሲያጠፋ፣ የግጦሽ መሬቱ ደግሞ እየተሰነጠቀ መጥቶ አካባቢው የከፋ ችግር ውስጥ እንደነበር የአካባቢው ነዋሪዎች ይናገራሉ።

የብራቃት ቀበሌ አስተዳዳሪ አቶ መኳንንት አዳሙ እንደሚሉት፤ ብራቃት በአማሩና በተዋቡ እጽዋት የተሞላች፣ ፍሬ የማይታጣባት ቦታ ነበረች። ተፈጥሮ እስኪያጠወልጋት ድረስ ልምላሜ ይታይባት ነበር። ሆኖም በአየር ንብረት ለውጥ፣ ጎርፍ ባስከተለው ጉዳት አካባቢው ሙሉ ለሙሉ ምደረ በዳ ሆኖ ቆይቷል።

አቶ መኳንንት እንደሚሉት፤ ብራቃት መሬቶቿ እረፍትን፣ ነዋሪዎቿ ልማትን፣ መንፈሷ ልምላሜን በሻተ ጊዜ በ2006 ዓ.ም በውሃና መሬት ሀብት ማእከል አስተባባሪነት ጉርፍን በማስቀረት፣ የተራቆተውን መሬት በማልማት የተፈጥሮ ሀብትን ከምርምር ጋር በማያያዝ የህዝቡን የባለቤትነት ስሜት በማዳበር በትብብር የሚሰራ "የመማሪያ ተፋሰስ" ፕሮጀክት ተጠቃሚ የመሆን እድልን አገኘች።

ልዩ ምድራዊ ገጽታ ተሰጥቷት የተፈጠረችው ብራቃት ሰውም እንስሳቱም ከእርሷ እንዲመገቡ አልተከለከሉምና ዳግም የመልማትና ሚዛኑን የጠበቀ ተፈጥሮ እንዲኖራት ተስፋዋ እየጨመረ መምጣቱን አቶ መኳንንት ያስረዳሉ።

በውሃና መሬት ሀብት ማእከል የተፋሰስ ልማት ባለሙያ ወጣት መለሰ ቢልልኝ፣ ቀበሌዋ በከፍተኛ የአፈር ናዳና በጐርፍ መሸርሸር አደጋ ትቸገር እንደነበር ያስታውሳል። አካባቢው በተፋሰስ ልማት ከታቀፈ በኋላ የተለያዩ የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ተጀምረው ወደነበረበት ተፈጥሮአዊ ገጽታ ለመመለስ ቁርጠኝነትን የሚጠይቅ ሥራ መከናወኑንም ነው የጠቀሰው።

በፕሮጀክቱ የወል መሬት፣ የሳር ግጦሽ ልማት፣ ከብቶችን ከማሰማራት ይጎዳ የነበረውን መሬት ለማከም ለእንስሳቱ መኖን በመጠለያ በመስጠት ማቆየት፣ የእርከን ሥራ፣ ችግኝ የማዘጋጀትና የተራቆቱ መሬቶችን የማልማት ሥራ በሰፊው እንደተከናወነ ተገልጿል።

በቀበሌዋ ልዩ ስሙ ወቃሪ በምትባል አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አርሶአደር ሽፈራው ክንዴ፤ የአፈርና የውሃ ጥበቃ ባለመሰራቱ ከፍተኛ የሆነ የአፈር መሸርሸርና ናዳ፣ የጐርፍ መጥለቅለቅ፣ በማጋጠሙ ዘር ዘርቶ ምርት የማያገኙበት ሁኔታ እንደነበር ይናገራሉ። በዚህም አስቸጋሪውን የህይወት ውጣ ወረድ ተጋፍጠው ከርመዋል።

ፕሮጀክቱ ከጀመረ ወዲህ ባገኙት ሥልጠናና ቴክኒካዊ ድጋፍ አስተሳሰባቸውን በመለወጥ በችግኝና ፍራፍሬ ልማት፣ ከብት በማደለብ እንዲሁም የግጦሽ መሬትን በማሻሻል ተጠቃሚ መሆናቸውን አርሶ አደሩ ይገልጻሉ። አሁን ላይ የተፋሰስ ልማት ስራዎች በመከናወናቸው የገጠር ህይወት በማይመስል ደረጃ ኑሯቸው እንደተሻሻለ ደስታን በሚያንጸባርቁ ቃላት ይናገራሉ።

አርሶ አደሩ አትክልትና ፍራፍሬውን በቅርብ ከጓሮ ማግኘት ችለዋል። የእንስሳት መኖውን በበቂ ሁኔታ ያገኛሉ። ልጆቻቸው እንስሳትን ይዘው መኖ ፍለጋ አይሮጡም። መሬታቸውም እንስሳት ስለማይሰማሩባቸው ታክመው ወደ ቀድሞ ገጽታቸው ተመልሰዋል። የመጠጥና የአትክልት የውሃ አመራጮችን አግኝተዋል። እርከን ከመስራት ባሻገር እርከንን እያለሙ ይገኛሉ። ይህን ለሌሎች ተሞክሮ በማካፈል አካባቢው እንዲለወጥ የራሳቸውን ድርሻ ተወጥተዋል።

የቀበሌዋ ነዋሪ አርሶ አደር አለኸኝ ደምለው እንደሚሉት፤ አካባቢው ከ2006 ዓ.ም በፊት 176 ተጠቃሚ ያለው የወል መሬት ከብት የሚሰማራበትና አርሶ አደሩ የማይጠቀምበት ነበር። መሬቱ በራሱ ጊዜ ተንዶ አርሶ አደሩን ለችግር የዳረገበት ነበር። ፕሮክቱን ተግባራዊ ለማድረግ ከማህበረሰቡ ጋር በተደረገ ውይይት መሬቱን ከንክኪ ነጻ በማድረግ ሁሉንም ማህበረሰብ ያማከለ ጥቅም እንዲሰጥ ተደርጓል።

መሬቱ ከንክኪ ነጻ ባልነበረበት ወቅት በአፈር መሸርሸር ምክንያት እየደረሰ በነበረው ችግር ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው የቀሩበት አጋጣሚ እንደነበር በማስታወስ፤ መሬቱ ከንክኪ ነጻ ከተደረገ ወዲህ አንድ አርሶ አደር የራሱን ድርሻ የግጦሽ ሳር እየሸጠ እንዲተዳደር አስችሎታል ብለዋል። አሁን ላይ ብዙ እማወራዎች ልጆቻቸውን ማስተማር የቻሉበት ጊዜ እንደሆነም ጠቅሰዋል።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ማህበረሰቡ የፕሮጀክቱ ጥቅም ስለገባው በከብት ማደለብና እንስሳት እርባታ፣ በችግኝ ማፍላትና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብት ስራ ላይ ተሰማርቶ ተጠቃሚ እየሆነ ይገኛል። መሬቱም አገግሞ ለሎች አካባቢዎች ምሳሌ ሊሆን የሚችል የግብርና ስራን እያስተናገደ ስጋት ውስጥ የነበረውን ህዝብ ታድጐ በአግባቡ እየመገበ ይገኛል።

ፈጣሪ ብራቃት ለተባለችው ቀዬ መንከባከቢያ መንገድ ፈጥሮ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ከተደረገ ወዲህ ከነሙሉ ክብሯ እንዳለች ሙሉ ገጽታዋን ለተመለከታት ታስታውቃለች። የትናንትናዋ ምድረ በዳ መሬት ሰው እንደ ልቡ በልቶ ህጻናት ቦርቀው የሚያድሩባት ምድራዊ ገነት ሆናለች። መልካሙን ፍሬ ለማግኘት ሌት ተቀን ሰርተው የለወጧት አርሶ አደሮች ዛሬን በደስታ እየኖሩባት ነው።

የአካባቢውን ሥነ ምህዳር ለመጠበቅ ተብሎ የተዘሩ ተክሎች መዓዛቸው ልብን ይመስጣል፣ ፍራፍሬዎቹ ከጣዕማቸው የተነሳ ከአፍ የሚጠፉ አይደለም።

# የአዲስ ቴክኖሎጂ አገልግሎት ትሩፋት ተጠቃሚ የሆነችው አዳማ

**ጌትነት ምህረቴ**

የስምጥ ሸለቆዋ እምብርት ከተማ ናት። በንግድና የኮንፈረስ ቱሪዝም ባላት ሰፋ ያለ አገልግሎት ትታወቃለች- አዳማ።

በዚች በከፍተኛ ፍጥነት እያደገች ባለች ከተማ ሰሞኑን አዲስ የ5 ጂ ቴክኖሎጂ ይፋ ተደርጓል። ይህ የአምስተኛው ትውልድ የኔትዎርክ አገልግሎት ከተማዋን በእጅጉ ምቹና ዘመናዊ ለማድረግ የሚያስችል ነው።

ኢትዮ ቴሌኮም ዓለም የደረሰበትን የአምስተኛ ትውልድ (5ጂ) የኔትወርክ አገልግሎት በአዳማ ከተማ አስጀምሯል። ይህም በንግድና በቱሪዝም ኮንፈረስ የምትታወቀውን የአዳማ ከተማ የንግድ እንቅስቃሴዎች ለማሳለጥ የሚያስችል መሆኑ ተገልጿል። ከተማዋን የኢኮኖሚ ማዕከል ለማድረግም ጥቅሙ ፈርጀ ብዙ ነው ተብሏል።

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ስራ አስፈፃሚ ወይዘሪት ፍሬህይወት ታምሩ በአዳማ ከተማ 5ጂ የኔትወርክ አገልግሎት በማስጀመሪያ ስነ ስርዓት ላይ እንደገለፁት፤ ከዚህ ቀደም በአዲስ አበባ ከተማ ፤አሁን ደግሞ በአዳማ የጀመረውና በቀጣይ በሌሎች ከተሞች የሚስፋፋው 5ጂ ኔትወርክ አገልግሎት ዲጅታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ያስችላል። የቴክኖሎጂ አገልግሎት በመጠቀም ከተማዋን ዘመናዊና ለነዋሪዎቿ እንዲሁም ለእንግዶቹ የተመቸች ለማድረግ የሚያስችል መሆኑንም ጠቅሰዋል።

ኩባንያው የደንበኞቹን የዕለት ተዕለት የንግድ እንቅስቃሴ ለማዘመንና ለማፋጠን በሰፊው እየሰራ ነው። ከእነዚህም ማሳያዎች አንዱ ከፍተኛ የንግድና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ባለባቸው ከተሞች የ5ጂ አገልግሎት የማስፋፋት ስራ መሆኑን አንስተዋል። ቴክኖሎጂው የአገራችን



ወይዘሪት ፍሬህይወት ታምሩ

የዲጂታል ኢኮኖሚ እንቅስቃሴን ለማነቃቃትና በህዝቡ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ ከፍተኛ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል መሆኑን ያብራራሉ።

ኢትዮጵያ በብዙ አስቸጋሪና ፈተናዎች ውስጥ ሆና በአፍሪካ 5ጂ የኔትዎርክ ቴክኖሎጂን ካስጀመሩ ጥቂት የአፍሪካ አገሮች አንዷ መሆኗን ጠቅሰው፤በአዳማ ከተማ የተጀመረው ይህ ቴክኖሎጂ ተቋማት ብዙ ከሰሩበት ከፍተኛ ለውጥና ዕድገት ማምጣት ያስችላል ሲሉ ገልጸዋል።

5ጂ ኔትወርክ አገልግሎት ፍጥነቱና አገልግሎቱ ወደር የማይገኝለት መሆኑን አመልክተው፤ የማዕድን ዘርፉን፣ግብርናውንና የመንግስት ሥራዎችን በቀላሉና በአጭር ጊዜ ለማከናወን ያስችላል። የተሻለች ከተማን ለመገንባት ይረዳል ነው ያሉት።

በተለይ የከተማዋን ፀጥታና ደህንነት ለማስጠበቅ፣የንግድ እንቅስቃሴን ለማሳለጥ፣ ኢንቨስትመንት ለማቀላጠፍና የኢንዱስትሪዎችን ውጤታማነት ለማሳካት የሚያስችል መሆኑን ወይዘሪት ፍሬህይወት ይገልጻሉ።

ለአብነትም በሰው የማይሰሩና ከፍተኛ አደጋ የሚያስከትሉ የኢንዱስትሪ ስራዎችን 5 ጂ ኔትዎርክ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሮቦቶችን በመጠቀም መስራት የሚቻል መሆኑን አንስተዋል። ሌላው ግብርናውን ለማዘመንና ምርታማ ለማድረግ ጸረ ተባይና ጸረ አረም የኬሚካል ርጭት ለማካሄድ በ5ጂ ኔትዎርክ ቴክኖሎጂ ሰው አልባ አውሮፕላኖችን መጠቀም የሚቻል መሆኑን በምሳሌነት አንስተዋል።

ኩባንያቸው ዲጂታል ኢትዮጵያን ለማሳካት ፈርጀ ብዙ ስራዎችን እየሰራ እንደሚገኝ ገልጸው፤ አዳማ ከተማን ስማርት ሲቲ ለማድረግ የታቀደውን ፕሮጀክት ለማሳካት ኢትዮ ቴሌኮም የሚጠበቅበትን ሁሉ ድጋፍና ትብብር ያደርጋል ይላሉ።

የአዳማ ከንቲባ አቶ ሀይሉ ጀልዱ በበኩላቸው እንደገለፁት፤ ኢትዮ ቴሌኮም በአዳማ ከተማ ያስጀመረው 5ጂ ኔትዎርክ ቴክኖሎጂ አገልግሎት አስተዳደሩ ከተማዋን ስማርት ሲቲ ለማድረግ የያዘውን ፕሮጀክት ለማሳካት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይናገራሉ።

በተለይ ከቀበሌ ጀምሮ ጠንካራ መዋቅር ለመገንባት፣ የተሟላ መሰረተ ልማት ለመዘርጋትና ፈጣን የመንግስት አገልግሎት ለመስጠት በከተማ አስተዳድሩ የተጀመሩ ስራዎችን ያፋጥናል ነው ያሉት። ይህም በአጭር ጊዜ ከተማዋን ዘመናዊ፣ለነዋሪዎቹ የተመቸችና ሁሉም ለመንብኘት የሚናፍቃት ከተማ ለማድረግ ይረዳል ባይ ናቸው።

አዳማን ስማርት ሲቲ የማድረግ ዕቅድ የከተማዋን ለመሰረተ ልማት፣ ለመልካም አስተዳደር ማነቆ የሆኑ የአገልግሎት ችግሮች ለመፍታትና ዲጂታላይዝ ለማድረግና አጠቃላይ የህብረተሰቡን የአኗኗር ዘይቤ ለመለወጥ ያለመ ፕሮጀክት መሆኑን ገልጸዋል።

# የሠላም ስምምነቱ ኢኮኖሚው እንዲያገግም ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የሠላም ስምምነቱ ለጦርነት ሲውል የነበረውን በጀት ወደልማት በማዞር ኢኮኖሚው እንዲያገግም ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው የምጣኔ ሃብት ባለሙያው ቆስጠንጢኖስ በርኸተስፋ (ዶክተር) ገለጹ። ኢኮኖሚው ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን በአንዳንድ ስግብግብ ነጋዴዎች የሚፈጠሩ አሻጥሮችን እና ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን መፍታት እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሠላም ስምምነቱ በሁለቱም ወገኖች በኩል ለመሳሪያ ግዥና ለተለያዩ ጉዳዮች የሚወጡ በጀቶች በሙሉ ወደ ልማት በማዞር በአገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ እንድምታ ያለው ነው።

ስምምነቱ የሚኖረው ትርጉም የሰው ህይወትን ማዳን፣ በጦርነት የተጎዱትን ህዝቦች መልሶ ማቋቋም፣ የፈረሱ መሰረተ ልማቶችን እንደገና ለመገንባት የሚያስችል ነው ያሉት ዶክተር ቆስጠንጢኖስ፤ በተጨማሪም እስካሁን ድረስ ጦርነት በመኖሩ የውጭ አገር ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ ላለመምጣት ሲወስኑ ነበር ብለዋል። አሁን ላይ ሠላም መጥቷል ብለው ወደ ኢትዮጵያ ገብተው ኢንቨስት ለማድረግ ፍላጎት ይኖራቸዋል ሲሉም ተናግረዋል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ እንዲህ አይነቶቹ የሠላም



ፎቶ- በእዮብ ተፈራ

**ዶክተር ቆስጠንጢኖስ በርሄተስፋ**

ስምምነቶች ሲደረጉ ከፍተኛ የውጭ እርዳታ የሚያመጡ ናቸው። የተጎዱ ህዝቦችን መልሶ ለማቋቋም የዓለም ባንክን ጨምሮ የአውሮፓ ህብረትና የተለያዩ ዓለም አቀፍ ረጂ ድርጅቶች በከፍተኛ ደረጃ ድጋፍ እንዲያደርጉ የሚያስችል ነው ብለዋል።

ዶክተር ቆስጠንጢኖስ እንደተናገሩት፤ ህዝቡ በጦርነት ምክንያት የእርሻ ስራን በአግባቡ ማከናወን አልቻለም ነበር፤ የቁም እንስሳት ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ ከተሞች ፈራርሰዋል፤ ማምረት አቁመው ነበር። ስለዚህ ስምምነቱ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለመጠገን ወሳኝ ነው። በአጠቃላይ የሰውን ህይወት እንደገና መገንባት ማለት መሆኑን ገልጸዋል።

የሠላም ስምምነቱ ኢኮኖሚው በብዙ መልኩ እንዲያገግም ያደርጋል ያሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፤ ጦርነቱ እንዳለ ሆኖ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ችግር ከጦርነት ባሻገርም ስለሆነ ብዙ ተግዳሮቶች ስላሉ መፍታት ያስፈልጋል ብለዋል።

በተለይ ከታችኛው የወረዳ አስተዳደር አካባቢ ምቹ አሰራሮች መኖር አለባቸው፤ ትልቁ ስራ የሚሰራው ወረዳ ውስጥ ነው። ኢንቨስትመንት፣ ጤና፣ እርሻና መሰል ስራዎች የሚሰሩት ወረዳ ውስጥ ነው። ስለዚህ በወረዳው አካባቢ ያለው አስተዳደር በብቃትና ክህሎት መመራት አለበት። ይህ ካልሆነ ኢኮኖሚውን ለማሳደግ እንቅፋት ይፈጠራል ሲሉም አክለዋል።

በሌላ በኩልም ሙስና በከፍተኛ ደረጃ ኢትዮጵያ ውስጥ ተንሰራፍቷል። የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኦዲት ሪፖርት በሚያቀርቡበት ወቅት በርካታ ጉድለቶችን እንሰማለን። የሙስናን አደገኛነት ምን ያህል እንደተንሰራፋ ነው። ይህ የሚያሳየው ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ትልቁ ተግዳሮት ሙስና መሆኑ ነው። በተጨማሪም የፋይናንስ ተቋሞቻችንና የፋይናንስ አስተዳደር ያሉባቸውን ችግሮች አጥርተው ከሌላው አገር መወዳደር ያስፈልጋል ሲሉ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ገልጸዋል።



# ኢትዮጵያ ለስንዴ ልማት የሰጠችው ትኩረት በዓለም ገበያ የስንዴ ምርት እጥረትን እንደሚቀርፍ አምባሳደሮች ተናገሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ለስንዴ ልማት የሰጠችው ትኩረት ከአገር ውስጥ ባለፈ በዓለም ገበያ ያለውን የስንዴ ምርት እጥረት ለመቅረፍ እገዛ እንደሚያደርግ በኢትዮጵያ የፈረንሳይና የብሪታኒያ አምባሳደሮች ተናገሩ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በአዲስ አበባ ከሚገኙ የተለያዩ አገራት አምባሳደሮችና ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት የስራ ኃላፊዎች ጋር በምእራብ አርሲ ዞን ገደብ አሳሳ እየተካሄደ ያለውን የስንዴ ምርት አሰባሰብ ሂደት ጎብኝተዋል።

በጉብኝቱ ከተሳተፉት መካከል በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር ሬሚ ማሬሾ፣ በኢትዮጵያ የእንግሊዝ አምባሳደር አልስቴር ማክፔል፣ በኢትዮጵያ የጀርመን አምባሳደር ስቴፈን ኦዎር እንዲሁም በኢትዮጵያ የጣሊያን አምባሳደር አውጉስቲኖ ፓሌስ እና ሌሎች የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ አባላት ይገኙበታል።

በኢትዮጵያ የፈረንሳይ አምባሳደር ሬሚ ማሬሾ ኢትዮጵያ ለስንዴ ልማት ትኩረት ሰጥታ እየሰራች መሆኗን በጉብኝታቸው መመልከታቸውን ጠቅሰዋል።

በዓለም የጂኦ ፖለቲካ መለዋወጥ ምክንያት ስንዴን ጨምሮ የምግብ ሸቀጦች ዋጋ እጅግ እየናረ መምጣቱን ጠቅሰው፤ይህም ለዓለማችን ወቅታዊ ፈተና ሆኗል ነው ያሉት። ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ ለስንዴ ምርት ትኩረት ሰጥታ መስራቷ የሚደገፍ መሆኑን ነው የገለጹት።



**አምባሳደር አልስቴር ማክፔል**



**አምባሳደር ሬሚ ማሬሾ**

የፈረንሳይ ኩባንያዎች በተለይ በኢትዮጵያ በቢራ ገብስ ምርት ላይ መዋእለ ንዋያቸውን በግብርናው ዘርፍ እያዋሉ መሆኑን ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ የብሪታኒያ አምባሳደር አልስቴር ማክፔል በበኩላቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ የስንዴ ምርት እጥረት መኖሩን ጠቅሰዋል።

ለዚህም እንደ ኢትዮጵያ ሌሎች ሀገራት በራስ አቅም ስንዴን በማምረት ለወጪ ንግድ ለማቅረብ ሊሰሩ እንደሚገባ ተናግረዋል።

ብሪታኒያ ከኢትዮጵያ ጋር በግብርናው መስክ የተሻለ ትብብር እንዳላት ጠቅሰው፤ በቀጣይ ይህ ትብብር ሊጠናከር ይገባል ነው ያሉት።

ከዚህ አኳያ በርካታ የብሪታኒያ ኩባንያዎች በኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ ሊሰማሩ እንደሚገባ መክረዋል።

በአሜሪካ የኢትዮጵያ አምባሳደር ስለሺ በቀለ ኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በግብርና መካናይዜሽን ወጤታማ ስራ እያከናወነች መሆኗን ተናግረዋል።

የግብርና መካናይዜሽን በተለይ በምርት ወቅት የሚከሰትን የምርት ብክነት በመከላከል ምርታማነት እንዲጨምር ትልቅ ፋይዳ እንዳለው አብራርተዋል። በዚህም በኢትዮጵያ የግብርና ምርታማነት ወደተሻለ ደረጃ እያደገ መምጣቱን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ ከመኸር በተጨማሪ ለበጋ ስንዴ ልማት ልዩ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ሲሆን፤ በዘንድሮው የበጋ ወቅትም በአገር አቀፍ ደረጃ በ1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ በኩታ ገጠም ስንዴ በማልማት 52 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለመሰብሰብ እቅድ ተይዟል። በዘንድሮው ዓመትም የስንዴ ምርትን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ እቅድ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል።

# የዲያስፖራ ማኅበራቱ ለመልሶ ግንባታው ዝግጁ መሆናቸውን አስታወቁ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በጦርነቱ የወደሙ ተቋማትን ለመገንባትና የተፈናቀሉ ዜጎችን ወደ ቀዬአቸው ለመመለስ የበኩላቸውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆናቸውን የዲያስፖራ ማኅበራት አስታወቁ። በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰውን ስምምነት በደስታ እንደሚቀበሉትም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያን እናድን በዩናይትድ ኪንግደም ግብረ ኃይል አስተባባሪ አቶ ዘላለም ተሰማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዲያስፖራው በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመታት ኢትዮጵያን ለማዳንና ለመከላከል በዲፕሎማሲ እና በፖለቲካው ረገድ እንዲሁም በሌሎችም መስኮች ሰፊ የሆነ ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል።

የዲያስፖራው ማኅበረሰብ የሀገሪቱን ነፃነት እና ሉአላዊነት ሲከላከል ቆይቶ ሠላማዊ ንግግር ተደርጎ የሠላም ስምምነት መፈረሙ እንደ ትልቅ ድል የሚቆጠርና ሠላምና ኢትዮጵያዊነት ያሸነፉበት ስምምነት ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ከግጭትና ጦርነት አዙሪት ውስጥ መውጣት የምትችልበትን ዕድል እና አጋጣሚ ሁሉ መጠቀም ስለሚያስፈልግ ዲያስፖራው ማኅበረሰብ ይህንን ስምምነት የሚቀበለው በበጎ መሆኑን ገልጸው፤ በስምምነቱ መሰረት ሠላም ከወረደ ዲያስፖራው በጦርነት የፈረሰውን ተቋምና የተፈናቀለውን ማኅበረሰብ መልሶ ለማቋቋምና ለመገንባት የሚደረጉ ጥረቶች ላይ ተገቢውን አስተዋፅዖ ያደርጋል ብለዋል።

የሠላም ስምምነቱ ላይ ለመድረስ ብዙ ኢትዮጵያውያን ዋጋ ከፍለዋል ያሉት አቶ ዘላለም፤ በመጪዎቹ ጊዜያት ግጭቱንና ጦርነቱን ብቻ ሳይሆን ሠላሙንም ማሸነፍ ያስፈልጋል ሲሉ ገልጸዋል። የሠላም ስምምነቱ ለዘላቂ ሠላም በር ይከፍታል ብለው ተስፋ እንደሚያደርጉም አክለው ተናግረዋል።

የግብረ ኃይሉ አስተባባሪ ድሉ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ጭምር መሆኑን ጠቁመው፤ የውጭ ጫና እንደተጠበቀ ሆኖ በተለይ ደግሞ የሠላም ስምምነቱ በአፍሪካ ሕብረት መደረጉ ድርብ ድል መሆኑን አንስተዋል።

ሆኖም የሠላም ስምምነቱ የመጀመሪያ ምዕራፍ እንጂ የመጨረሻ አለመሆንኑ የተናገሩት አቶ ዘላለም፤ ስምምነቱ በሠላምና በተሳለጠ መንገድ ያለምንም ተንኮል እና ጫና ይተገበራል የሚል ተስፋ አለን ብለዋል።

በተመሳሳይ ኢትዮ-ካናዳውያን ኔትወርክ ለማኅበራዊ ድጋፍ የዲያስፖራ ማህበር ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በላከው መግለጫ፤ በኢትዮጵያ መንግስት እና በሕወሓት መካከል ጦርነት ለማቆም የተደረሰውን የሠላም ስምምነት በደስታ እንደሚቀበለው ገልጿል። በሂደቱ ለተሳተፉም ከፍተኛ ምስጋና አቅርቧል።

በጦርነቱ ምክንያት የፈረሱ መሰረተ ልማቶች መልሶ በመገንባት፣ ለተፈናቀሉት አፋጣኝ ሰብዓዊ ርዳታ በመስጠት እና ለሀገሪቱ ሠላምና ብልፅግናን በማስፈን ረገድ የኢትዮጵያውያን ዲያስፖራዎች ሚና ከፍተኛ መሆኑን እንገነዘባለን ያለው መግለጫው፤ ይህንን ለማረጋገጥ የዲያስፖራው ማህበረሰብ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል ብሏል።

የሠላም ዕድል በአፈፃፀሙ ሂደት ቁርጠኛ ጥረት የሚጠይቅና የረዥም ጊዜ ሂደት መሆኑን የጠቀሰው የማህበሩ መግለጫ፤ ይህ የ፤ላም ስምምነት ለዘላቂ ሠላም ግንባታ መሰረት እንደሚሆን ተስፋውን በመግለፅ የስምምነቱ ተግባራዊ መሆን ሠላማዊ፣ ዲሞክራሲያዊ እና አንድነቷን የጠበቀች ኢትዮጵያን አዲስ ምዕራፍ ያመጣል ብሏል።

ዜና

# «ከስምምነቱ ጋር ተያይዘው የሚወጡ መረጃዎችን የሚቆጣጠር የሚዲያ ፎረም ሊቋቋም ይገባል»

*- ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ*
*የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዚዳንት*

**ሳሙኤል ወንደሰን**

<u>አዲስ አበባ</u>፦ ከሠላም ስምምነቱ ጋር ተያይዘው የሚወጡ የመገናኛ ብዙኃን መረጃዎች የሀገርን ክብር፣ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በሚጠብቅ መልኩ የሚቆጣጠር የሚዲያ ፎረም ሊቋቋም እንደሚገባ የአሐዱ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ዋና ሥራ አስኪያጅ እና የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዚዳንት ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ አሳሰቡ።

የአሃዱ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ዋና ሥራ አስኪያጅ እና የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዚዳንት ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ከስምምነቱ ጋር ተያይዘው የሚወጡ መረጃዎችን የሚቆጣጠር የሚዲያ ፎረም ሊቋቋም ይገባል። ይህም መረጃዎች በትክክለኛው መንገድ እንዲሰራጩ ያደርጋል።

በሰሜን የተደረገው ጦርነት እጅግ ብዙ ውድመቶችን አድርሷል ያሉት ጋዜጠኛ ጥበቡ፤ ንፁሃን ህይወታቸውን አጥተዋል፤ ሴቶች ተደፍረዋል፤ ህፃናት ተርበዋል፤ መሰረተ ልማቶች ወድመዋል፤ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ደርሷል። ስለዚህ ጉዳዩ የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ከምንጊዜውም በላይ ሚዲያዎች ጥንቃቄ ሊያደርጉ ያስፈልጋል ብለዋል።

ህዝብ እንኳን ቢሳሳት ሚዲያው የመሪነት ሚናውን በመጠቀም ህዝቡን ወደ ትክክለኛ አቋም መመለስ ይኖርበታል ያሉት ጋዜጠኛ ጥበቡ፤ መንግስትና የሚዲያ ባለሙያዎች ተቀራርበው በአንድ መድረክ እየተነጋገሩ የስምምነቱን አተገባበር የሀገርን ክብር፣ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በሚጠብቅ መልኩ መቀየስ ይኖርባቸዋል። የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣንም ሚዲያዎችን የሚቆጣጠርና የሚደግፍ ስለሆነ ትልቅ ኃላፊነት ይጠበቅበታል ብለዋል።

እንደ የማህበሩ ፕሬዚዳንት ገለፃ፤ የሠላም ስምምነቱን አስመልክቶ የሚወጡ መረጃዎች በጋዜጣዊ መግለጫ ቢሰጥ ሁሉም ሚዲያ እንደ ልቡ ሄዶ ሊናገረውና ሊዘግበው አይችልም። ይህም ከዚህ አካሄድ ውጭ የሚደረጉ የሴራና የአሉባልታ ትንታኔዎች ዋጋ እንዲያጡ ያደርጋል። ስለዚህ ሚዲያዎችን የሚቆጣጠር የሚዲያ ፎረም መዘጋጀቱ ነገሮችን በስርዓቱ ለማከናወንና የሀገርን ክብር ለመጠበቅ ያስችላል።

የሚዲያ ፎረሙ ሚዲያዎችን የመቆጣጠር፣ ሀሳብ የመስጠትና በስርዓት እንዲሄዱ ድጋፍ የማድረግ ሥራ ለመሥራት ያስችላል ያሉት አቶ ጥበቡ፤ ህዝብን ለችግርና ለሠላም እጦት ከሚዳርጉ ነገሮች መታቀብ የእያንዳንዱ ጋዜጠኛ ሀገራዊ ኃላፊነት ነው ሲሉም ተናግረዋል። ከዚህ አንፃር የተደረገው የሠላም ስምምነት ዘላቂነት እንዲኖረው መገናኛ ብዙኃን የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይገባል ብለዋል።

ጋዜጠኝነት በራሱ ሠላም አቀንቃኝነትና ለሠላም የቆመ ነው። አንዳንድ ጊዜ ባለማወቅ መገናኛ ብዙኃን ከስነ ምግባር ውጪ የሆነ ሥራን ይሰራሉ። ነገር ግን ትክክለኛ የመገናኛ ብዙሃን ሥራ ሠላምን ማስፈን ነው። ከዚህ አንጻር መገናኛ ብዙሃን ግጭቶች እንዳይከሰቱ፣ መረጃዎች ያላግባብ እንዳይወጡ የሚያስችል የሚዲያ ፎረም አስፈላጊ ነው ብለዋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎችና ተቋማት የሰሜን ጦርነቱን አይነት ጉዳዮች በመጠቀም ስም ለማግኘት ይጥራሉ። ስለዚህ ጋዜጠኞች ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በጥንቃቄ መስራት ይኖርባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

በሚዲያ ታሪክ ውስጥ እንደዚህ አይነት ሀገራዊ ችግሮች ሲመጡ መፍትሄ ለማምጣት የሚያመች ስርዓት አልተደራጀም ያሉት ጋዜጠኛው፤ ከዚህ በኋላ ሚዲያው አለም አቀፍ እውቅና እንዲኖረው፣ በነጻነት እንዲሰራ፣ አቅሙ እንዲጎለብትና ጠንካራ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉም ጠቁመዋል።

ከዚህም ባለፈ ሁሉም ሚዲያ በአንድ ሳምንት ውስጥ ምን እንዳደረጉ የሚያሳይና የኢትዮጵያን የእድገት ጉዞ ለአለም አቀፉ ማህበረሰብ ሚዲያ ቢደራጅ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት የሚጋዳደሩ አካላትን በቀላሉ ማጋለጥ ያስችላል። ይህን ማድረግ የሚቻለው ከአለም አቀፉ ማህበረሰብ ጋር የሚያግባቡ ቋንቋዎችን በሚዲያ በመጠቀም ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ በመሆኗ ከአዲስ አበባ መላውን አፍሪካ በሚዲያ መድረስ ይቻላል። ስለዚህ ይህንን ሁኔታ በመጠቀም የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ማስረዳትና ማስገንዘብ ያስፈልጋል። የሀገር ውስጥ ሚዲያዎችም ሀገርን የማቆም ሥራ ሊሰሩ ይገባል ብለዋል።

---

## ኢትዮጵያ በዓለም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የተደረገው የሠላም ስምምነት በስኬት እንዲጠናቀቅ ውሳኔ ላሳለፉት የሁለቱም ወገን ተሳታፊዎች ምስጋና ይገባቸዋል ብለዋል።

“በደቡብ አፍሪካ የተደረሰው የሠላም ስምምነት ሁላችንንም አረጋግቶናል፤ እፎይ እንድንልም አድርጎናል። የዚህ ዓይነት ስምምነት ላይ መድረስ ድፍረትና ታሪክን ይጠይቃል። የሁለቱም ወገን ተደራዳሪዎች በደረሱት የፖለቲካ ውሳኔ ላስገኙት ውጤት ምስጋና ሊቸራቸው ይገባል” ብለዋል።

በእርስ በርስ ጦርነት አሸናፊ የለም ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ በተደረሰው ስምምነት አሸናፊዋም ኢትዮጵያ ነች። የተሰበረውን መጠገን፣ የተጎዳውን ማጽናናት የሁሉም ኢትዮጵያውያን ኃላፊነት ነው ብለዋል።

አዲስ አበባ ያገኘችው ሽልማት የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ ጭምር ነው። በትምህርት ቤት ምገባ፣ በምግብ ዋስትና ማረጋገጥ፣ በደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም የታየው ውጤት ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ነው ያሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ።

“ከሚታየው ቆሻሻ ውስጥ የሚገዝፍ ሃብትን ማውጣት የግድ ነው። የማንጠራጠረው እውነት ጠንክረን ከሰራን አገራችንን በራሳችን አቅም ማበልጸግ እንደምንችል ነው። በደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ዘርፍ የተሰማሩ ወጣቶች በየቦታው የሚጣለውን ቆሻሻ ገንዘብ በማድረግ የአካባቢያቸውን ጽዳት ጠብቀዋል፤ ሃብት አፍርተዋል፤ ከእነርሱ አልፈው ለሌሎች መትረፍ ችለዋል። ህጻናቱና ወላጆቻቸው የሚፈተኑበትን ችግር ፈትቶ ለዚህ ድል መብቃት በቀላሉ የተገኘ አይደለም። ከፍተኛ የአመራር ጥረትና ትጋትን የሚጠይቅ ነው” ሲሉ ፕሬዚዳንቷ ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ ስታሸንፍ የምታሸንፈው አፍሪካ መሆኗን የገለጹት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ፤ የአፍሪካ ችግር በራስዋ በአፍሪካ መፈታት ይችላል የሚል የጸና አቋም የምናራምደው እሳቤ በይፋ ታይቷል፤ ዓለምም ተምሮበታል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ አዲስ አበባ ያገኘቻቸው ሁለት አለም አቀፍ ሽልማቶች ወቅታዊ ችግሮችን ከመፍታት አልፈን ብልጽግናን የምናረጋግጥበትን መንገድ ያሳየ ነው።

አገር የምትገነባው በስራ ነው፤ አዲስ አበባ የበካይ ጋዝ ልቀትን በመከላከል አለም አቀፍ ተሞክሮና ከ30 ሺ በላይ ተማሪዎችን በመመገብ ያገኘችው አለም አቀፍ ሽልማት የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካና አዲስ አበባ ለተቀመጡ ዲፕሎማቶች ጭምር ነው ብለዋል።

የደረቅ ቆሻሻን መልሶ በማልማት ከ4 መቶ ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ማግኘት ተችሏል። አባቶቻችን ነፃነቷን ጠብቀው ያስረከቡንን ሃገር፤ በትብብር ወደ አዲስ ከፍታ ምዕራፍ ለመውሰድ ትውልዳችን ታላላቅ አሻራዎችን በየእለቱ እያኖረ ይገኛል። ሽልማቱ የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የመላው አፍሪካ እና የከተማችን ነዋሪ የሆኑ የአለም አቀፍ ተቋማት እና የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ አባላት ጭምር ነው ብለዋል ከንቲባዋ።

ከንቲባ አዳነች፤ “አዲስ አበባ ተወዳድራ ያሸነፈቻቸው ሃገራት ታላቅነትን ስንመለከትና የስራችንን ውጤት የአለም እውቅና ሲሰጠው ስናይ ለበለጠ ውጤት እንድንተጋ፤ ለሌሎች ታላላቅ ስራዎች እንድንነሳሳ የሚያደረገን ስንቅና ትጥቅ በመሰነቅ ተጨማሪ ቁጭት በውስጣችን ፈጥሯል። ለሽልማቱ ያበቃን ደግሞ የመንግስታችን ትክክለኛ የትኩረት አቅጣጫና የፖሊሲ አቅጣጫ ነው” ብለዋል።

በመዲናችን 13 የምገባ ማዕከላትን በመገንባት በሺዎች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን መመገብ ተችሏል። በተማሪዎች ምገባ መርሀ ግብር የትምህርት መጠነ ማቋረጥን የቀነሰ ሲሆን በምግብ እጦት ራሳቸውን የሚስቱ ተማሪዎች በአግባቡ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ማስቻሉን አንስተዋል። በርካታ ተማሪዎች በተረጋጋ ሁኔታ የሚማሩበት በአገር አቀፍ ደረጃ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ያስጀመሩትን “የሌማት ትሩፋትን “ በከተማችንም ተግባራዊ በማድረግ በእርግጥም እውነተኛ ነፃ ሃገር፤ ብሎም ሁሉም ዜጋ የለመለመ ማዕድና ለጎረቤት የሚተርፍ ገበታ እንዲኖረው የያዝነውን ግብ እውን ለማድረግ እልህ ገብተን በትጋት በመስራት ማሳካት ይኖርብናል ሲሉ ከንቲባዋ ገልጸዋል።

የC40 የአፍሪካ ሪጂናል ዳይሬክተር ሃስቲንግስ ቺኮኮ፤ አዲስ አበባ እና ከንቲባዋ የC40 አላማዎች ለማሳካት እያደረጉ ያለውን ጥረት የሚደነቅ ነው ብለዋል። ይህ እውቅና የፖለቲካ አመራሩ ቁርጠኝነትና ጉልህ እርምጃ ውጤት ነው ያሉት ዳይሬክተሩ ‹‹እንደ አፍሪካዊ እንደ ኢትዮጵያዊነታችሁ በተገኘው ሽልማት ካልተደሰታችሁ ምን ያስደስታችሁ ይሆን? በማለት አዲስ አበባ አንጸባራቂዋ የአፍሪካ መዲና መሆኗን ገልጸዋል።

አዲስ አበባ ከተማ ይህን ታላቅ ዓለም አቀፍ ሽልማት ማሸነፍ የቻለችው ኒውዮርክን ከመሳሰሉ ታላላቅ ከተሞች ጋር በመወዳደር ነው ያሉት ሃስቲንግስ ቺኮኮ፤ በቀጣይም የጀመራችሁትን ስራ አጠናክራችሁ ልትቀጥሉበት ይገባል ሲሉ ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

---

## የሠላም ስምምነቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የአፍሪካን ችግር በአፍሪካውያን የሚለው ሃሳብ አሸናፊ ሆኗል። በዚህ ስምምነትም አፍሪካውያን ሙሉ ለሙሉ አቅም እንዳላቸው ያሳዩበት ነው። እንዲሁም የአድዋ ድል ያመጣውን ነጻነት ዳግም እያጣጣሙት ነው። በስምምነቱም ሁሉም ኢትዮጵያውያን አሸናፊ የሆኑበት ነው ብለዋል።

እንደ መምህሩ ማብራሪያ፤ ስምምነቱ ለአፍሪካ በሙሉ አዲስ ምዕራፍን የከፈተ ነው። አንዳንድ የውጭ አካላት ጥቁር ማሸነፍና ነጻነቱን ማረጋገጥ ይችላል ብለው ዳግም አድዋን እንዲያስቡ ተገደዋል። ከአገር ውጭና በአገር ውስጥ ያሉ ኢትዮጵያውያን ባደረጉት ጥረት ሁለተኛው የድህረ ቅኝ ግዛት በኢትዮጵያ ውስጥ ተሸንፏል። ወዳጅ አገራትና አፍሪካውያንም ከጎናችን ነበሩ።

ኢትዮጵያ የአፍሪካውያን ችግር በአፍሪካውያን ይፈታል የሚል የጸና አቋም አላት ያሉት አቶ እንዳለ፤ አንዳንድ ምዕራባውያን እያንዳንዱን ነገር መጠቀም የሚፈልጉት ከራሳቸው ጥቅም አንጻር በመሆኑ ኢትዮጵያ ጣልቃ እንዲገቡ አልፈቀደችም ብለዋል።

ምዕራባውያን በአንድ አገር ውስጥ ለሚነሱ ችግሮች መፍትሔ የማምጣት ችሎታ ቢኖራቸው በርካታ አገሮች አይፈርሱም ነበር። በሩሲያና በዩክሬን መካከል ችግር እንዳይፈጠር ማድረግ ይችሉ ነበር። ነገር ግን ፍላጎታቸው የራሳቸውን ጥቅም መቶ በመቶ ማረጋገጥ ብቻ በመሆኑ ማስማማት የሚል ጨዋታ መጫወት አይችሉም ሲሉም ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ላይ ከፍተኛ በደል ሲፈጸም ዝምታን የመረጡ አገሮች በኢትዮጵያ መንግስትና በሕወሓት መካከል ስምምነት እንዲመጣ ማድረግ አይችሉም ብለዋል።

እንደ አቶ እንዳለ ማብራሪያ፤ ሕብረቱንና አፍሪካውያንን ማሳነስ የቅኝ ግዛትና የድህረ ቅኝ ግዛት አንዱ አካሄድ ነው። ከፋፍሎ የመግዛት ፖሊሲን በመጠቀም ኢትዮጵያን የማፍረስና አንገት የማስደፋት ጥረት ቢያደርጉም አልተቻላቸውም። ከዚህ በኋላ በምዕራቡ አለም ያለው አማራጭ ከኢትዮጵያ ጋር ወዳጅ መሆን ብቻ ነው ሲሉም ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ ጣልቃ ገብነትን ለመከላከል ሕዝቡ የከፈለውን መስዋእትነት ሁሉም የአፍሪካ አገሮች መድገም እንዳለባቸውም አቶ እንዳለ አሳስበዋል።

---

## «ሕዝብን ሲያክም፣ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በማፍጠን ወደ ተግባር መለወጥ ያሻል ሲሉም ተናግረዋል።

ስለ ሰላም፣ ፍቅርና ይቅርታ የሚወራበት እንዲሁም ስምምነት ለተደረገበት ቀን እንኳን አደረሳችሁ ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ ከዚህ በኋላ ከግል ስሜታችን ወጥተን የማህበረሰብ ሰላምና እድገት የሚያመጡ ተግባራት ላይ ልናተኩር ይገባልም ሲሉ ገልጸዋል።

መንግስት የተቆጣጠራቸውን ከተሞች መልሶ የማልማት ተግባራትን በመከወን ላይ እንደሚገኝ የገለጹት ኡስታዝ አቡበከር፤ ወደ ሠላም ስምምነት ከተገባ ከመንግስትም ይሁን ከሕወሓት በኩል ወደ ትግበራው በመግባት ፊታቸውን ወደ መልሶ ግንባታ ማዞር አለባቸውም ብለዋል።

እንደ ኡስታዝ አቡበከር ንግግር፤ የእርስ በርስ ግንኙነትን ሰላማዊ ሊያደርግ የሚችል ትግበራና ወደ አፈፃጸም መሄድ ላይ በመፍጠን ህዝብ ለህዝብ ግንኙነትና ወንድማማችነትን የሚያጠናክር ስራ መስራት ያስፈልጋል።

ይህ የሠላም ስምምነት ከዚህ ቀን ቀድሞ ቢደረግ መልካም ነበር ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ አሁንም ቢሆን ከዚህ በኋላ በሃገራችን የጥይት ድምጽ እንዳይሰማ በጋራ መስራት ያስፈልጋል ብለዋል።

እንደ ኡስታዝ አቡበከር ገለጻ፤ እስከዛሬ መስማማት ባለመቻሉ ሀገር ወደፊት የምትሄድባቸውን አመታት ወደ ኋላ እንድትጓዝ ሆናለች፤ ዛሬ ላይ ስህተትን በመረዳት አይንን ወደ ሠላም አማራጭ ማዞር ትልቅ ነገር እንደሆነም ተናግረዋል።

ሠላም ሁልጊዜም አሸናፊ ነው ያሉት ኡስታዝ አቡበከር፤ በሁለቱ ወገን ያሉ ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም የማህበረሰቡ ክፍሎች አዲሱን የሠላሙን መንገድ በመጓዝ ከጥቁሩ ፋይል በመውጣት ሠላማዊ ወደ ሆነው ብርሀን መጓዝ እንደሚያሻም ገልጸዋል።

እስከዛሬ በማህበረሰብ አንቂዎችና ባለድርሻ አካላት ሠላም እንዲሰፍን በሀይማኖት አባቶችም ሆነ በሀገር ሽማግሌዎች በሚገባው ልክ ያልተሰራ ስራ አለ፤ አሁን ግን ስለ ሠላምና እርቁ የሚያብብበት ሂደት ላይ መንግስትን በማገዝ መሳተፍ እንደሚገባውም ነው የተናገሩት።

ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ሀገር ወደ አዲስ ምዕራፍ የምትሸጋገርበትን መንገድ በመምረጥ የግል ፍላጎትን ወደ ጎን ብሎ ሠላምን ብቻ መምረጥ እንደሚገባውም ኡስታዝ አቡበከር አመላክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሰላም፡- የኢትዮጵያ ብልጽግና አልፋና ኦሜጋ!

ዓለም የሁለት ተቃርኖዎች ስሪት ናት፤ ብርሃንና ጨለማ፣ ሰላምና ጦርነት፣ ፍቅርና ጥላቻ፣ ቂምና ይቅር ባይነት፣ ክፋትና ደግነት፣ ሞትና ሕይወት፣… በተቃርኖ ቆመው የሚሟገቱባት፤ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በሚል መንፈስ የሚገዳደሩባት፤ ሆኖም አንዱ ያለ አንዱ ህልውናቸው የማይገለጥባት ናት። የሰው ልጆችም የዚህችው ዓለም ባለቤት ሆነው የተፈጠሩ እንደመሆናቸው የእነዚሁ ተቃርኖዎች ተጋሪ ናቸው።

ይሁን እንጂ ከእነዚህ ተቃርኖዎች መካከል በተለይ ደግሞ በራሱ የሰው ልጅ የሚንጸባረቁና የሚዘወሩ እውነቶች አሉ። እነዚህ የራሱ የሰው ልጅ ባህሪና ተግባር መገለጫ የሆኑት የተቃርኖ ሁነቶች ደግሞ የሰው ልጅን በእጅጉ እየፈተኑት፤ ወደማይወጣው ችግርና መከራ እየከተቱት ይስተዋላሉ።

የሰው ልጅ በፍቅርና ጥላቻ፣ በጸብና ሰላም፣ በቂምና ይቅርታ፣… ተቃርኖዎች ውስጥ ራሱን ይገልጣል። በዚህም ፍቅር፣ ይቅርታ፣ ሰላምና አብሮነት የሰብዕናውን ልዕልና ከፍ አድርገው ሲገልጡ፤ በአንጻሩ ጥላቻ፣ ጸብ፣ ቂም፣ በቀልና መነጣጠልን የመሳሰሉት ደግሞ የሰብዕናውን መውረድ ከመግለጣቸውም ባሻገር ወደማይወጣው ምስቅልቅል ውስጥ የሚከቱት ስለመሆኑ ዛሬ ዓለማችን ያለችበትን ዘርፈ ብዙ ችግሮች መመልከቱ በቂ ነው።

የጸብ፣ የጦርነት፣ የጥላቻ፣ የቂምና በቀል መንገዶች በስሜት የመነዳትና የአስተውሎት መጋረድን ብቻ የሚፈልጉ የክፋት መንገድ ፍሬዎች እንደመሆናቸው፤ የሰው ልጆች የፖለቲካ ጉዞ በዘመናት ሂደት ውስጥ ከእነዚህ ችግሮች ሳይላቀቅ በዜጎች ላይ የማያባራ ጦርነትን ሲያስከትል ኖሯል።

በአንጻሩ ይሄንን የስሜት ግፊትና የማስተዋል ግርዶሻቸውን ገፍፈው ጉዞና መንገዳቸውን በፍቅር፣ በይቅርታ፣ በወንድማማችነት፣ በሰላምና ወንድማማችነት ቅኝት ውስጥ የመራመድ የሰብዕናን ልዕልና የተጎናጸፉ የአገራት የፖለቲካ ኃይሎች በሃገረ መንግስት ሂደታቸው ለዜጎቻቸው ከፍ ያለ ሁሉን አቀፍ ብልጽግናን አስገኝተዋል።

በዚህ መልኩ የሚታየው የሁለቱ ጽንፍ አካሄድ የመጨረሻው ውጤት በፖለቲከኛውና የፖለቲካ ጡዘት ፈጣሪውን ሳይሆን፤ በአገርና ዜጎች ላይ የሚገለጥ ነው። በዚህም የሰላምና ይቅርታ መንገድን የመረጡ ለዜጎቻቸው እፎይታን፤ ለአገራቸውም ብልጽግናን ሲያተርፉ፤ በአንጻሩ ቂምና በቀልን፣ ጥላቻና ፀብን ሲመርጡ ዜጎችን ለከፋ እንግልትና ሰቆቃ፤ አገርንም ከፍ ላለ ችግርና አለመረጋጋት ሲዳርጉት ታይተዋል።

በዚህ ረገድ አህጉረ አፍሪካ በተለይም ኢትዮጵያ የምትገኝበት የምስራቅ አፍሪካ ቀጣና መገለጫው ሆኖ የዘለቀው የፖለቲካ አለመረጋጋት፤ ቀጣናውን በየምክንያቱ ለሚከሰት ግጭት ሲዳርገው፤ አገራቱ የጦር አውድ፣ ዜጎቻቸውም የችግርና ሰቆቃ ተሸካሚ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል።

ኢትዮጵያም የዚህ ችግር አንዷ ተቋዳሽ ብቻ ሳይሆን፤ ሥርዓቶች በተለዋወጡ ቁጥር በሚፈጠር መፋተግ ውስጥ ዜጎቿ ለበዛ እልቂት፣ ስደትና እንግልት ሲዳረጉባት የኖሩባት ሃገር ናት።

የኢትዮጵያን የአብዮታዊ ለውጥ ጉዞ መግታትን ታሳቢ ያደረገው እና አገራዊ ለውጡን በሪፎርም ቅኝት ያስጓዘው የ2010 አገራዊ ለውጥም፤ ምንም እንኳን ከለውጡ ማግስት በትረ መንግስቱን የያዘው ኃይል አብዮትን በሪፎርም የመተካትና ደም አፋሳሽ አካሄድን ለማስቀም በብርቱ ቢለፋም፤ ጉዞና ሕልማቸው ሁሉ አብዮትና ደም አፋሳሽ የሆኑ ኃይሎች ይሄ ሊዋጥላቸው ባለመቻሉ አገር እንደ አገር፣ ኢትዮጵያውያንም እንደ ህዝብ ከፍ ያለ ዋጋ የከፈሉበት ጦርነት እንዲቀሰቀስ ሆኗል። በዚህም ኢትዮጵያ በርካታ ዜጎቿን በሞት ተነጥቃለች፤ በርካቶችም ለአካልና ስነልቦናዊ ጉዳት፤ በአስር ሚሊዮን የሚቆጠሩትም ለስደትና መፈናቀል ተዳርገውባታል። በመቶ ቢሊዮኖች የሚገመት ሃብትና ንብረት ለውድመት ተዳርጎባታል።

ይሄ ጦርነት አገርን ብቻ ሳይሆን ዜጎችን ዋጋ ያስከፈለ፤ በርካታ ወጣቶች የረገፉበት፤ ከህጻን እስከ አዋቂ ዘርና ፆታ ሳይለይ ለከፋ ሃዘንና ሰቆቃ የተዳረጉበት ነበር። በዚህ መልኩ ከፍ ያለ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ምስቅልቅሎሽን የፈጠረው ይሄ ጦርነት ታዲያ፤ ከሁለት ዓመታት በኋላ አሁን ላይ ዘላቂ ሰላምን ማምጣት በሚያስችል መልኩ የሰላም ስምምነት ላይ ተደርሷል።

ይሄ ይበል የሚያሰኝ መልካም ተግባር ሲሆን፤ ይሄ በሰነድ የሰፈረ ስምምነት ግን በተሳካ መልኩ እንዲጓዝ ማድረግ ከሁሉም የሚጠበቅ ሥራ መሆኑ ይታመናል። ሆኖም ሊዘነጋ የማይገባው ነገር ቢኖር፤ ይሄ የሰላም ስምምነት ከብዙ መስዋዕትነትና ውድ ዋጋ መክፈል በኋላ የመጣ መሆኑ ላይ ነው። ምክንያቱም የሁለቱን ዓመታት የመከራና መስዋዕትነት ዘመን ከፈጠረው ምስቅልቅል ባለፈ፤ ዜጎች ስለ ሰላምና አብሮነት ያላቸውን እረፍት የለሽ ምኞት በብዙ መልኩ የታየበት ነው።

በመሆኑም ሰላምን እውን በማድረግ ሂደቱ በሁለት ዓመቱ የተከፈለውን ዋጋ ማሰብ ይገባል ሲባል፤ በመከራ ውስጥ እንኳን ሆኖ ስለሰላምና አንድነቱ እንቅልፍ ያጣን ወገን ማሰብ ማለት ነው፤ በጦርነት ውስጥ በክፉ አሳቢና አድራጊዎች ግፍና መከራ የደረሰባቸውን አረጋውያን፣ ሴቶች፣ ህጻናት፣ መነኮሳት ዋይታና ሕመም ማሰብ ማለት ነው፤

ሃብት ንብረታቸውን ያጡ፣ ከሞቀ ጎጆና ንብረታቸው የተፈናቀሉ፣… ዜጎችን ማሰብ ማለት ነው፤ በጥቅሉ ይሄ ሁሉ ምስቅልቅል እንዳይደገም የጸና አቋም የመያዝን አቅም መሰነቅ ማለት ነው። ስለ ሕዝብና ሃገር ሲባል የራስና የቡድን ፍላጎትን መጨቆን ማለት ነው። ለሰላም ሂደቱ መሳካት የተከፈለውን ዋጋ ማሰቡ ተገቢ ነው የሚባለውም ለዚህ ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።**

## የሰላምን መንገድ ስንራመድ

ታምራት ተስፋዬ

ስለ ሰላም ብዙዎች ዘምረዋል። በርካቶች አዚመዋል። ጥቂት የማይባሉ ጽፈዋል። አያሌዎች ህይወታቸውን ሰውተዋል። ሚሊየኖችም ሰላምን ለመሻት ከአገር ከቄያቸው ተሰደዉ ተንከራተዋል። የሰውነትን ስብእና እና ክብር አጥተዋል።

ሰላም ሁሉ አቀፍ ተፈላጊነት አለው። ሁሉም በተግባር ይፈልገዋል። ይፈቅደዋል። የተለየ ዋጋ ይሰጠዋል። በሁሉም ባህሎችና እምነቶች እንዲሁም ሕዝቦች ዘንድ ሰላም ከፍተኛ ዋጋ አለው። ሰላምን የማያስተምር እምነትም የለም።

በየቤተ እምነቱ በሚደረጉ ፀሎቶችም ሰላም ከቀዳሚ ርዕሶች የመጀመሪያው ነው። ህዝብን እንደ የእምነቱ ፈጣሪን እለት እለት በሰላም ያሳደርከኝ በሰላም አውለኝ ከማለት አልፎ፤ ለአገሩ፣ ለህዝቡ ሰላም መሆን ይመኛል። ይፀልያል።

ዩናይትድ እስቴትስ ተወዳጅ ፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬገን፣ ‹‹ሠላም ማለት ግጭቶችን በሠላማዊ መንገድ መፍታት መቻል ማለት ነው›› ይላሉ። እርግጥም ሠላምን በጉልበት ማስጠበቅ አይቻልም። ሠላምን ማሳካት የሚቻለው በመግባባት ብቻ ነው። ልዩነትን ማቀራረብ ወይም ቅራኔን ማርገብ የሚቻለው በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ እንጂ፣ ‹‹የምፈልገውን አስፈጽማለሁ›› በሚል ጀብደኝነት አይደለም።

በተለይ በፖለቲካው ዓለም ፉክክርና የትግል ተሳትፎ ሁለንተናዊ ሰላም እውን ይሆን ዘንድ በተለይ ከአገርና ከሕዝብ በፊት ሥልጣንን ማስቀደም፣ ከራስ ክብርና ዝና በላይ ለሌላው አለመጨነቅና ዕብሪት አሸቀንጥሮ ማስወገድ የግድ ይላል።

ሰላም የሚረጋገጠው በሠለጠነ አስተሳሰብ እንጂ ዘመን ባለፈበት አስተሳሰብና በጠመንጃ አምላኪነት አይደለም። ለአገር የሚበጅ ሥርዓት ዕውን ሊሆን የሚችለው በሕዝብ ይሁንታ እንጂ በጀብደኝነት አይደለም። ሆኖም አያውቅም። በኋላ ቀር አስተሳሰብ ተቸክሎ ጠመንጃ መወልወልም ሆነ ውረድ እንውረድ ተባብሎ ጦር መስበቅ፣ በየትኛውም መመዘኛ በጣም የሚያስንቅ አስነዋሪ ድርጊት ነው።

ሰላምን በጉልበት የማምጣት ሙከራዎችም በአብዛኛው ትርፋቸው መከራ ነው። በጉልበትና በጠመንጃ የሚጠበቅ ሰላም ቀኝ ጠብቆ ፍርክርኩ መውጣቱ አይቀሬ ነው። አንዳንድ ፀሃፍት እንዳውም በጉልበት የተገኘ ድል ከሽንፈት እኩል ያነፃፅሩታል። ምክንያታችን የሚሉት ደግሞ ጊዜያዊ መፍትሄ መሆኑን ነው።

ኢትዮጵያ ታሪክ አንድ ችግር ሲያጋጥና ሰላም ሲደፈርስ ተነጋግሮ መፍትሔ ለማፍለቅ ከመትጋት ይልቅ ዱላ መምዘዝ የተለመደ ነው። በዚህም ምክንያት ግጭትን ወይም ጦርነትን ሙጥኝ በማለት ዓላማን ለማስፈጸም ጥድፊያው ሲበረታም ይታያል።

ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት ዓመታት ጦርነት ባስከተለው ሁለንተናዊ ቀውስ ከባድ መንገራገጮችን ውስጥ ቆይታለች። በውጫዊም ሆነ በውስጣዊ ምክንያቶች የሰላም አየር ናፍቆት ቆይታል። ችግሩ እንዳይከሰት ብዙ የሰላም አማራጮች ተሞክረዋል፤ ሳይሳኩ ቀርተው ጦርነት ውስጠይ ገብተን ቆይተናል።

በጦርነቱ ምክንያት በሺዎች የሚቆጠሩ ሞተዋል። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩት ደግሞ ከአካላዊና ከሥነ ልቦናዊ ጉዳት በተጨማሪ ተፈናቅለው ሜዳ ላይ ወድቀዋል። ግምቱ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የህዝብ እና አገር ሀብት ወድሟል።

የሰሜን ጦርነት ከተጀመረ ጊዜ አንስቶ ባለፉት ሁለት ዓመታት ጦርነቱ ኢኮኖሚውን እያደቀቀ የዜጎችን ኑሮ ከማክፋቱና የሚሊዮኖችን ደኅንነት ከማቃወሱም በላይ ኢትዮጵያ ብዙ ሴራ ተሸርቦባታል። በርካታ መሰናክሎች አሳልፋለችል። ተወንጅላለች። በተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ሚዲያዎች ሆን ተብሎ ገጽታዋ እንዲጠቁር ተደርጓል። ተስፋ ቢስ እንደሆነች ተደርጋም ተስላለች።

በመጨረሻው አሁን ችግሩ በሰላም ስምምነት መስመር መያዥ እየጀመረ ነው። ከቀናት በፊትም በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ሥር በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ከተማ በፌዴራል መንግሥትና በ ሕወሓት መካከል የሰላም ንግግር እውን ሆናል። የኢትዮጵያን ጥቅምና ክብር ባስጠበቀ መልኩ ሰላምን እውን ለማድረግ ከስምምነት ተደርሷል።

ይህም የሰላም መንገድ ለኢትዮጵያ ትልቅ ድል ነው። በሰላም እንጂ በጦርነት ያተረፈ አገር አለመኖሩን በመረዳት ግጭትና ጦርነት ይብቃን መባሉ እጅግ የሚደገፍና የሚያስደስት ነው። ከምንም በላይ ለህዝባችን ትልቅ እፎይታ ነው።

በሠለጠነ መንገድ ሰላም መንገድ ማራመድም ትሩፋቱ በርካታ ነው። በተለይ ኢትዮጵያ የታሪካዊ ጠላቶቿ መቀለጃና መፈንጫ እንዳትሆን ያደርጋል። በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ እጃቸውን አስረዝመው እያስገቡ ያሉ የውጭ ኃይሎች ፍላጎት እንዳይሳካ ግዙፍ ሚና ይጫወታል።

በዚህ የሰላም መንገድ ኢትዮጵያን ጨምሮ የአፍሪካ አገሮች ከምእራባውያን ይልቅ በራሳቸው አቅም ያለማንም ጣልቃ ገብነት ከቅኝ ግዛት እሳቤ ተላቀው የራሳቸውን ችግር በራስ መፍታት እንደሚችሉ በተጨባጭ ማመላከት ተችላል።

ሰላም በመገኘቱ የሚከስር ህዝብም ሆነ የህዝብ አጀንዳ የለም። ይሑንና ከሰላም ይልቅ ጦርነት ምርጫቸውና የደስታቸው ምንጭ የሆነ አንዳንዶች መኖራቸው የሚደበቅ አይደለም። ትናንት ‹‹የትግራይ ሕዝብ መንገድ ተዘጋበት፣ የእርዳታ እህል እየደረሰው አይደለም፣ ስልክ፣ መብራት፣ ወዘተ ወዘተ ተከለከለ። በከበባ ውስጥ ሆኖ ዘሩ ሊጠፋ ነው›› ሲሉ የነበሩ ሰዎች ዛሬ ጦርነቱ ለምን ቆመ ብለው ነጠላ ዘቅዝቀው፣ ደረት እየደቁ ናቸው።

በኢትዮጵያ ምድር የሰላም አየር መንፈስ እንዲቀጥል ታዲያ መሰል የሰላም መንገድ ለመዝጋት የሚታትሩ እና እንደ ጎልያድ መንገድ የሚዘጉን አይቶ እናዳላየ ሰምቶ እንዳልሰማ በጥንቃቄ ማለፍ ከፍ ሲልም ገሸሽ ማድረግ የግድ ይላል።

በኢትዮጵያ ምድር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የጦርነት ምዕራፍ ተዘግቶ ሰላም እንዲሰፍን፣ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከዳር እስከ ዳር በአንድነት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። የአገር ጉዳይ ያገባናል የሚሉ ወገኖች በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ ተቀራርበው መነጋገር ይጠበቅባቸዋል።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎችም ሆኑ ሌሎች የአገር ጉዳይ የሚመለከታቸው ወገኖች፣ ኢትዮጵያ ከግጭት የፀዳች አገር እንድትሆን ቁርጠኝነታቸውን በተግባር ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ ስኬት ደግሞ ብሔራዊ ምክክር አስፈላጊ ነው። ጦርነቱ ሲጠናቀቅ ኢትዮጵያ ዳግም ወደ ጦርነት እንዳትመለስ ተደርጎ መሆን ይኖርበታል።

አንድ መታወቅ ያለበት አብይ ጉዳይ የሰላም ሽግግር ስክነትና ብስለት ይፈልጋል። ከቂምና በቀል በመፅዳት ይጠይቃል። የሰላምን መንገድ ስንራመድም ይሕ መፈክራችን ሊሆን የግድ ይላል። ኢትጵያ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች እድገት ለማስመዝገብ መጀመሪያ ሊኖራት የሚገባው ሃብት ሰላም ነው።

የሰላም ዋጋው የይቅርታ ብቻ በመሆኑ በይቅርታ ላይ የተመሰረተ የሰላም ባህል ማበልጸግ ይገባናል። ጦርነት ብዙ አውዳሚ እንደመሆኑ በዚህ ጦርነት የተጎዱትን የሶልሶ ማቋቋም እና መደገፍ የመንግስት ኃላፊነት ብቻ ሳይሆን የሁላችንንም ርብርብ ሊሆን የግድ ይላል።

የሰላምን መንድ ስንራመድ ሰላም እውን እንዳይሆን የኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች የተዳፈነው እሳት እሳቱን ለማራገብ አድፍጠው እንደሚተጉም ለአፍታ መዘንጋት የለበትም። በሰላም ንግግሩ የሚፈለገው ውጤት ላይ ቢደርስምም እንኳን ምዕራባውያኑ በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርጉትን ዲፕሎማሲያዊና ፖለቲካዊ ጫና ይቆማል ብሎ ማሰብም አይቻልም። ይሕ እንደመሆኑም አንድነታችንን ይበልጥ ሊጠናከር ይገባል።

እንደ አገር የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ተቀብሎ ለአፈጻጸሙ በአግባቡ ሊዘጋጅና ስለ ሰላም ሃያልነት መንገር ቋሚ መልዕክቱ ሊሆን ይገባል። በዚህ ሂደት በአንድ አፍ ስለሰላም እየዘመሩ በሌላ አፍ ጦርነትን የሚደግፉ የፖለቲካ ተዋንያንም ሆኑ አክቲቪስቶች፣ የሰላም መንገዱ እንዲዘጋና ጦርነቱ እንዲያገረሽ ከሚያደርጉ ፕሮፓጋንዳዎች እንዲታቀቡ ማድረግ የግድ ይላል።

ሰላምን መንገድ በመራመድ ጠላትን በጋራ በመመከት የምናስመዘግባቸው ድሎች በሌሎች ዘርፎችም ሊደገሙ ይገባል። ይህን ማድረግ ኢትዮጵያ በእድገት ጐዳና ላይ ያራምዳል። የተሻለች አገር ለቀጣዩ ትውልድ እንድናስረክብ ያግዛል።

# ፋሽን

## አካል ጉዳተኞችና ፋሽን

**ቦጋስ አበበ**

አካል ጉዳተኞች በህብረተሰቡ ዘንድ በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካው፣ በማህበራዊ እና በሌሎችም አስተዋጽኦ እያበረከቱ ቢገኙም ካለባቸው አካላዊ እክል የተነሳ ያሉባቸው ችግሮች አሁንም አልተቀረፉም፡፡ ለዚህም በዋነኛነት እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው በህብረተሰቡ ዘንድ ስለአካል ጉዳተኞች ያለው የተሳሳተ አመለካከት ነው።

በተጨማሪም፣ በብዙ የስራ መስኮች ምቹ ሁኔታ ስላልተፈጠረላቸው አካል ጉዳተኝነት የመገለል እጣ ያጋጥማቸዋል። ይህ ችግር ከሚታይባቸው መስኮች አንዱ የፋሽን ሙያው ነው። ብዙ ጊዜ አካል ጉዳተኞች ተሰማርተውበት የማይታይ ዘርፍ ቢኖር ፋሽን በቀዳሚነት ይጠቀሳል። በተለይም በኢትዮጵያ በርካቶች ስለ ፋሽንና ውበት ሲያስቡ አካል ጉዳተኞችን ማሰብ እንደሚከብዳቸው መካድ አይቻልም።

በኢትዮጵያ ፋሽንና ፋሽን ነክ የሆኑ ኢንደስትሪዎች አካል ጉዳተኞችን ያማከሉ ናቸው ብሎ ለመናገር የሚያስደፍር ሁኔታም የለም። በእርግጥ ፋሽኑ ዘርፍ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ማኅበራዊ ክንውኖችም እውን አካል ጉዳተኞችን ያማክላሉ? የሚለው ጉዳይ ያጠያይቃል፡፡

ከፋሽን ትርዒቶች ጀምሮ ፋሽን የሚባሉ እንደ አልባሳትና ሌሎችም ሲዘጋጁና ለገበያ ሲቀርቡ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ አድርገው አይደለም፡፡ የልብስ ዲዛይን፣ የሞዴሊንግና ሌሎችም የፋሽን ዘርፎች አካል ጉዳተኞችን የዘነጉ መሆናቸው ለዚህ አንድ ማሳያ ነው።

ዘርፉ አካል ጉዳተኞችን ከማግለሉ ባሻገር አብዛኛው ማኅበረሰብ ውስጥ ውብ ወይም ቆንጆ የሚባል ሰው የሚገለጽበት መንገድ በራሱ አካል ጉዳተኞችን ያማከለ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ‹‹ቀጠን ረዘም ያለች ሴት ወይም ደንደን ያለ ወንድ›› የሚለው ተለምዷዊ የተዛባ የውበት አገላለጽ ቁንጅናን በአንዳች መንገድ ብቻ የሚገድብ ሲሆን፣ የሰው ልጆች ባጠቃላይ እንደየአፈጣጠራቸው ውብ መሆናቸውን የዘነጋም ነው፡፡



**አካል ጉዳተኞች የዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አካታች የፋሽን ትርኢቶች መጠናከር አለባቸው**

በሌሎች ዓለማት በዊልቸር ወይም በክራንች ድጋፍ የሚሄዱ ሞዴሎችን መመልከት እየተለመደ መጥቷል፡፡ መስማት የተሳናቸው፣ ዓይነ ሥውራንና ሌሎችም አካል ጉዳተኞች የፋሽኑን ዘርፍ በስፋት ሲቀላቀሉ ይስተዋላል። ለአካል ጉዳተኞች ምቹ የሆኑ አልባሳት የሚያዘጋጁ ዲዛይነሮችም እየተበራከቱ ነው፡፡ በአንድ ወቅት ኒውዮርክ ታይምስ በፋሽን ኤንድ ስታይል አምዱ ‹‹በአንድ ወቅት ፋሽን ገንዘብ ያላቸው፣ ተክለ ቁመናቸው ‹‹ያማረ›› የሚባሉ ሰዎች ብቻ እንደሆነ ይታሰብ ነበር፡፡ አሁን ግን ፋሽን የሁሉም መሆኑን የማሳየት አብዮቱ ተጧጡፏል፤›› በማለት ስለጉዳዩ ሰፋ ያለ ዘገባ አስነብቧል። ዘገባው በዋነኛነት ያተኮረውም ለአካል ጉዳተኞች ተብለው ዲዛይን በሚደረጉ አልባሳትና በአካል ጉዳተኛ ሞዴሎች ዙሪያ ነበር፡፡

አንድ ብራዚላዊ ዲዛይነር ለአካል ጉዳተኞች ያዘጋጃቸው ልብሶችን ሲያስተዋውቅ፣ አካል ጉዳተኞች ምቹ ልብስ ለማግኘት ስለሚያዩት ውጣ ውረድ ገልጾ ነበር፡፡ አልባሳቱ በአካል ጉዳተኛ ሞዴሎች ተለብሰው እንዲታዩ አድርጎም ነበር፡፡ በዓለም ዕውቅናን እያተረፉ ከመጡ አካል ጉዳተኛ ሞዴሎች አንዷ ካናዳዊቷ ዊኒ ሀርሎ በቆዳ ሕመም ትሰቃያለች፡፡ በልጅነቷ በቆዳዋ ሁኔታ ምክንያት የዕድሜ እኩዮቿ ‹‹የሜዳ አህያ›› እያሉ ይቀልዱባት ነበር፡፡ ዛሬ የፋሽን ዘርፉን አካሄድ በተለየ ሁኔታ እየቀየሩ ካሉ ወጣት ሞዴሎች አንዷ ዊኒ ሀርሎ መሆኗ ይታወቃል።

በኢትዮጵያም አንዳንድ አካል ጉዳተኞች ዊኒ ሀርሎን ተከትለው በዘርፉ ብቅ ለማለት የሞከሩበት ጊዜ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ። ነገር ግን ብዙም ጎልተው ሳይወጡ ውጥናቸውም ረጅም ተጉዞ ተጽእኖ ሲያሳድር አይስተዋልም። አሁንም ቢሆን ውበት የሚተረጎምበትን መንገድ የሚቀይሩ፣ በሁሉም ሰው ውበት እንዳለ የሚያሳዩ አካል ጉዳተኛ ሞዴሎች ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳሉ ይታመናል። መሠረታዊ ነገሮች ባልተሟሉበት ሁኔታ ስለ ፋሽን ማሰባቸው ከባድ ቢሆንም የሚደግፋቸው አካል ሊኖር እንደሚገባ ግልጽ ነው።

በኢትዮጵያ ለአካል ጉዳተኞች ምቹ ልብስ በማምረትም ይሁን በዲዛይንና ሞዴሊንግ አካል ጉዳተኞችን የማሳተፍ እንቅስቃሴው እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ከጊዜ ወደ ጊዜ ግን ለውጥ ሊኖር እንደሚችል ባለሙያዎች እምነት አላቸው።

ለዚህ ደግሞ አካል ጉዳተኞችን ያማከለ የፋሽን ትርዒት መዘጋጀቱ አንድ ዕርምጃ ሊሆን እንደሚችል ይታመናል። በዚህ ረገድ የኢትዮጵያ የፋሽን ዲዛይነሮች ማኅበር ከዓመታት በፊት የጀመረው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል። በዚህም ለአካል ጉዳተኞች የሚሆን ልብስ በብዛት አዘጋጅቶ ለገበያ የማቅረብ እድል ይፈጠራል። አካል ጉዳተኞች ገበያ ሲወጡ ምቹ ልብስ እንዲያገኙ ከትርዒቶች በኋላም ሌሎች ልብሶች ዲዛይን ሲደረጉ አካታች እንዲሆኑ ያግዛል። አልባሳት ዲዛይን ሲደረጉ የተጠቃሚውን ምቾትና አቅም ያገናዘቡ መሆናቸው ቅድሚያ ይሰጠዋልና አካታችነቱ እንዲቀጥልም እድል ይሰጣል። ዲዛይነሮቹ ለትርዒቱ አልባሳት ሲያዘጋጁ አካል ጉዳተኞች ምን እንደሚያስፈልጋቸው በመጠየቅና እርስ በርስ በመወያየትም ተሞክሮውን ማስፋት እንደሚችሉ የዘርፉ ባለሙያዎች እምነት እንዳላቸው ይገልጻሉ።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ትራማዶል እና ውሳኔው

**አቤል ገ/ኪዳን**

ሰሞኑን የኢትዮጵያ ምግብና መድሀኒት ባለስልጣን ትራማዶል የሚባለው መድሀኒት ያለ ሀኪም ፈቃድ እንዳይሸጥ ውሳኔ ማስተላለፉን በመግለጫ ተናግሯል። ይሄ መድሀኒት እስከዛሬ እንደ አንዳንድ ቀላል መድሀኒቶች እንዲሁ ያለ ሀኪም ትእዛዝ ተጠቃሚው የፋርማሲ ባለሙያውን በማማከር ብቻ ይገዛ የነበረ ሲሆን ከአሁን በኋላ ግን የሀኪም ትእዛዝ ከሌለ እንዳይሸጥ ተብሏል። ምክንያቱ ደግሞ ብዙ ወጣቶች በዚህ መድሀኒት ሱስ እየተያዙ በመሆናቸው ነው። ትራማዶልን ከጤና ባለሙያ ትዕዛዝ ውጭ ያለ ማዘዣ መውሰድ ወይም ከታዘዘ ጥንካሬ እና መጠን በላይ ብዙ ጊዜ መውሰድ ወይም ከታዘዘ ጊዜ ገደብ ውጭ ለረጅም ጊዜ መውሰድ ለሱሰኝነት ያጋልጣል። ሰውነት ደግሞ አንዴ ይህን መድሀኒት ከለመደ አሁንም አሁንም አምጡ ይላል። እና ችግሩ ምንድን ነው ካላችሁ መድሀኒቱ የህመም ማስታገሻ በመሆኑ ለጊዜው ለተወሰነ ሰዓት ለተጠቃሚው ዘና የማድረግ ጥቅም ቢኖረውም በዘለቄታው ግን የምግብ ፍላጎት ማጣት፤ ከፍተኛ የራስ ምታት፤ የሰውነት ላብ፤ እረፍት ማጣት፤ እንቅልፍ ማጣት፤ ድካም ስሜት፤ ማስመለስ ሊያመጣ የሚችል መሆኑ ብሎም በተለይ መድኃኒቱን መውሰድ ለማቆም የሚያስቸግር መሆኑ ነው። ከጤና አንጻር ሊከሰት ከሚችለው ጉዳት ባለፈ የማህበራዊ ህይወት ቀውስና ለተለያዩ ወንጀሎች ተጋላጭ መሆን፤ ለድህነት እና ለስነ ልቡና ቀውስም ያጋልጣል።

ሰሞኑን ዶ/ር ናሆም ግሩም የሚባል አንድ የህክምና ባለሙያ በዚህ ዙሪያ የገጠመውን ነገር በማህበራዊ ሚዲያ እንደሚከተለው አካፍሎን ነበር። ዶክተሩ እንዲህ ይላል “ከቀናት በፊት አንድ እድሜዋ በአስራዎቹ መገባደጃ አከባቢ የሚገኝ ታካሚዬ ለመጣችበት ህመም መፍትሄ ይሆናል ብዬ ያሰብኩትን መድሃኒት ሰጥቼያት ተሰናብታኝ ልትወጣ ስትል “አንድ ነገር ላማክርህ ነው እባክህ እርዳኝ” እያለች ማልቀስ ጀመረች። ጉዳዩን በአንዴ ለማስረዳት ፍቃደኛ ባትሆንም ከስንት ግዜ ውትወታ በኋላ ችግሯን ነገረችኝ።

ትራማዶል የሚባል መድኃኒት በቀን ብዙ ፍሬ እንደምትወስድ እና አሁን እሱም አልበቃ ብሏት በመርፌ ሚወጋ መውሰድ መጀመሯን፣ ይሄን መድሃኒት እሷ ብቻ ሳትሆን ብዙ ጓደኞቿ እንደሚወስዱት እና ትምህርት ቤት ውስጥ ጭምር ታዋቂ መሆኑን ጭምር አጫወተችኝ። “መድኀኒት ቤቶች ብር ከተሰጣቸው ያለ ጤና ባለሙያ ትዕዛዝ ይሸጣሉ። አንዳንዶቹ ገና ሲያዩን ምን ፈልገን እንደመጣን ያውቃሉ” አለች።

ከዚ በፊት አንድ መኪና ማጠቢያ ቦታ ማውቀው ልጅ መኪና ውስጥ የስራ ቦታ መታወቂያዬን አይቶ ሀኪም መሆኔን ካወቀ በኋላ “እባክህ በጣም ስላመመኝ (Tramado) ሚባል መድኃኒት በርከት አርገህ እዘዝልኝ” ብሎኝ ያውቃል። በኋላ በደንብ ቀርቤው ስጠይቀው መውሰድ ከጀመረ 2 ዓመት እንደሞላው እና ያለሱ ስራውን መስራት እንደማይችል አጫወተኝ። ማገገሚያ ቤት ያሉ ታካሚዎች ህክምና ቦታ ከመጡ ብዙዎቹ ለባለሙያው “ትራማዶል ካልሆነ ሌላ መድሃኒት አያሸለኝም” ሲሉ ብዙ ግዜ ገጥሞኝ ያውቃል። የሌሎቹን ታሪክ ቤት ይቁጠረው!”

እንግዲህ ዶክተር ናሆም እንደነገረን መድሀኒቱ ብዙ ወጣቶችን ከጥቅም ውጭ እያደረገ ነው። በዚህም የተነሳ አሁን መንግስት የወሰደው እርምጃ ትክክለኛ ሊባል የሚችል ነው። ነገር ግን ከዚህ ውሳኔ በኋላ ቀጥሎ የሚመጣ አዲስ ጥያቄ ይኖራል። እሱም፤ በዚህ ሱስ ውስጥ ያሉ ወጣቶች ቀጥሎ እጣ ፈንታቸው ምን ይሆናል? ትራማዶል ስለተከለከለ በአንዴ መጠቀም ያቆማሉ? ካላቆሙስ ወደ ሌሎች አደንዛዥ እና አነቃቂ እጾች ተጠቃሚነት ሊሻገሩ አይችሉም? እንዲህ አይነት ነገርን ለመከላከል ምን መላ ተዘይዷል? እና መሰል ጥያቄዎች ይቀጥላሉ።

እንግዲህ ሁላችንም እንደምናውቀው ሱስ ውቃቢ አይደለም በአንዴ ነቅሎ አይጠፋም። ስለዚህም ትራማዶል ተጠቃሚዎች ትራማዶልን እንደ በፊቱ በቀላሉ ማግኘት ሲያቅታቸው ወደ ሌሎች ሱሶች ይዞራሉ። ይህም ማለት የትራማዶል ገበያ ተዘግቶ የእነ ካናቢስ እና ኮኬይን ገበያ ይጦፋል ማለት ነው። በሱስ ዓለም ሁሌም እንደሚታወቀው ሱሰኛ ከአንድ ሱስ ወደ ባሰው ሱስ ይሄዳል እንጂ ወደኋላ አይመለስም። ተጠቃሚው ትራማዶልን ሲከለከል ከትራማዶል የባሰ መድሀኒት ፍለጋ መውጣቱ አይቀርም። ስለዚህም ስንወስን ውሳኔያችን ልክ እንደ ትራማዶል ጊዜያዊ እፎይታን የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን ዘላቂ መፍትሄን የሚያመጣ መሆን አለበት።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሊታወቅ የሚገባው ነገር ሱስ በህግ ሊቆም የማይችል እንደሆነ ነው። ሱስ የሚቆመው በሳይንሳዊ መንገድ ብቻ ነው። ሳይንሳዊው መንገድ ደግሞ ማገገሚያ ማእከላትን በማቋቋም፤ ባለሙያዎችን በማፍራት፤ ከመንፈሳዊ ተቋማት ጋር ተናብቦ በመስራት፤ የአደንዛዥ እጽ አከፋፋዮችን በመቆጣጠር እና ተጠያቂ በማድረግ፤ እና መሰል መንገዶች ነው መፍትሄ የሚመጣው። በሌላ መልኩ አገራችን በአሁኑ ወቅት ህገወጥ ንግድ፤ የገበያ ሳቦታጅ እና ሌሎችም ውንብድናዎች የተስፋፉባት በመሆኗ ሀሰተኛ የሀኪም ማዘዣ የሚያድሉ፤ ከሙያ ስነ ምግባር ውጭ ማዘዣ የሚጽፉ፤ ያለ ማዘዣ የሚሸጡ አልፎም በህገወጥ መልኩ መድሀኒቱን አምጥተው የሚያከፋፍሉ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ገምቶ መንቀሳቀስ አስፈላጊ ነው።

በመጨረሻም መንግስት እንዲህ አይነት ውሳኔዎችን ለመወሰን ጉዳዩ በሶሻል ሚዲያ እስኪነሳ ድረስ መጠበቅ የለበትም። ይህ ችግር ለረዥም ጊዜ የከረመ እና ሲወራበት የኖረ ነው። ነገር ግን የሚመለከተው መስሪያ ቤት እርምጃ የወሰደው ጉዳዩ ሰሞኑን እንደ አዲስ በማህበራዊ ሚዲያ ሲራገብ ነው ማለት ይቻላል። ይህ ትክክለኛ አሰራር አይመስልም። መስሪያ ቤቱ የዚህ መድሀኒት ፍላጎት በየጊዜው እያሻቀበ ሲመጣ ችግር እንዳለ መገንዘብ ነበረበት። አሁን ላይ ውሳኔውን የወሰነው በዚህ የፍላጎት መረጃ ላይ ተመርኩዞ ከሆነ እሰየው ነው። ካልሆነ እና በሶሻል ሚዲያ ጫና ውስጥ ሆኖ ከሆነ የወሰነው ግን ለከርሞው መታረም አለበት።

ቸር እንሰንብት!

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

# የፀረ-አፓርታይድ ትግል አጋር ኢትዮጵያዊው/ አፍሪካዊው ጄኔራል

**ዲያቆን ተፈሪ ወርቁ**

ባሳለፍነው ሳምንት በኢትዮጵያዊው ጀግና፣ በጄኔራል ታደሰ ብሩ የሕይወት ታሪክ ላይ ያጠነጠነ መጽሐፍ በዙፋን ኡርጋ ተጽፎ ለምርቃት በቅቷል። ታሪካችንን ሙሉዕ ለማድረግና የዛሬውና የነገው ትውልድ በጀግኖች አባቶቹና እናቶቹ የጀግንነት ገድል ብሔራዊ ኩራት እንዲኖረው ለማድረግ እንዲህ ዓይነቶቹ መጻሕፍት መታተም ፋይዳቸው ትልቅ ነውና ይበል የሚያሰኝ ነው። በዛሬው ጽሑፌም ከጄ/ል ታደሰ ብሩ የሕይወት ታሪክ ጋር በተያያዘ ሁለት ገጠመኞቼን በማስቀደም ጥቂት ነገሮችን ለማንሳት ወደድኹ።

ጀግናው ጄኔራል ታደሰ ብሩ የኦሮሞ ምድር ያፈራቸው ጀግና ኢትዮጵያዊ ሲሆኑ፤ ጀግንነታቸው ከኢትዮጵያ ምድር አልፎ በአኅጉረ አፍሪካ ጭምር ከፍ ያለ ነው። ስለ እኚህ ከፍተኛ ወታደራዊ መኮንን ጀግንነትና ደቡብ አፍሪካ ድረስ ስለተሻገረው ዝናቸው ያወቅኩባቸው ሁለት አጋጣሚዎች ነበሩ። የመጀመሪያው በደቡብ አፍሪካ፣ በዌስተርን ኬፕ ዩኒቨርሲቲ ትምህርቴን በምከታተልበት ወቅት በሆነ አንድ አጋጣሚ ነበር።

አጋጣሚው ይህን ይመስላል። በምማርበት በዌስተርን ኬፕ ዩኒቨርሲቲ፣ የሮቢን ሙዚየም የማይቡዬ ቤተ-መዛግብት/አርካይቭ ክፍል ኃላፊ፣ የመዛግብት ጥናት መምህራችን የሆነች ደቡብ አፍሪካዊት ፕሮፌሰር ሴት- በአንድ ወቅት በዩኒቨርሲቲው አርካይቭ ካለው የፎቶ ስብስቦች ውስጥ ሁለት ፎቶችን አምጥታ አሳየችኝ። ፎቶዎችን እያቀበለችኝ፤ ‘‘ከነጻነት ታጋያችን፣ ከታታ ማዲባ/ኔልሰን ሮሂላላ ማንዴላ ጋር አብረው የተነሱትን እኚህን ኢትዮጵያዊ፣ ጀግና የጦር መኮንን ታውቃቸው ይሆን?!’’ ስትል ጠየቀችኝ።

እኔም ፎቶውን በኢትዮጵያዊ የጀግንነት ኩራት ትኩር ብዬ እያየሁ… አዎን አውቃቸዋለሁ! ኔልሰን ማንዴላ ያሰለጠኑትና በወቅቱ የኮልፌ ፈጥኖ ደራሽ ማሰልጠኛ አዛዥ የነበሩት ጄኔራል ታደሰ ብሩ ናቸው። አልኳት። ‘‘አ! ትክክል ነህ፤ ይገርማል እነዚህን ፎቶዎች ያሳየኋቸው አብዛኛዎቹ ኢትዮጵያውን ተማሪዎች አያውቋቸውም። እነዚህ ፎቶዎች በቤተ-መዛግብታችን/በአርካይቫችን ውስጥ ለብዙ ጊዜ ቆይተዋል። እዚህ ዩኒቨርሲቲ በስኮላር ሺፕ ለሚመጡ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ሁሉ፤

‘‘እናንተ ኢትዮጵያውያን ለእኛ ለደቡብ አፍሪካውያን ከዘረኛው አፓርታይድ አገዛዝ ነጻ እንድንወጣ ላደረጋችሁት አስተዋጽኦ ባለውለታዎቻችን ናችሁና ሁሌም አመስጋኞቻችሁ ነን በማለት ይህን ታሪካዊ ፎቶዎች እያሳየኋቸው በኩራት እነግራቸዋለሁ።’’ አለችኝ።

በርግጥም፤ የነፃነት አርበኛ፣ የሰላም አባት፣ የይቅር ባይነት ተምሳሌት፣ የአይበገሬነት የፅኑ መንፈስ ባለቤት፣ የመለያየትንና የዘረኝነትን ፅኑ ግንብ በወንድማማችነት መንፈስ ያፈረሱ፣ የጠላትነትን ክፉ የጥላቻ ዘር በፍቅር ያመከኑ፣ በሰላምና እርቅ ጥሪያቸው ለበቀል የተመዘዙ የጥፋት ሰይፎችን ወደ ሰገባቸው እንዲመለሱ ያደረጉ፣ የሰው ልጆች ሁሉ አንድነት፣ የሰብአዊነት ክብር ምልክት በመባል የሚታወቁት- ታታ ማዲባ/ኔልሰን ማንዴላ- የነፃነት ትግል ሕይወት ውስጥ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ያለን ስፍራ በእጅጉ የተለየና ታላቅ ነው። የዚህ ታሪክ ተጋሪና የፀረ-አፓርታይድ ትግሉ አጋር ከሆኑ ኢትዮጵያኖች መካከል ደግሞ ኢትዮጵያዊው ጄ/ል ታደሰ ብሩ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱ ናቸው።

ይህን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በልባቸው ውስጥ ያላቸውን ታላቅ ስፍራና ክብር በተመለከተ፤ ራሳቸው ማንዴላ በፃፉት ***‘‘Long Walk to Freedom’’*** በሚለው መጽሐፋቸው ውስጥ እንዲህ በማለት ነበር የገለጹት፡-



***‘‘Ethiopia has always held a special place in my own imagination and the prospect of visiting Ethiopia attracted me more strongly than a trip to France, England and America combined. I felt I would be visiting my own genesis, unearthing the roots of what made me African.’’***

ሌላኛው ጄ/ል ታደሰ ብሩን በይበልጥ ታሪካቸውን እንዳውቅ ያደረገኝ አጋጣሚ ደግሞ ይህን ይመስላል። ከጥቂት ዓመታት በፊት የደቡብ አፍሪካው- የአፍሪካ ናሽናል ኮንግረስ ፓርቲ/ኤ.ኤን.ሲ መቶኛ ዓመቱን ለማክበር ሲዘጋጅ- የደቡብ አፍሪካ መንግሥት በኤ.ኤን.ሲ ፓርቲ እና በኔልሰን ማንዴላና የትግል ጓዶቹ የፀረ-አፓርታድ ትግል ዙሪያ የሚያጠነጥን ዶክመንተሪ ፊልም ለመሥራት የደቡብ አፍሪካ DV8 እና የእንግሊዝ ቢር ኸርት ሊሚትድ የተባሉ የፊልም ካምፓኒዎች የተጣመሩበት ቡድን ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ነበር።

ይህ ዶክመንተሪ ፊልም ዋናው ዐፅመ-ታሪኩ የሚያጠንጥነው ኔልሰን ማንዴላ ለወታደራዊና ለፖለቲካዊ ስልጠና ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ወደ አገራቸው በሚመለሱበት ወቅት በአሰልጣኛቸው በጄ/ል ታደሰ ብሩ በተበረከተላቸው ቡልጋሪያ ሠራሽ ማካሮቭ ሽጉጥ ላይ ነው። ታዲያ ማንዴላ ሥልጠናቸውን አጠናቀው ወደ አገራቸው ደቡብ አፍሪካ ሲመለሱ ይህን ማካሮቭ ሽጉጥ በጆሐንስበርግ ከተማ በሚገኘው የኤ.ኤን.ሲ ፓርቲ ኅቡዕ መሰብሰቢያ ግቢ ውስጥ ባለ አንድ ዛፍ ስር በምስጢር ቀብረውት ነበር።

ማንዴላ በኢትዮጵያ በተመለሱ ማግሥትም በዘረኛው የአፓርታይድ መንግሥት ‘‘በአገር ክዳት’’ ወንጀል ተከሰው ወደ ወኅኒ እንዲወረወሩ ተደረጉ። ማንዴላ ከ27 ዓመታት እስር በኋላ ከእስር ቤት ሲወጡ ያቺን የኤ.ኤን.ሲ ፓርቲ የትጥቅ ትግል ማብሰሪ የሆነች ማካሮቭ ሽጉጥ ከቀበሩበት ለማውጣት ወደ ጆሐንስበርግ የቀድሞው የፓርቲያቸው ኅቡዕ መሰብሰቢያ አዳራሽ ግቢ ከትግል ጓዶቻቸው ጋር አምርተው ነበር።

ይሁን እንጂ ቦታው በመቀያየሩና ጊዜው በመርዘሙ የተነሳ ማንዴላ በትክክል ቦታውን ለመጠቆም አልቻሉም ነበር። እናም ከኢትዮጵያዊው አሰልጣኛቸው ከጄ/ል ታደሰ ብሩ በስጦታ የተበረከተላቸውን ያችን ማካሮቭ ሽጉጥ ከተቀበረችበት ቆፍሮ በማውጣት ከኤ.ኤን.ሲ 100ኛ ዓመት ምስረታ በዓል ጋር በማስተሳሰር- የፀረ-አፓርታይድ ትግል ረጅሙ ጉዞ ታሪካዊ ቅርስና አሻራ እንድትሆን በማሰብ የተደረገው ሙከራም ሳይሳካ ይቀራል።

ሽጉጡን ቆፍሮ ለማውጣት የተደረገው ሙከራ ባይሳካም የደቡብ አፍሪካ መንግሥት በኔልሰን ማንዴላና በኤ.ኤን.ሲ የፀረ-አፓርታይድ ትግል ታሪክ ውስጥ ደማቅ አሻራ ያላትን ከኢትዮጵያዊው ጄኔራል ታደሰ ብሩ ለማንዴላ የተበረከተችውን ሽጉጥ የደቡብ አፍሪካውያን የነጻነት ትግል ቋሚ ማስታወሻ ቅርስ ናት። እናም ታሪኳ በሚገባ ሊዘከር ይገባል ሲል ‘‘the Mandela’s Gun’’ በሚል አርእስት ዶክመንተሪ ፊልም ለመስራት ነበር የደቡብ አፍሪካና የብሪቲሽ የፊልም ካምፓኒዎች የተጣመሩበት ቡድን ወደ አገራችን የመጡት።

በዚህ ዶክመንተሪ ፊልም ፕሮጀክት ውስጥ የማንዴላን የኢትዮጵያ ቆይታ፣ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ስልጠና በተመለከተ የጥናት ምርምር ሥራ ለመሥራት Senior Researcher ሆኜ ለመሥራት ዕድሉ ገጥሞኝ ነበር። በወቅቱ በዚህ ፕሮጀክት ውስጥ መሳተፌ ስለ ጄ/ል ታደሰ ብሩ በይበልጥ ለማወቅ ትልቅ ዕድል ነበር የሰጠኝ። ታዲያ በወቅቱ ስለጄ/ል ታደሰ ቃለ-መጠይቅ ካደረኳቸው መካከል ታናሽ እኅታቸው ወ/ሮ ጸሐይ ታደሰ እና የማንዴላ የቅርብ ሰውና ሌላኛው አሰልጣኛቸው የነበሩት ኮሎኔል ፈቃዱ ዋኬኔ ይገኙበታል።

ከወ/ሮ ፀሐይ ጋር በነበረን ቆይታም ታላቅ ወንድማቸው ጄ/ል ታደሰ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ አስፈላጊ ያሏቸውን መረጃዎችና ታሪካዊ ሰነዶች እንዳስረከቧቸውና እነዚህን መረጃዎችም በብረት ሳጥን ውስጥ ቆልፈው እንዳስቀመጧቸው አጫውተውኝ ነበር። ጄኔራሉ በተለይ ለነጻነት፣ ለፍትሕና እኩልነት ካደረጉት ትግላቸው ባሻገርም ከእነ ፕ/ር ኤፍሬም ይስሐቅ ጋር በመሆን በአብዛኛው በመሀይምነት ጨለማ ውስጥ የነበረውን የገጠሩን ኢትዮጵያዊ ከመሀይምነት እንዲላቀቅ ትልቅ አስተዋጽዖ ማድረጋቸውን ነግረውኛል። በወቅቱ ለማስተማር ይጠቀሙበት የነበረው የፊደል ሰራዊት ያየዘው የፊደል ገበታም ለታላቅ ወንድማቸው፣ ለጄ/ል ታደሰ ብሩ መታሰቢያነት በሚል በመኖሪያ ቤታቸው መግቢያ ግድግዳ ላይ በክብር ተሰቅሎ አስተውያለኹ።

ወ/ሮ ጸሐይ እንደነገሩኝ፤ ወንድማቸው ለነጻነትና ለፍትሕ ሲታገሉ የነበሩ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ነበሩ። ከደቡብ አፍሪካውያን የፀረ-አፓርታይድ ተጋድሎ ታሪክ ጋር በተያያዘም ጄኔራሉ ለወታደራዊና ለፖለቲካዊ ሥልጠና ወደ ኢትዮጵያ የመጡትን ኔልሰን ማንዴላን ለእውነትና ለፍትሕ፣ ለሰው ልጆች ነጻነት በጽናት እንዲቆሙ አስተምሯቸዋል። ዘረኛውን የአፓርታይድ ሥርዓት ለማስወገድ ማንዴላና የትግል አጋሮቻቸው ለጀመሩት የትጥቅ ትግል መታሰቢያ ይሆን ዘንድም ጄ/ል ታደሰ ብሩ ለማንዴላ ሽጉጥ አበርክተውላቸው ነበር።

ይህች ሽጉጥም ከነፃነት ምድር፣ ከጥቁር ሕዝቦች የነጻነት ተጋድሎ ታሪክ፣ የጥቁር ሕዝቦች ታሪክ፣ ቅርስና የስልጣኔ እምብርት ከሆነችው ከኢትዮጵያዊው መኮንን ከጄ/ል ታደሰ ብሩ ዘንድ በስጦታ የተገኘች ናትና በማንዴላና በትግል ጓዶቻቸው/በኤ.ኤን.ሲ ፓርቲ ልብ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያላት ናት።

ይህች ሽጉጥ ተራ ሽጉጥ አይደለችም፤ ይህች ሽጉጥ የከበረውን የሰውን ልጅ ደም በከንቱ ለማፍሰስ የተሰጠችም ሽጉጥ አይደለችም፣ ይህች ሽጉጥ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ለነፃነታቸው ክብር የከፈሉትን ክቡር መስዋዕትነት የምታሳስብ፣ ለጥቁር ሕዝቦች ነፃነት ተምሳሌት ትሆን ዘንድ ከጥቁሮች እናብስት ምድር ለማንዴላ የተበረከተች ማስታወሻ ናት።

ይህቺ የጄ/ል ታደሰ ብሩ ስጦታ የሆነች ሽጉጥ፤ ማንዴላና ደቡብ አፍሪካውያን ፈጣሪ በሰጠን ውብ ምድር ላይ ነፃነት፣ እውነትና ፍትሕ … ድል ነስተው እስኪወጡ ድረስ የአንቺ ሥፍራ የከበረ የአገራችን ጥቁር አፈር ነው ሲሉ፣ ያችን ነፃነት ዓርማ የሆነች ሽጉጥ በዘረኞቹ የአፓርታይድ አራማጆች ስብከትና የጥይት አረር በጥቁሮች ሕዝብ ደም ለጨቀየችው፣ በሕዝቦቿ ግፍና ሰቆቃ ለተጨነቀችው ምድራቸው በአደራ አስረከቧት።

በኢትዮጵያዊው ጀግና በጄ/ል ታደሰ ብሩ ልብ ውስጥ የናኘው የኢትዮጵያዊነት የነጻነት ሕያው መንፈስ፣ አይበገሬነት፣ ቆራጥነትና የጀግንነት ወኔ- ከኢትዮጵያ ምድር ተሻግሮ በማንዴላና በደቡብ አፍሪካውያን የነጻነት አርበኞች ልብ ውስጥ ትልቅ የነጻነት ሐውልት ተከሏል። እናም ኢትዮጵያዊውን ጀግና፣ ጄኔራል ታደሰ ብሩ የፀረ-አፓርታይድ ትግል አጋር አፍሪካዊው፣ ጄኔራል መባላቸውን ትክክል የሚያደርገው ይህ የከበረ ታሪካቸውና እኛም እንደ ኢትዮጵያዊ የምንጋራው አኩሪ የታሪካችን አካል መሆኑ ነው!!

ሰላም**!!**

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# እየጨመረ ያለው የተሻሻለ የእንስሳት መኖ ዝርያዎች ፍላጎት

ስምስም መንግሥቱ





አቶ መንግሥቱ ተሰማ በዘር ብዜት መሣ፤

ፎርደስግራስ፣ አልፋአልፋ፣ ሉሲኒያ፣ ላብላብ፣ የላም አተር (ካኦፒ)፣ ፒጃምፒ (የእርግብ አተር)፣ ፎደርቢት (የከብት ድንች)፣ ዲስሞዲየም፣ ሲናር፣ ፋለሪስ፣ ፓኒኮም፣ የሳር፣ የጥራጥሬና የሐረግ ዝርያዎች እንደ ሆለታ፣ ባኮ፣ አዳሚ ቱሉ ባሉ የእርሻ ምርምር ማዕከሎች በምርምር ተሻሽለው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማረጋገጫ የተሰጣቸው ለእንስሳት መኖ የሚውሉ ዝርያዎች ናቸው።

ፎስፈረስና ካልሺየም የተባሉ የተለያዩ ንጥረ ነገሮችን በውስጣቸው የያዙት እነዚህ የተሻሻሉ የመኖ ዝርያዎች በጎችና ፍየሎችን ጨምሮ የወተት ላም ምርታማነትን ለመጨመር፣የሥጋ ከብቶችን ለማደለብ ተመራጭ መሆናቸውን ተጠቃሚዎችና የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ። የዝርያዎቹ ምርታማነት የሚለያይ ቢሆንም፣ አንድ ጊዜ በማሳ ላይ ተዘርቶ ደጋግሞ ምርት የሚሰጥ ዝርያም አለ። በአንዴ የተመረተውንም ረዘም ላለ ጊዜ በመጠቀም የመኖ እጥረትን ማቃለል እንደሚቻል መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በድርቆሽ መልክ አዘጋጅቶ ጥቅም ላይ ማዋል ይቻላል፤ ይህም በተለይ በበጋው ወቅት የሚያጋጥመውን የመኖ እጥረት በማቃለል ረገድ የጎላ ሚና አለው። በአንድ ሄክታር መሬት ላይ አራት ኪሎ ግራም የተሻሻለ የመኖ ዘር ቢዘራ እስከ ስድስት ሜትር ኩብ ምርት ማግኘት እንደሚቻል ከአስር ዓመት በላይ በእንስሳት መኖ፣ የደን ዛፍ ችግኝ፣ እንዲሁም አትክልትና ፍራፍሬ ዘር ብዜት ሥራ ላይ የቆዩት መንግሥቱ ተሰማ የእጽዋት ዘር አምራችና አቅራቢ ድርጅት ባለቤት አቶ መንግሥቱ ተሰማ ያስረዳሉ።

አቶ መንግሥቱ እንደሚገልጹት፤ የተለያየ ዝርያ ያላቸውን የእንስሳት መኖ የዘር ብዜት የሚያከናውኑት በሰሜን ሸዋ በ10ሄክታር መሬት፣ በወላይታ ላይ ደግሞ በ21 ሄክታር መሬት እንዲሁም ከአርሶ አደሮች ጋር በጋራ በመሆን ነው። በተለይም ከአርሶ አደሩ ጋር ሲሰሩ ከመሬት ዝግጅት ጀምሮ እስከ ምርት መሰብሰብ ባለው ሂደት ክትትል ያደርጋሉ።

በዚህ ሂደትም አርሶ አደሩ ተሞክሮ ያገኝበታል። መሬቱን ለዘር ብዜት በማዋሉም ገቢ ያገኛል። ተረፈ ምርቱን ደግሞ ለእንስሳቱ መኖ በመጠቀም እንዲህ በተለያየ መንገድ ተጠቃሚ ይሆናል።

በዚህ መንገድ ድርጅታቸው እስከ ሁለት ሺ አምስት መቶ ኩንታል የተለያዩ የመኖ ዝርያዎች በማልማት ለተጠቃሚው እንዲደርስ ያደርጋል። እንደ ዝርያው አይነት የዋጋ ልዩነት ቢኖረውም፣ አርሶ አደሩ በተመጣጣኝ ዋጋ ያገኛል። ከፍተኛው የመኖ ዘር ዋጋ በኪሎ ግራም እስከ ሁለት ሺ አምስት መቶ ብር ቢሆንም፣ በኪሎ ግራም በ40 ብር ሊገዛቸው የሚችሉ ዝርያዎች በመኖራቸው ሁሉም እንደአቅሙና ፍላጎቱ መጠቀም ይችላል።

ድርጅታቸው በአብዛኛው የመኖ ዝርያ አቅርቦቱን የሚያከናውነው በመንግሥት የጨረታ ሂደት ውስጥ በማለፍ ሲሆን፣ አርሶ አደሩን በተለያየ መንገድ የሚረዱ እንደ የዓለም ምግብ ድርጅት (ፋኦ) እና በኔዘርላንድ ድርጅት የሚደገፉ አርሶ አደሩን በግብርና የሚያግዙ ተቋማትም ግዥ ያከናውናሉ። ድርጅቱ በግላቸው ግዥ የሚፈጽሙ አርሶ አደር ደንበኞችም አሉት።

የተሻሻለ መኖ ዘር ብዜቱ ብዙ ሂደት ውስጥ አልፎ ጥቅም ላይ እንደሚውል የጠቀሱት አቶ መንግሥቱ፣ የዘር ብዜት የሚከናወንበት የማሳ ዝግጅት፣ የዘሩ ጥራትና አዘራሩ፣ በአበባው ወቅት ደግሞ የብቅለት መጠኑ በባለሙያ ክትትል እንደሚደረግበት ይገልጻሉ። እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ምርቱ ከማሳ ላይ ከተሰበሰበ በኋላም ናሙና ተወስዶ በቤተሙከራ ፍተሻ ይደረግበታል። ድርጅታቸው ይህን ሁሉ የፍተሻ ሂደት የሚያልፈው በኦሮሚያ ክልል የደረጃና ቁጥጥር ባለሥልጣን በሚከናወን ክትትልና ቁጥጥር ነው። ከማሳ የተሰበሰበው የመኖ ዘር በብጠራና በለቀማ የበለጠ ጥራቱ እንዲረጋገጥም ድርጅታቸው ለዚህ ሥራ ሠራተኞችን ቀጥሮ ያሰራል።

የማከማቻ መጋዘንም ሰርቷል። ይህ ሁሉ ዝግጅት ጥራቱን የጠበቀ የመኖ ዘር ተጠቃሚው ዘንድ ለማድረስ ሲባል የሚደረግ እንደሆነ አቶ መንግሥቱ ያስረዳሉ። ለዜጎችም የሥራ ዕድል የፈጠረ ተቋም መሆኑም ሌላው የድርጅቱ መገለጫ ነው።

እርሳቸው እንዳሉት፤ መኖውን ለማምረት ያዘጋጁትን የዘር አይነት እና የዘር ብዜቱ የሚከናወንበት የእርሻ መሬት መጠን አመታዊ እቅድ ያወጣሉ። እቅዳቸውንም ለኦሮሚያ የግብርና ግብአት ቁጥጥር ባለሥልጣን አስቀድመው ያቀርባሉ። እንዲህ የቅድመ እቅድ ዝግጅት ተደርጎ፣ በባለሙያዎችም ክትትልና ቁጥጥር ሥራ ተከናውኖ የመኖ ዘር ብዜት ሥራ በጥራት ውድቅ ወይንም ከተቀመጠው መሥፈርት በታች የሚሆንበት አጋጣሚ ስለሚፈጠር ያልተቋረጠ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ ነው አቶ መንግሥቱ የተናገሩት።

አቶ መንግሥቱ በሥራው በቆዩባቸው አመታት በክፍተቶች ያጋጠሟቸውንና በጥንካሬም ያዩዋቸውን መልካም ጎኖች ገልጸውልናል። እርሳቸው ከአስር አመት በፊት የመኖ ዘር ብዜት ሥራ ውስጥ ሲገቡ በአርሶ አደሩ በኩል ዘሩን ለመጠቀም የነበረው ፍላጎት እጅግ አናሳ ነበር። ለአንዳንድ አርሶ አደሮች በነፃ በመስጠት እንዲጠቀሙ ለማበረታታትም የሞከሩባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ። አንድ ቀን ፍላጎት እንደሚጨምር ግን እርግጠኛ በመሆን የጀመሩትን ጥረት ቀጠሉ።

ቀድመው የተነበዩትን አሁን ላይ ማየት ችለዋል። በዚህ ወቅት የተሻሻለ የእንስሳት መኖ ፍላጎት እየጨመረ መጥቷል። መንግሥትም የተሻሻለ የእንስሳት መኖ ተጠቃሚነት እንዲጎለብት ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ትኩረት መስጠቱም አስፈላጊነቱን ያረጋግጣል።በአፋር፣ ባሌ፣ ሶማሌ ቆላማ የአገሪቱ አካባቢዎች የእንስሳት መኖ በመሥኖ እንዲለማ ጭምር በመንግሥት እንቅስቃሴ መደረጉ የዘር ብዜትና ልማት ሥራን ቀድመው ለጀመሩት ትልቅ ብርታትና የበለጠ የሚያነሳሳ ነው።

አገራዊ ተነሳሽነቱ ቀድሞ ተጀምሮ ቢሆንና የተሻሻለ መኖ ልማቱ ቢጠናከር የኢትዮጵያ የእንስሳት ሀብት ምንጭ የሆኑት የቦረና ከብቶች በውሃና በመኖ እጥረት ለድርቅ ባልተጋለጡና ብዙ እንስሳትም ለከፋ ጉዳት ባልተዳረጉ ነበር ይላሉ። ከዚህ በኋላም የተጀመረው ተነሳሽነት ቀጣይነት ሊኖረው ይገባል ባይ ናቸው።

አቶ መንግሥቱ በተግዳሮት ካነሱት አንዱ ከቴክኖሎጂ ጋር የተያያዘው ነው። የዘር ብዜቱን ሲያከናውኑ በራሳቸው የጥራት ደረጃውን እያረጋገጡ የሚያመርቱበት ሂደት ቢኖር በሥራቸው የበለጠ እርግጠኛ ለመሆን ያግዛቸዋል።

በቅርቡ በስካይላይት ሆቴል የተካሄደው የዶሮ ኤክስፖና ሰባተኛው የእንስሳት ሀብት ዐውደርዕይ ላይ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎች ቢቀርቡም እርሳቸው የሚፈልጉት ቴክኖሎጂ አልገጠማቸውም። እሳቸው ግን ተስፋ አልቆረጡም ቴክኖሎጂውን ካገኙ በራሳቸው ለመሥራት ቤተሙከራ (ላብራቶሪ) አዘጋጅተዋል። ቴክኖሎጂውን ለማግኘት የተለያዩ ጥረቶች በማድረግ ላይም ይገኛሉ። በዚህ በኩል የመንግሥት ድጋፍን ይፈልጋሉ።

የዘር ብዜት የሚከናወንበት የእርሻ መሬትም በትራክተር ቢታረስና ከአጨዳ እስከ ምርት መሰብሰብ በዘመናዊ መሣሪያ ቢታገዝ በምርታማነትም በጥራትም ተጠቃሚ መሆን ይቻላል ብለዋል። ቴክኖሎጂ መጠቀም ከተቻለ ከዘር ብዜቱ በተጨማሪ ለአመጋገብ ምቹ የሆነ መኖ ማዘጋጀት እንደሚቻል ጠቁመዋል።

ኤክስፖው መዘጋጀቱ ቴክኖሎጂዎችን ለማግኘት፣ አንዱ ከሌላው የልምድ ልውውጥ ለማድረግ፣ የገበያ እድል ለማስፋት ከማገዙ በተጨማሪ መንግሥት በመኖ ዘር ብዜትና ልማት ላይ የተሰማሩትን ማሳተፉ ለመኖ ልማቱ መስፋፋት የሰጠውን ትኩረት ማሳያም አድርገው ወስደዋል።

ሌላው ያነሱት በምርምር ተቋማት የወጡ የተሻሻሉ የመኖ ዘሮች ጥቅም ላይ ከዋሉ ከተወሰኑ አመታት በኋላ እየቀነሱ ስለሚሄዱ ቶሎ መተካት የሚኖርባቸው መሆኑን ነው። መሥራች ዘር በፍጥነት የመተካቱ ሁኔታ እጅግ የዘገየ በመሆኑና በአቅርቦት እጥረት በሚፈለገው ልክ የመተካቱ ሥራ እየተከናወነ አለመሆኑን ይጠቁማሉ። በዚህ ረገድ በምርምር ተቋማት በኩል ሊታሰብበት ይገባል ይላሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ዘርፉን በገንዘብ ወይንም ለመደገፍ የሚደረግ ጥረት የለም። በተለይ በባንኮች በኩል ብድር አልተመቻቸም። ለሥራ መነሻም ሆነ ለማስፋፋት ካፒታል ቢመቻች የበለጠ በመሥራት አቅርቦትን ማሳደግ ይቻላል።

የመኖ ማባዣ መሬት ለማግኘትም ተግዳሮት መኖሩን የጠቆሙት አቶ መንግሥቱ፣ አሁን ላይ የሚንቀሳቀሱት ከአርሶ አደር በኪራይ በሚያገኙት የእርሻ መሬት ላይ መሆኑን ይገልጻሉ፤ የመሬት የኮንትራት ዋጋም ውድ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከመንግሥት መሬት ቢያገኙ ግን በስፋት በማምረት አርሶአደሩ በጥራት፣ በአይነትና በተመጣጣኝ ዋጋም ዘር የሚያገኝበት እድል ይፈጠራል ብለዋል።

የተሻሻለ የመኖ ልማት በኩታገጠም (ክላስተር) ቢታገዝ ውጤታማነቱ ከፍተኛ እንደሚሆንም ሀሳብ ሰጥተዋል። እርሳቸው፤ በተሻሻለ የእንስሳት መኖ ዘር ብዜትና ልማት ላይ የተሰማሩ ተሰባስበው ማህበር በመመሥረት ዘርፉ አድጎ ውጤታማ የሚሆንበትን ለማመቻቸት ጥረት በማድረግ ላይ መሆናቸውንና ከሁለት አመት በፊት ማህበር መሥርተው በእንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኙም ገልጸዋል።

አቶ መንግሥቱ ከዘር ብዜት ማሳ ሰብስበው በብጠራና በለቀማ በጥራት አዘጋጅተው በማገዝ ለገበያ ዝግጁ ያደረጉትን የተሻሻለ የመኖ ዘር የማየት ዕድሉን አግኝተናል። እይታን የሚስቡ የተለያዩ ዘርፎችን ነው ያየነው። ከሙያው ውጭ ለሆነ ሰው ዘሮቹ ወደ ሳርነት ተቀይረው ለመኖ ይውላሉ ብሎ ለመቀበል ያዳግታል። ዘሩን ከባእድ ነገር ንክኪ ነፃ እንዲሆን ተደርጎ በመጋዘን ውስጥ በማስቀመጥ የተደረገውንም ጥንቃቄ ተመልክተናል። ስማቸው ተለጥፎበት በጠርሙስ ውስጥ የተቀመጡት የተለያዩ የመኖ ዘሮችም ትኩረትን ይስባሉ። በዚህ መንገድ የተዘጋጀ የተሻሻለ የእንስሳት መኖ በኢትዮጵያ ውስጥ ተዘጋጅቶ መቅረቡ ደስ የሚያሰኝ ሆኖ ነው ያገኘነው።

አቶ መንግሥቱ በሥራቸው ደስተኛ መሆናቸውን ከፊታቸው ገጽታ፣ ለሙያውም ቅርበት እንዳላቸው ከገለጻቸው መገንዘብ ችለናል። እርሳቸው እንደነገሩን ትምርታቸው ከግብርና ጋር የተያያዘ ከመሆኑ በተጨማሪ በዘርፉ በመንግሥት ተቋም ተቀጥረው ለአስር ዓመት ያህል አገልግለዋል። በግላቸው ወደ ሥራው ገብተው ለመምራት ያልተቸገሩበት ሚስጥርም የሙያው ባለቤት በመሆናቸው ነው።

ኢትዮጵያ በእንስሳት ሀብቷ ከአፍሪካ ቀዳሚ፣ በዓለምም ታዋቂ ሆና በተሻሻለ የመኖ ዝርያ የእንስሳት ምርታማነት እንዲጨምር ባለመደረጉ ከሌላው ዓለም ወደኋላ መቅረቷን በቁጭት ይገልጻሉ። ይህን ለመለወጥ እርሳቸውን ጨምሮ በዘርፉ ላይ የሚገኙት ጥረት ወሳኝ እንደሆነና የሚችሉትንም እንደሚያደርጉ ገልጸዋል።

ከእርሻ ሥራ ጎን ለጎን ከብቶችን በማድለብና ከሚያረቧቸው የወተት ላሞች የሚያገኙትን የወተት ምርት ለገበያ በማቅረብ ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት ላለፉት 12 ዓመታት ሲሰሩ መቆየታቸውን ያጫወቱን በዓለምጤና አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አርሶ አደር ዘውዴ እሸቱ ሲናር የተባለውን የተሻሻለ የመኖ ዝርያ ቀድመው ለከብቶቻቸው አለመመገባቸውን በቁጭት ይገልጻሉ። ሲናር የተባለውን የመኖ ዘር በጓደኛቸው አማካኝነት ከአቶ መንግሥቱ በነጻ አግኝተው መጠቀም ከጀመሩ ሁለት አመት ሆኗቸዋል። ቀደም ሲል ፋጉሎ በሚባለው የዘይት ተረፈ ምርት አንድ ከብት አደልቦ ለገበያ ለማድረስ እስከ አምስት ወር ጊዜ ይወስድባቸው ነበር። ፉሩሽካ ከሚመግቧቸው የወተት ላሞች የሚያገኙት የወተት መጠንም አነስተኛ ነው። ሲናር መኖን ለከብቶቻቸው መመገብ ከጀመሩ ወዲህ ግን በሶስት ወር ጊዜ አደልበው ለገበያ ማቅረብ ችለዋል። የላሞቻቸው የወተት ምርታማነትም ጨምሯል። የከብቶቻቸው ሰውነትም ከቀድሞው የተሻለ ሆኖ ነው ያገኙት።

አርሶ አደሩ ስለአዘራሩና አጠቃቀሙም እንደገለጹት፤ ሰብል በተሰበሰበ ማሳ ላይ ነው የመኖ ዘሩን የሚዘሩት። መኖው በመጠኑ ወፍራም ሲሆን፣ በመኮትኮት (ቾፕ) በማድረግ ከሌላ ግብአት ወይንም ገለባ ጋር በመቀላቀል ነው ለበሬዎቻቸው የሚሰጧቸው። ለወተት ላሞች ደግሞ ፉሩሽካ ከሚባለው ግብአት ጋር ይመግቧቸዋል።

ለከብቶቻቸው የተሻሻለ መኖ ማቅረብ በመቻላቸው በዚህ ወቅት ከብቶቻቸውን የሣር ግጦሽ ወደ ሚገኝበት ለማሰማራት የሚያጋጥማቸውን የእረኛ ችግር አቃልሎላቸዋል።ልጆችም ትምህርት ቤት ስለሚውሉ የሚጠብቅ የለም። በአሁኑ ወቅት ግጦሽም አይገኝም። በተለይ በጋ ላይ የመኖ እጥረት የከፋ በመሆኑ ክፍተቱን ይሞላላቸዋል።

አርሶ አደሩን በአካባቢያቸው ስላለው ተሞክሮም ጠይቀናቸው እርሳቸውን ጨምሮ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው አርሶ አደሮች ናቸው መኖውን መጠቀም የጀመሩት። የግጦሽ ሣር መጥፋቱና ከእረኛ ጋርም ተያይዞ እየተቸገሩ በመሆናቸው እንዲሁም ቀድመው የጀመሩት ያገኙትን ጥቅም በማየት ተሞክሮ ለማግኘት አንዳንዶች ፍላጎት እያሳዩ መሆናቸውን ተናግረዋል። በተሻሻለው የመኖ ዝርያ ላይ ያለው ግንዛቤ ቢዳብርና አቅርቦትም ቢኖር ከፍተኛ ለውጥ እንደሚገኝበትም ገልጸዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# በግል ትምህርት ቤቶች ክፍያ የሚፈተኑ ቤተሰቦች

**ጽጌረዳ ጫንያለው**




የግል ትምህርት ቤቶች በአገሪቱ ያላቸው የትምህርት አገልግሎት ድርሻ ከፍተኛ መሆኑን ማንም አይክድም። በተለይም ከትምህርት ጥራት ጋር በተያያዘ የመንግስቱን ትምህርት ቤት ባስናቀ መልኩ ጥሩ መሻሻሎችን ያመጡ ናቸው። ተወዳዳሪነትን ከመፍጠርም አኳያ የማይተካ ሚናን ተጫውተዋል። ይሁን እንጂ ለድሃው ማህበረሰብ የሚቀመሱ አልሆኑም። ምክንያቱም የሚጠይቁት የትምህርት ቤት ክፍያ በቀላሉ የሚገባበት አይደለም።

አንዳንዴ ሲታዩ ደግሞ የንግድ ተቋማት እንጂ አገልጋይ ተቋም ጭምር አይመስሉም። ሰበብ እየፈለጉ ማህበረሰቡን እየበዘበዙት እንደሆነ ብዙ ማሳያዎችን ማንሳት ይቻላል። የሶፍት፣ የተጨማሪ መጻሐፍት፣ የሳሙና ምናምን እያሉ ድሃ እንዳያስተምር ያደርጉታል። የወላጆች ገቢ ባላደገበት ሁኔታ በየጊዜው የተማሪዎችን ክፍያ ማናር ደግሞ ቤተሰብን ብቻ ሳይሆን አገርንም ለችግር የሚዳርግ እንደሆነ የማይካድ ሀቅ ነው። እናም ይህንን ታሳቢ በማድረግም እንደመንግስት የተለያዩ ውሳኔዎች እየተላለፉ ይገኛሉ።

አንዱ ከክፍያ ውጪ መጽሐፍትን አሳትሞ መሸጥ አይቻልም የሚለው ሲሆን፣ እየተሰማ ያለው ግን ከዚህ የተለየ ነው። ወረቀት ጨምሯል በሚል በክፍል ደረጃ በተለየ መልኩ የመጻሐፍት ዋጋ ሲጨምሩ ብዙዎች ላይ ይስተዋላል። መነሻችን የሆኑት ቅሬታ አቅራቢ አቶ መብራቱ ከበደ ይህንን ያረጋግጣሉ። ለቅድመ አንደኛ ክፍል ተማሪ እስከ ሁለት ሺህ ብር እየተጠየቁ እንደሆነም ያስረዳሉ።

ቀጥለውም የግል ትምህርት ቤቶች በየጊዜው በሚጠይቁት ክፍያ ምክንያት ወጪያቸው በተለያየ መልኩ እየጨመረባቸው እንደሆነ ይናገራሉ። ለአብነትም ከትምህርት ቤት ክፍያው በተጨማሪ የመመዝገቢያ በሚል 1500 ብር መክፈላቸው፣ የሳይኒታይዘር፣ የልብስ ሳሙና ወዘተ በሚል የተጠየቁት ገንዘብ ለአንድ ተማሪ ብቻ ሳይሆን ለአራትና አምስት ተማሪ ሲሆን እንደሚችል ያነሳሉ። ነገሮችን እያደረጉ ያሉት ልጃቸውን በምንም መልኩ ላለማሳፈር ብለው እንደሆነ ይገልጻሉ። ሕጉ ቢወጣም ተግባራዊ እየሆነ እንዳልሆነ ያስረዳሉ።

ወላጆች ልጆቻቸውን ለማስተማር እየተፈተኑ እንደሆነም የሚናገሩት አቶ መብራቱ፣ በተለይም አዲሱ የትምህርት ዘመን የጀመረ በመሆኑ ምላሽ ሳያገኙ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት ለመላክ እንደተገደዱና ይህም እንደሚያንገበግባቸው ያነሳሉ። ልጃቸውን የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ቅዱስ ሚካኤል ትምህርት ቤቶች የሚባል ሲሆን፣ እርሳቸው ልጃቸውን ቢልኩም አንዳንድ ወላጆች ግን በሁለት ምክንያት ልጆቻቸውን እስካሁን እንዳላስገቡ ያስረዳሉ። የመጀመሪያው የመክፈል አቅም ስለሌላቸው ሲሆን፣ ሁለተኛው ሕጉን ስላላከበራችሁ አናደርግም ያሉ መሆናቸውን ገልጸውልናል።

እንደ ትምህርት ቢሮ ተቋማቱ መጽሐፍት በራሳቸው አሳትመው መሸጥ አይችሉም። ተገቢ ያልሆኑና እነርሱ ሊያደርጓቸው የማይችሉ ነገሮች ላይም ክፍያዎችንም መጠየቅ የለባቸውም ተብሏል። ነገር ግን ከሕግ ውጪ ሆነው ይህንን እያደረጉ ይገኛሉ። የተጠየቁትን ጭምር በአግባቡ ለመመለስ ዝግጁ አይደሉም። ስለሆነም መንግስት ይህንን አይቶ መፍትሄ በአፋጣኝ ሊሰጠን ይገባል ይላሉ።

ድርጊታቸው የትምህርት ተቋማት የሚመሩበት ሕግ የለም እንዴ? ትምህርት በንግድ ሕግ ሊዳኝ አይገባም ወይ ያስብላል። ምክንያቱም ትምህርት ለሁሉም ዜጋ መብት መሆን እንዳለበት ቢታመንም እነርሱ ግን በአንዱ ሲገደቡ በሌላው እንድናወጣና ልጆቻችንን እንዳናስተምር እያደረጉ ናቸው። በአቅም ማነሥ ምክንያት ልጆችን ቤት እንዲቀሩ የማድረግ ሥራ እየሰሩም ይገኛሉ። እናም ለሕጉ እውን መሆን መንግስትና የትምህርት ተቋማት ብቻ ሳይሆኑ ግለሰቦች ጭምር መታገል እንዳለባቸውም ያስገነዝባሉ።

የግል ትምህርት ቤቶች ላይ እየታዬ ያለው የተጋነነ ወርሃዊ ክፍያ ሀይ ሊባል ያልቻለው መንግሥት ጣልቃ ገብቶ አንድ መላ ባለማበጀቱ ብቻ እንዳልሆነ የሚያነሱት አቶ መብራቱ፣ በትምህርት ተቋማቱ ላይ የሚሰሩ ባለሙያዎችም መመርመር አለባቸው ይላሉ። በምክንያትነት የሚጠቅሱትም መፍትሄዎች ቶሎ ያለመምጣታቸውና ለጥቆማ ተብለው የተቀመጡ ስልኮች አለመስራታቸውን ነው። ስለዚህም መማርም ሆነ ልጅ ማሥተማር ቅንጦት እንዳይሆን በታማኝነት ሁሉም ማገልገል እንዳለበት ያሳስባሉ።

ችግሩ ከግል ትምህርት ቤቶች አንጻር በሁሉም ክልሎች ያለና የሚተገበር ቢሆንም እንደ አዲስ አበባ አልጎላምና ይህንን የሚመለከተውን አካል ምን እየሰራ እንደሆነ ለማነጋገር ችለናል። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን ዓለም አቀፍ ወረርሽኝ የሆነው የኮረና ቫይረስ መስፋፋትን ተከትሎ ጀምሮ ነው ይህንን ተግባር ማከናወኑን የቀጠለው። በዚህም በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ የግል ትምህርት ቤቶች የገጽ ለገጽ የትምህርት አገልግሎታቸውን እንዲያቋርጡ፣ የአገልግሎት አሰጣጣቸውንም በተለያዩ መንገዶች እንዲያከናውኑ እና የሚያስከፍሉት የአገልግሎት ክፍያም ከ50 እስከ 75 በመቶ እንዲሆን አዟል።

መመሪያውን ተግባራዊ ያላደረጉ የግል ትምህርት ቤቶችም እንደነበሩ ታይቷል። እናም ባለስልጣኑ ይህንን ተከታትሎ የግል ትምህርት ቤቶቹን በመለየት መጀመሪያ ማስጠንቀቂያ ከዚያም እንቢኝ ሲሉ ለአንድ ዓመት የእውቅና ፍቃዳቸውን በማገድ ውሳኔ አስተላልፎ ተግብሮታል። ሆኖም ዛሬም ከድርጊታቸው ሲቆጠቡ አይታይም። እናም ይህንን አስመልክቶ በጉዳዩ ላይ የአዲስ አበባ የትምህርትና ስልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለስልጣን ውይይት አድርጓል። በወቅቱም የ2015 የትምህርት ዘመንን በተመለከተ በ2014 ዓ.ም ጭማሪ ያደረጉ ትምህርት ቤቶች በ2015 የትምህርት ዘመን ምንም ዓይነት ጭማሪ ማድረግ እንደማይችሉ መግባባት ላይ ደርሷል።

የባለስልጣኑ ዋና ስራ አስኪያጅ ወይዘሮ ሕይወት ጉግሳ እንደተናገሩት፣ ላለፉት ሁለት እና ሶስት ዓመታት ጭማሪ ሳያደርጉ የቆዩ ትምህርት ቤቶች በሚያቀርቡት ፕሮፖዛል እና ከወላጅ ጋር በሚያደርጉት መግባባት መሰረት ጭማሪ ማድረግ ይችላሉ። ነገር ግን ከወላጅ ፍላጎት ውጪ ምንም ሊያደርጉ አይገባቸውም። ይህንን ጥሶ የተገኘ ግን እርምጃ ይወሰድበታል። በመመሪያው መሠረት ያላግባብ ያስከፈሉ ካሉም ገንዘብ እንዲመልሱ ይደረጋል።

ችግሮቹን ለመፍታት ጠንካራ ቅድመ ዝግጅት ተደርጎ እየተሰራ እንደሆነ የተናገሩት ሥራ አስኪያጇ፣ በመጀመሪያ ዙር ምልከታ 26 ችግሩ ለታየባቸው ተቋማት የተገኙ ሲሆን፣ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ተሰጥቷቸዋል። ሁለተኛ ዙር ደብዳቤ የሚሰጣቸውም አሉ። እስከአሁን 50ና 60 ይሆናሉ። በተጨማሪም ለሦስተኛ ዙር 520 የሚሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮና የባለስልጣኑ ባለሙያዎች በጋራ ምልከታ እያከናወኑ ይገኛሉ። ይህ ሁኔታ ችግሩ እስከሚቆም ድረስም የሚቀጥል እንደሚሆን ያስረዳሉ።

ማንኛውም ችግር አስተማሪ የሚሆነው እርምጃ በመውሰድ ሳይሆን ችግሮችን በመመካከር በመፍታት እንደሆነ የሚገልጹት ወይዘሮ ሕይወት፣ ትምህርት የሚመራበትን ሕግ መረዳት ላይ ከተቋማቱ ጋር በተደጋጋሚ እየመከርንበት ነው። ትምህርትቤቶች ጥሰትን መሰረት አድርገው ለመተማመን መሞከር እንደሌለባቸውም በተደጋጋሚ ለማስገንዘብ ሞክረናል። ይሁንና ብዙዎቹ ከዚህ ችግራቸው መላቀቅ አልቻሉም። ያለን ላይ መደመርን መተማመኛ ማድረግን ይፈራሉ። ስለሆነም ባለስልጣኑ ይህ እስኪታረም ድረስ የሚሰራ ይሆናልም ይላሉ።

አሁን ባለው ሁኔታ የግል ትምህርት ቤቶቹ ጉዳይ ያልተገባ ክፍያ ችግር ብቻ የሚታይበት አይደለም። በመማር ማስተማሩ ላይ ጭምር ጥላ የሚያጠሉ ተግባራትን ሲፈጽሙ ይስተዋላል የሚሉት ወይዘሮ ሕይወት፣ በትምህርት ተቋማቱ ከተገኙት የአሰራር ችግሮች ውስጥ አንደኛው ከሌሎች አገራት የተቀዱ ሥርዓተ ትምህርትን በአገሪቱ የሥርዓተ ትምህርት መመዘኛ መስፈርቶች ሳይጠና ተማሪዎች እንዲጠቀሙ ማድረጋቸው ነው። ይህም ተማሪዎች ከአገር ውስጥ ባህል፣ ሥነ ሥርዓትና ጥበብ ጋር እንዲራራቁ በማድረግ በውጭ አገራት ባህል የሚማረክ ትውልድ እንዲፈጠር ያደርጋል።

ሁለተኛው ተማሪዎች በተገቢው ሰዓት መማር ያለባቸውን የትምህርት አይነት በሌሎች የትምህርት አይነቶችን እንዲተኩ ማድረግ ሲሆን፣ ይህም ተማሪዎች የትምህርት ፍላጎታቸው እንዲቀንስ ከማድረጉም በላይ ተደራራቢ የትምህርት ጫና እንዲፈጠርባቸውና ተማሪዎች ለጭንቀት እንዲዳረጉ ይጋብዛል። ሌላውና ሦስተኛው ችግራቸው ከአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የተያያዘው ጉዳይ ሲሆን፣ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል በአገር ውስጥ ቋንቋ መማር ያለባቸውን ትምህርቶች በእንግሊዝኛ እንዲማሩ ያደርጋሉ። ይህ ደግሞ በአገሪቷ በአፍ ቋንቋ የመማር መብትን የሚፃረር ነው። ስለዚህም ተቋማቱ ከወዲሁ መፍትሄ ማበጀት እንዳለባቸው ያሳስባሉ።

እንደ ወይዘሮ ሕይወት ገለፃ፣ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ተማሪዎች አገራቸውን እንዲያውቁ፣ እንዲደግፉና አገራዊ አስተሳሰብ ይዘው እንዲያድጉ ተደርጎ የተቀረፀ ነው። በዚህም በርካታ ምሁራንና የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል። እነዚህ አካላት ያልተሳተፉበትን የትምህርት ሥርዓት ለተማሪዎች ማስተማር አገርን ከማሳደግ ይልቅ ጉዳቱ ያመዝናል። በተጨማሪም ልጆች ከፍ እያሉ ሲሄዱ ትምህርት እንዲጠሉ ከማድረግ ባለፈ ልጆች ተገቢውን የአገር ፍቅር እንዳያገኙ ያደርጋቸዋል። እናም ተቋማቱ ይህንን አስበው መስራት ይኖርባቸዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ሕግን በሚጥሱ የትምህርት ተቋማት ችግር ምክንያት በአዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ትግበራ ውስጥ አራት አይነት ትምህርት ቤቶች ተፈጥረዋል የሚሉት ሥራ አስኪያጇ፣ አንደኛው በመንግስት ስርዓተ ትምህርት ጥራት ያለው ትምህርት እየሰጠ ያለው ሲሆን፣ ብቁ፣ ተወዳዳሪ፣ በስነምግባር የታነጸ ተማሪ እየፈጠረ ያለው ነው። ሁለተኛው በመንግስት ስርዓተ ትምህርት መሰረት የሚያስተምሩ ነገር ግን ከፍተኛ የወላጅ ጫና ያለባቸው ናቸው። ወላጆች የመንግስት ስርዓተ ትምህርትን የምታስተምሩ ከሆነ እናንተ ጋር ምን እንሰራለን ስለሚሏቸው ወጣ ገባ ለማለት የተገደዱ ትምህርት ቤቶች ናቸው።

ሦስተኛው የመንግስትንም የራሳቸውንም የሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች ናቸው። ለቁጥጥር ሲኬድባቸው ፖሊሲውን እየተገበሩ ለማስመሰል የሚያቀርቡ። እነዚህ የአፍ መፍቻ ቋንቋን እንደ ቋንቋ ብቻ የሚያስተምሩ ናቸውም። በአራተኛ ደረጃ የሚነሱት ደግሞ ሙሉ ለሙሉ የመንግስትን ስርዓተ ትምህርት የማያስተምሩ ናቸው። ከሌላ አገር የመጣ ስርዓተ ትምህርትን ይተገብራሉ። ከ1500 በላይ ተቋማት በዚህ አይነት አተገባበር ውስጥ ሆነው እየተንቀሳቀሱ ይገኛሉ። እናም ይህንን ለማስተካከል ከፍተኛ ሥራ ይጠይቃልና ወላጆች እያገዙን ካልሄዱ ሁኔታው ከባድ ይሆናል ብለዋል።

አጋዥ መጻሐፍት በሚል እያዘጋጁ ተማሪዎችን ለጭንቀት መዳረግም ትምህርት ቤቶቹ ከፈቃድ ውጪ የሚሰሯቸው ተግባራት እንደሆኑ የሚያነሱት ወይዘሮ ሕይወት፣ አጋዥ መጻሐፍ መዘጋጀት ካለበት ትምህርት ቢሮ ባሉት ባለሙያዎች አማካኝነት የሚያደርገው ይሆናል እንጂ ያልተገመገመና ለተማሪዎች የማይመጥን መጻሐፍ ማዘጋጀት አይፈቀድም። እዚህ ላይ መግባባት ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ ባለሥልጣኑ ጠንካራ የትምህርት ክትትልና ጥራት ፍተሻ እያደረገ የሚቀጥል ሲሆን፣ ሁሉም ትምህርት ቤቶች ግን ሊያግዙት ይገባል። በእኩል ደረጃ ችግሮችን ለመለወጥ መትጋት እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል።

የባለስልጣኑ ምክትል ሥራ አስኪያጅ ፍቅርተ አበራ ሀሳብ በበኩላቸው እንዳሉት፣ ቀደም ብሎ በተደረገው አጭር ምልከታ 12 የግል ትምህርት ቤቶች ጭማሪን አስመልክቶ የወጣውን መመሪያ ጥሰው ተገኝተዋል። በዚህም ከመመሪያ ውጪ የሰበሰቡትን ገንዘብ ለወላጅ መልሰው ሪፖርት እንዲያደርጉ ታዘዋል። መልሰናል ያሉ ትምህርትቤቶች ተገኝተዋል። ይሁንና አሁንም የክፍያንና መሰል ጭማሪዎችን ያደረጉ የግል ትምህርት ቤቶች እንዳሉ አሁንም ጥቆማ እየደረሰ ነው። በዚህም ዛሬ ድረስ ተቋማቱን ለመየት ተከታታይ ሥራ በተዋቀረው ቡድን አማካኝነት እየተከናወነ ይገኛል። ለዚህ ያግዝ ዘንድ ደግሞ እንደ ባለስልጣኑ ለክትትል የሚላኩ ባለሙያዎች አቅጣጫ ተሰጥቶዋቸው እንዲሄዱ ተደርጓል። ባለሙያዎቹ የተከፈለበትን ደረሰኝ ጭምር ተመልክተው እንዲያረጋግጡ የሚያደርግ የመገምገሚያ ሰነድም ተዘጋጅቷል። ከተቻለም በየአንዳንዱ ተቋም የተወሰኑ ወላጆችን ማነጋገር የሚቻልበት አሠራር ተዘርግቷል። የተለያዩ ጥቆማዎች በመኖራቸው አሠራሩን እንደሚያሻሽለው ይታመናል።

ትምህርት ቤቶች ከመደበኛ ክፍያ ውጪ በየትኛውም መልኩ ክፍያ ማስከፈል አይችሉም፣ አንድ የትምህርት ተቋም ፍቃድ የተሰጠው ለማስተማር እንጂ፣ መጽሐፍም ሆነ ደብተር ለመሸጥ አይደለም። ስለዚህም ከተሰጠው ፍቃድ ውጪ የተንቀሳቀሰ ተቋም ከተገኘ ርምጃ ይወሰድበታል። ምክንያቱም ዓላማው የኅብረተሰቡ የመክፈል አቅም፣ የኑሮ ውድነት ችግርን ታሳቢ ባደረገ መልኩ መስራትን ያስቀደመ ነውና ይህንን የሚያደሩጉ አካላትን እንደማይታገሱም ያነሳሉ።

የትምህርት ጉዳይ የንግድ ጉዳይ አይደለም፣ የአገር መገንባት ጉዳይ እንጂ። ስለዚህም ትምህርት ቤቶች የትምህርት ሕጉን አክብረው መስራት ይኖርባቸዋልና እንደ ዜጋና እንደ አገር አስበው ቢሰሩ መልካም ነው እያልን ለዛሬ የያዝነውን በዚህ አበቃን። ሰላም!!

# ወቅታዊ

# "በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያለውን ጠላት ፈልገን ካከሰምን በጫካ ያለው ሸኔ ከመስመር ይወጣል"

\- ብርጋዴር ጀነራል ኃይሉ ጎንፋ
የፓርላማ አባልና የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት የደህንነት አማካሪ

**አስቴር ኤልያስ**

ብርጋዴር ጀነራል ኃይሉ ጎንፋ ተወልደው ያደጉት ምዕራብ ሸዋ እጪኒ በተባለው አካባቢ ነው። ትምህርታቸውን በጉደርና በአምቦ የተማሩ ሲሆን፣ መከላከያ ገብተው አገራቸውን በተለያየ መስክ አገልግለዋል። መከላከያ ከገቡ በኋላ የተለያየ ስልጠና ወስደዋል። ከአገር ውጪም በራሽያ ትምህርታቸውን የተከታተሉ ሲሆን፣ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ይዘዋል። ብርጋዴር ጀነራል ኃይሉ፣ ሰላም ማስከበር ላይ የተሳተፉ ናቸው፤ አገራቸውንም 21 ዓመት ያህል አገልግለዋል። እያዩ የነበረው ሁኔታ አጥጋቢና ስኬታማ ባለመሆኑ ወደትግል መሄድን አማራጭ አድርገዋል። ትግሉንም የተቀላቀሉት ከባድሜ ጦርነት በኋላ በ1998 ዓ.ም ነው። ከለውጡ በኋላ ግን ተመልሰው ወደአገራቸው በመግባት ሰላማዊ ትግሉን መቀላቀል ችለዋል። በአሁኑ ሰዓት መንግስትን እያገለገሉ ሲሆን፣ የፓርላማ አባልና የኦሮሚያ ክልል የፕሬዚዳንቱ የደህንነት አማካሪ ናቸው። በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በኦሮሚያ ቋንቋ የሚታተመው የበሪሳ ጋዜጣ ከብርጋዴር ጀነራል ኃይሉ ጋር በአገራዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ያደረገውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅረነዋል።

**አዲስ ዘመን፡- በትግል ላይ ቆይተው ለውጡን ተከትለው ወደ አገር ቤት ከገቡ ቆይተዋል፤ በወቅቱ ማንን ነበር ሲታገሉ የነበሩት? የት ነበር ስትታገሉስ የነበረው?**

**ብርጋዴር ጀነራል ኃይሉ፡-** በአገሪቱ ያለው የፌዴራሊዝም ስርዓት ነው ይባል እንጂ ስርዓቱ ሲያገለግል የነበረው ከብዙኃኑ ይልቅ ጥቂቶችን ብቻ ነበር። ይህ አግባብ አይደለም በሚል ትግል ውስጥ ቆይተናል። ምክንያቱም የኦሮሞ ሕዝብ በነበረው ስርዓት ከሚባለው በላይ ሲገፋ እና ሲጨቆን እንዲሁም ሲታሰር ቆይቷል። ከአገር እንዲሰደድም ተደርጓል። ከዚህም የተነሳ ነው ወደጫካ በመግባት ትግል ማካሄድ የጀመርነው። በዚህም የኦሮሞ ነጻ አውጪ ድርጅትን ተቀላቀልን። ለውጡ የመጣው በዚህ መሃል ነው። በመሆኑም ከለውጡ በኋላ ጠብመንጃ የሚያስነሳ ጉዳይ ስላልነበረ ወደ አገር የገባነው ትግላችንን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለማካሄድ በመስማማት ነው። በለውጡ የመጣ ትልቅ ነገር አለ፤ ይሁንና ሁሉም ተሳክቷል ባይባልም የቀረ ነገር መኖሩ የማይካድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ባለው ሁኔታ ጠብመንጃ ማንሳት የሚያስችል ትግል አለ ብለው ያስባሉ?**

**ብርጋዴር ጀነራል ኃይሉ፡-** ሲጠየቅ የነበረው የኦሮሞ ጥያቄ ሶስት ነበር። የመጀመሪያው የማንነት ጥያቄ ነበር። ማንነት ሲባል ኦሮሙማ ማለት ነው። ሁለተኛ ጥያቄ ደግሞ የአገር ባለቤትነት ነበር። እንዲህ ሲባል ትርጉሙ ብዙ ነው፤ ለምሳሌ በውስጡ የነጻነት ጥያቄ አለው። በአገሩ ባለቤት የመሆን ጥያቄንም የሚያካትት ነበር። ሶስተኛው ደግሞ እንደኦሮሞ የፌዴራል ስርዓት ውስጥ በሚያደርገው አስተዋጽኦ ምላሹም እንደእዛው መሆን አለበት የሚል በመሆኑ ትግሉ ረጅም ጊዜ ሊወስድ ችሏል።

ትግል ሲባል መሳሪያ ስላለን ወይም መሳሪያ ስላነሳን የሚደረግ ጉዳይ አይደለም። እታገልለታለሁ ለሚለው ሕዝብ በትክክል የዚያን ሕዝብ ጥያቄ አግባብነት ባለው አካሄድን ተከትዬ እየጠየቅሁ መሆኔን ማወቅ አለብኝ። ጠብመንጃ ማለት ግን በሰላማዊ መንገድ መታገል ያቃተኝን ነገር በጉልበት የማስኬደው ነገር ነው። አሁን ያለንበት ነገር ግን ጠብመንጃ የሚያስነሳ ነገር የለውም።



ፎቶ፡- በአሸናፊ ጉደታ

ያለጠብመንጃ በርካታ ነገሮችን ማሳካት ይቻላል።

ባለፉት 27 ዓመታት ስንታገል የቆየነው ነገር እውነተኛ የሆነ ነገር ስለነበር ነው። በወቅቱ ከሚደርሰው ጭቆና ራስን ለማላቀቅ በመወሰኑ ነው። ለምሳሌ ኦሮሞን ሊጠቅም የሚችለውን ነገር ታግለን ድል አግኝተናል። ያገኘውን ድል ደግሞ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ማጣጣም መቻል ነው። ከዚህ በኋላ በሰላማዊ መንገድ መደረግ ያለበት ነገር ጠላትን ከኦሮሞ ላይ ማሳነስና ወገን የሆነውን ማብዛት ነው። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ አገር ላይ ገዝፈን ለመታየት ራስን ማዘጋጀት ነው። እኛ ሰፊ ብሔር ነን። የትልቅ ብሔር ጥያቄ ማንሳት እንጂ እንደ ትንሽ መሆን የለብንም። እኛ ከዚህ በኋላ ማልቀስ የለብንም፤ ሌላውንም ሰው ማስለቀስ አይኖርብንም።

አሁን ሸኔ የሚያደርገው በኦሮሞ ላይ እንደመሳለቅ የሚቆጠር ነው። የኦሮሞ ሕዝብ የከፈለውን መስዋዕትነት አለማወቅ ነው። በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ባዕድ መሆን ነው። የሌላውን አካል ፍላጎት ማስፈጸም እንጂ የኦሮሞን ሕዝብ ፍላጎት መጠበቅ ማለት አይደለም።

**አዲስ ዘመን፡- እናንተ ወደትግል የገባችሁት በወቅቱ የነበረው የጊዜው ሁኔታ አስገድዷችሁ እንደነበር ጠቅሰዋል፤ አሁን ሸኔ በኦሮሞ ላይ ጠብመንጃ ማንሳቱን እንዴት ያዩታል?**

**ብርጋዴር ጀነራል ኃይሉ፡-** ኦሮሞ ሁሉን ያውቃልና ለእርሱ እንዲህ ነው ብዬ የምናገረው ነገር የለኝም። የኦሮሞ ሕዝብ በብዙ መንገድ ተምሯል ብዬ አምናለሁ። በመከራ ውስጥ ያለፈ በመሆኑ ከዛ የወሰደው ተሞክሮ አለ ብዬም አስባለሁ። ከነበረው ተጽዕኖ የተነሳ ልጁን በብዙ መንገድ ገብሯል። ይህን የሚያውቁ ሁሉ በትግሉ ጊዜ የሚያስፈልገውን ነገር ሁሉ ከጀነራሎች ጀምሮ ሼሆች፣ ቄሶችን ጨምሮ ታዋቂ ሰዎችም ሳይቀሩ በትግሉ አስፈላጊነት ላይ ልዩነት አልነበራቸውም። ትግሉም ያስፈልገናል በሚል አግዘውና መርቀው የሚጠበቅባቸውን አድርገዋል። ለውጥ መምጣት የቻለውም በእነርሱ የድካም ውጤት ጭምር ነው።

አሁን ግን ትግሉ ሰላማዊ በመሆኑ ‹ወደ ጫካ ሒዱና እርስ በእርሳችሁ ተገዳደሉ› ብሎ የሚመርቅ አባገዳ የለም። ሼሁም ቢሆን ‹‹ወደወንዝ ወርዳችሁ እርስ በእርስ ተገዳደሉ› አይሉም። ‹ጫካ ወርዳችሁ ተገዳደሉ› የሚሉ የኦሮሞ ሊቆችም በጭራሽ የሉም።

ጫካ ወርዳችሁ ተጣሉ የሚለው በርቀት ያለ የአገር ጠል ነው። ከዚህ ድርጊታቸው በእነርሱ ተንጠላጥሎ የፖለቲካ ትርፍ የሚያገኘው ኃይል ነው ያንን የሚያዛቸው። ኦሮሞ ኦሮሞን መግደሉ የሚደንቅ ነው፤ እንዲህ አይነቱ ድርጊት ከዚህ ቀደም በመካከላችን የሌለ ነው። እርግጥ ሁላችንም አንድ አይነት አመለካከት እና አስተሳሰብ የግድ ይኖረናል ማለት አይደለም። በመሰረታዊ ነገር ላይ ግን አንድ ልንሆን ይገባል። በዚያን ወቅት ጫካ አስገብቶ ሲያታግለን የኖረው የአገር ባለቤትነት፣ ነጻነትና የማንነት ጥያቄ ስለነበረን ነው።

በአሁኑ ወቅት ግን ጫካ ያለው አካል (ሸኔ) ትልቅ ስህተት እየፈጸመ ነው። ኦሮሞን ለ150 ዓመት ያህል ወደኋላ የጎተተውን ጉዳይ በተለያየ የእውቀት ዘርፍ በመሰማራት ወደፊት ማምጣት ተገቢ ነው እንጂ በዚህ ዘመን ጠብመንጃ አያስፈልገንም፤ ጠብመንጃ የሚመልሰን ወደኋላ ነው። በምንም አይነት ሁኔታ እንዲህ አይነት ኦሮሞን ራሱን መልሶ የሚያጠፋ ትግል አይተን አናውቅም።

እህል የሚያቃጥል ትግል፣ የጤና ተቋማትን የሚያጋይ ትግል፣ አምቡላንስን የሚያቃጥል ትግል፣ መንገድን የሚከለክል ትግል አይተን አናውቅም። እንዲህ አይነቱ ድርጊት የነጻነት ትግል ሳይሆን የባርነት ድርጊት ነው። ይህ ነውር ነው። የኦሮሞን ሞራልም የሚሰብር ድርጊት ነው። ይህ ከሆነማ ለዚያን ያህል ዓመታት ስንታገል የቆየነው ለምንድን ነው ያሰኛል። የኦሮሞን ንብረት የምናቃጥል፣ የምናወድም እና ንብረቱን የምናሳጣ ከሆነ ስለምን ደከምን ያስብላል። ቋንቋችንን ደባልቆ እርስ በእርስ እንዳንስማማ የሚያደርገን የጠላት ተልዕኮ ነውና ከዚህ ድርጊትና አስተሳሰብ ልንወጣ ይገባል። በእርግጥ ብዙዎች ይህ መንገድ አግባብነት የሌለው መሆኑን ተገንዝበዋል፤ ያልተገነዘቡ አሁንም ቢሆን ከዚህ ውስጥ መውጣት አለባቸው እላለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ በኦሮሚያ የተለያዩ አካባቢዎች ተዘዋውረው መጎብኘትዎ ይታወቃል፤ ኦሮሞን ከሰላም አንጻር ያለበትን ሁኔታ እንዴት ይገልጹታል?**

**ብርጋዴር ጀነራል ኃይሉ፡-** ኦሮሚያ በትግል ውስጥ ናት። ትግሉም የማንነትን ጉዳይ ማስጠበቅ፣ በእውቀት መላቅና ከሌሎች ጋር አብሮነትን በመፍጠር ረገድ የሚደረግ ነው። የአገር ባለቤትነትን አስተማማኝ የማድረግ ትግልና ራስን ማስተዳደር ነው። ይህን አይነት መልካም የሆነ ትግል ምልዑነት እንዲኖረው ለማድረግ የሚደረግ ሩጫ ነው። ይህን ሰላማዊ ትግል ከእጅ ለማስጣል የሚያደርጉ አካላት ግን አሉ።

ኦሮሞ ሰፊ ሕዝብ ነው። ኦሮሞ ጉልበታም ነው፤ ጉልበታም የሚያደርገው አንዱ ብዛቱ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ያለው የምጣኔ ሀብቱ ነው። ሶስተኛው ደግሞ መልካምድራዊ አቀማመጡ ነው። እነዚህ ሁሉ ስላሉት ጠላቶች በርክተውበት ቆይቷል። አሁን በዚህ ትግል ውስጥ ያለች ኦሮሚያን የጠላት ተላላኪ የሆኑ ደግሞ ትግሏን ለማስቀየስ ሲባዝኑ ይስተዋላሉ። እርስ በእርስ

# ወቅታዊ



**አሁን ሸኔ የሚያደርገው በኦሮሞ ላይ እንደመሳለቅ የሚቆጠር ነው፡፡ የኦሮሞ ሕዝብ የከፈለውን መስዋዕትነት አለማወቅ ነው፡፡ በኦሮሞ ሕዝብ ላይ ባዕድ መሆን ነው፡፡ የሌላውን አካል ፍላጎት ማስፈጸም እንጂ የኦሮሞን ሕዝብ ፍላጎት መጠበቅ ማለት አይደለም፡፡**

ለማጣላት የሚፈልገውን አካል ግን ስርዓት እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ ነው። ይህም ስርዓት የማስያዙ ጉዳይ በቅርቡ ምላሽ ያገኛል የሚል እምነት አለኝ። በዚህ ሁሉ መሃል ግን ጫና ሊኖር ይችላል፤ ልማትንም በሰላማዊ መንገድ ለማሳለጥ ይከብድ ይሆናል። አሁንም አንዱ ሌላውን ከቦታው ማሳደዱ አልቆመም። ይሁንና ይህ ጊዜያዊ ነው፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚያበቃ ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- በምዕራብ ኦሮሚያ እንዲሁም ሰሜን ሸዋ አንዳንድ አካባቢ የሸኔ ቡድን የሚዘዋወር እንደሆነ ይነገራል፤ ከዚህ ውስጥ ለመውጣት ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**ብርጋዴር ጀነራል ኃይሉ፡-** በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ እና አንዳንድ ቦታዎች ስናስተውል የሰላም ሁኔታው አስቸጋሪ ነው፤ ኦሮሞ ሰላም አግኝቶ አርሶ እንዳይበላ እየተደረገ ነው፤ የተማረ ሰው መብቱን ለመጠየቅ ይችላል። ነገር ግን ሰው እንዳይማር እንኳን ትምህርት ቤት ያቃጥላሉ። ቡድኑ ትምህርት ከነጻነት በኋላ ነው በሚል ብሒል ውስጥም በመግባቱ ይህ አግባብነት የሌለው ነው። ትናንት የነበሩ እንደ እነ ጄኔራል ታደሰ ብሩ አይነት ጀግኖቻችን ይሉን የነበረው ተማሩ፤ ተመራመሩ እንጂ ትምህርት ቤት አቃጥሉ አልነበረም። የተማረ ሰው ከባርነት ነጻ የሚወጣበትን መንገድ ያውቃል። ስለዚህ የሰላም መታጣትን የሚያመጣው አለማወቅ ነው።

ሰላም እንዲታጣ የሚደረገው አለማወቅ እንዲኖር በማድረግ ነው፤ ይህ እንዳይሆን መደረግ ያለበት በሶስት መንገድ ነው ብዬ አስባለሁ፤ የመጀመሪያው የኦሮሞን ሰላም ማጣት ለሚፈልገው ለላኪው ባለመላላክ ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ ተሳስቶ በዛ ውስጥ የገባን አካል በማስተማር ነው። ሶስተኛው ደግሞ ተጸጽቶ እንዲመለስ በመምከር ነው። በእነዚህ ሶስቱ የማይመለስ ከሆነ ደግሞ እርሱ በመጣበት መንገድ ወታደራዊ ስልት መጠቀም ነው። ይህ ሕዝብ ለረጅም ጊዜ ታግሎ ሰላም ሲያጣ ማየት ያሳዝናል። እንዲህ እያደረገ ያለው የራሱ ልጅ በመሆኑ የሚመከረውን መክሮና ዘክሮ መመለስ ሲሆን፣ አልመከር ያለውን ደግሞ አሳልፎ መስጠት ይጠበቅበታል።

**አዲስ ዘመን፡- የኦሮሚያ ክልል ሰላም እንዲሆንና አካባቢውም ሁሉ ሰላም ውሎ እንዲያድር ከማን ምን ይጠበቃል ይላሉ?**

**ብርጋዴር ጀነራል ኃይሉ፡-** ሰላም በመገዳደል አይመጣም፤ ሰላም የሚመጣው እርስ በእርስ በመረዳዳትና አንድነታችንን በማጠናከር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በማስተዋል መስራት ስንጀምር ነው። ለውጥ ማምጣት የሚችለው በጠብመንጃ አይደለም። በጠብመንጃማ ቀደም ሲል ብዙ ጊዜ ሰላም ለማምጣት ተሞክሯል። ሰላም ማምጣት የሚቻለው በመነጋገርና በመመካከር ነው። በአሁኑ ሰዓት ስልጣን ላይ ያለው መንግስት ሰላም እንዲመጣ ሲያደርግ የነበረው የኃይል ትግል ሰላማዊ ወደሆነው ትግል እንዲመጣ ማድረግ በመቻሉ ነው።

ለኦሮሞ ሕዝብ አሁን ካለው መንግስት የተሻለ የሚመጣለት መንግስት የለም። ከዚህ ያነሰ እድል ይመጣ ይሆናል እንጂ ከዚህ በኋላ ከዚህ የበለጠ ምቹ ሁኔታ አይመጣም። በየሰርጣሰርጡ ያሉ ቡድኖች የኦሮሞን ሕዝብ ከዚህ በኋላ ወደታች ለመመለስ የሚጥሩ ካልሆነ በስተቀር ከዚህ በላይ እድል የለም ባይ ነኝ። ስለዚህ ይህን እድል በአግባቡ ለመጠቀም አንደኛ አንድነትን ማጠናከር መልካም ነው። እንዲህም ሲባል በመካከላችን መከባበር መኖር አለበት። ታላቆችን ማክበር ያስፈልጋል። አዋጩ ይህ ነው፤ የላላውን የአንድነት ገመድ ማጠናከር ተገቢ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሕዝቡ መንግስት መዋቅር ውስጥ ያለው አካል ሰላምን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ሒደት አራዝሟል ይላል፤ ይህን ሁኔታ ሕዝቡ ባገኘው መድረክ ላይ ሁሉ ያንጸባርቃል። እርስዎ እዚህ ላይ ምን ይላሉ?**

**ብርጋዴር ጀነራል ኃይሉ፡-** እውነት ነው፤ ሕዝቡ ይህን ጉዳይ ስለመናገሩ ሐሰትነት የለውም። አንድ የማንወሻሽው ነገር ቢኖር የመንግስት መዋቅር ከሌላው ጋር የተቀላቀለ ነው፤ ትናንት በጥፊ ሲመታን የነበረውም ሆነ ሲያስጨንቀን የነበረውም በአንድ ላይ ተሸክመን እየተጓዝን ነው ማለት ያስደፍራል። በመሆኑም በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያለው አካል በጫካ ካለው ሸኔ በላይ ስጋት ነው።

በመሆኑም በመንግስት መዋቅር ያለውን ችግር ማጥራት ተገቢ ነው። ምክንያቱም አንዴ በዚህኛው አንዴ ደግሞ በዚያኛው እያሉ በሁለት ቢላዋ እየበሉ መኖር ከዚህ በኋላ የሚቻል አይሆንም። በጫካ ካለው ጠላት ይልቅ በመንግስት መዋቅር ውስጥ ያለውን ጠላት ፈልገን ካከሰምን በጫካ ያለውም ከመስመር ይወጣል።

ስለሆነም ሕዝብ በመንግስት መዋቅር ውስጥ የተሰገሰገ አካል አለ እያለ ያለው ነገር ትክክል ነው። ምክንያቱም የተለያየ አገልግሎት ፈልጎ ወደመንግስት ተቋማት ሲሄድ ጥቅማጥቅም የሚጠየቅ ከሆነ፣ አገልግሎት ማግኘት ፈልጎ በአግባቡ ሳይስተናገድ እና አገልግሎቱን ሳያገኝ ከቀረ መንግስት ሕዝብን የሚያገለግልና የሕዝብ መንግስት ነው ማለት ይከብዳል። ይህን ጉዳይ ከሕዝብ ጋር በመሆን ታግሎ ማስተካከል ያስፈልጋል። በመንግስት መዋቅር ውስጥ የዴሞክራሲ ችግር መኖሩ መቶ በመቶ የሚታመን ነው። እንደ አንድ በመንግስት መስሪያ ቤት ውስጥ እንደሚሰራ እንዲሁም ትናንት ደግሞ ሲታገል እንደቆየ ሰው ይህን ጉዳይ አጥርቼ መያዝ አለብኝ ብዬ አስባለሁ።

በመንግስት መዋቅር ውስጥ ሌቦች እና አጭበርባሪዎች እንዲሁም ያለችሎታቸው የገቡ ብዙዎች አሉ። እነዚህ አካላት ደግሞ ጠላት የሆነውን ቡድን በማገልገል ላይ ነው ወይ ያሉት? ከተባለ አዎ ነው መልሱ። ስለዚህ ምን ማድረግ አለብን? የሚባል ከሆነ ደግሞ እነዚህን አካላት ማጥራት ተገቢ ይሆናል፤ ከማን ጋር? የሚባል ከሆነ ደግሞ ከራሱ ከሕዝብ ጋር በመሆን የሚል ነው መልስ የሚሆነው። መንግስት ደግሞ በዚህ ላይ ቁርጠኝነቱ አለው።

ይህን ጉዳይ ለማወቅ የተለየ ጥናት የሚያስፈልገው አይደለም። ስርዓት አለ፤ በጀትም አለ፤ የመንግስትን መዋቅር እያስቸገረ ያለው ነገር አንዱ ሰነፍ መሆን ነው፤ እውቀቱ እያለው ከስንፍናው የተነሳ ማከናወን አለመቻል ነው። ሁለተኛው አስቸጋሪ ጉዳይ እውቀት ማጣት ነው። ያንን ነገር መስራት ይፈልጋል፤ ነገር ግን እውቀት ደግሞ ስለሌለው ስራውን ማከናወን ይሳነዋል ማለት ነው። ይህን መንግስት ተረድቷል። ዋናው ነገር መረዳቱ ነው። ከተረዳ ማጥራት ይችላል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ በዝግጅት ክፍሉ ስም አመሰግናለሁ።**

**ብርጋዴር ጀነራል ኃይሉ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

# ዓለም አቀፍ

## በህንድ የመጀመሪያው መራጭ በ105 ዓመታቸው አረፉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የህንድ የመጀመሪያ መራጭ በመባል የሚታወቁት ግለሰብ በ105 ዓመታቸው ከዚህ አለም በሞት ተለዩ።

ህንድ ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነጻ መውጣቷን ተከትሎ የመጀመሪያውን ጠቅላላ ምርጫ ስታካሂድ ሽያም ሳራን ኔጊ የመጀመሪያው መራጭ እንደነበሩም ተነግሯል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ህንድ ባደረገቻቸው ምርጫዎች ሽያም ሳራን ድምጻቸውን ሰጥተዋል።

ከትናንት በስቲያ ከመሞታቸው ከሶስት ቀናት በፊት በሂማካል ፕራዴሽ ግዛት በነበረው ምርጫም ላይ ድምጻቸውን በፖስታ ልከዋል።

ጡረተኛውም መምህር በበረዶ ውሽንፍር ምክንያት ምርጫው አምስት ወራት ቀደም እንዲል በሚኖሩበት ግዛት መወሰኑን ተከትሎም ነው በአውሮፓውያኑ 1951 የመረጡት።

በዚህም የምርጫ ውጤት የህንድ ብሔራዊ ኮንግረስ ከፍተኛ ድል የተቀዳጀ ሲሆን፤ ጃዋሃርላል ኔህሩም በዲሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጡ የመጀመሪያው ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኑ።

ይህም ምርጫ ከአውሮፓውያኑ 1848-1947 ለ100 ያህል የገዛው የብሪታንያ ቅኝ አገዛዝም ማክተሚያ ሆነ።

በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ አገሪቱ በህዳር ወር ከምታካሂደው ምርጫ በፊት ኔጊ ድምጻቸውን በፖስታ ሲልኩም የህንድ ምርጫ ኮሚሽን ባለስልጣናት ቀይ ምንጣፍ ዘርግተውላቸዋል።

የህንድ ሚዲያዎች እንደዘገቡት፤ ኔጊ በጤና እክል ምክንያት በምርጫ ጣቢያ ላይ ያልተገኙት



ሽያም ሳራን ኔጊ

ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑን ዘግበዋል።

በአውሮፓውያኑ 2014 ኔጊ መራጮችን ለማበረታታት በሚል የምርጫ ኮሚሽኑ አምባሳደር ሆነው የተሾሙ ሲሆን፤ አገሪቱ ባደረገችው አጠቃላይ ምርጫ በርካቶች እንዲመርጡ በሚያበረታታ የጉግል ቪዲዮም ላይ ተሳትፈዋል።

ረቡዕ እለት የምርጫ ድምጻቸውን በፖስታ በላኩበት ወቅት ወጣቶች እንዲመርጡ ማበረታታቸውን የህንዱ ዘ ትሪቡት ጋዜጣ ዘግቧል።

"ወጣቶች በምርጫ መሳተፍ መብታችን ሳይሆን ኃላፊነታችንም መሆኑንም በማወቅ በዲሞክራሲያዊ ሒደቱ ለመሳተፍ ወደፊት መምጣት አለብን" ሲሉም ተደምጠዋል።

የህንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ናሬንድራ ሞዲ ቅዳሜ ዕለት በነበረ የምርጫ ዘመቻ ላይ ለኔጊ የነበራቸውን ክብር ገልጸዋል።

ኔጊ በካልፖ በሚገኘው መንደራቸው በሚደረገው የቀብር ስነ ስርዓት ባህሉ በሚፈቅደው መሰረት አስከሬናቸው በክብር እንደሚቃጠል መንግስት ተናግሯል።

## ትራምፕ እና ኦባማ መጪው ምርጫ በሀገራቸው ላይ ስጋት እንደሚያሳድር ተናገሩ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ሁለቱ የቀድሞ የአሜሪካ የቀድሞ ፕሬዚዳንቶች ባራክ ኦባማ እና ዶናልድ ትራምፕ በፔንሲልቫኒያ ባደረጉት የግማሽ አመት የምርጫ የድጋፍ ቅስቀሳ ምሽት ላይ ሁለቱም ስለ አገራቸው ያላቸውን የተለያየ ስጋት ገልጸዋል።

ኦባማ ይህ የግማሽ አመት ምርጫ የአሜሪካን የዴሞክራሲ ጉዞ የሚወስን ነው ሲሉ፤ ትራምፕ ደግሞ የአገሪቷን የደህንነት ጉዳይ ቁርጡን የምናውቅበት ነው ሲሉ ቀስቅሰዋል።

የፔንሲልቫኒያ ግዛት ዴሞክራቶችም ሆኑ ሪፐብሊካን የበላይነት የሌላቸው ሲሆን፤ በተለያየ ጊዜ ለተለያየ ፓርቲ የሚመረጥበት በተለምዶ "ስዊንግ ስቴት" ተብለው ከሚጠሩ ግዛቶች አንዱ ነው።

በግዛቲቱ ሪፐብሊካኑም ሆኑ ዴሞክራቱ በሚያሸንፉበት ወቅት የሚኖረው የድምጽ ልዩነት እጅግ ጠባብ ነው።

በቅርቡ ለሚካሄደው የግማሽ አመት ምርጫ የግዛቲቱ ድምጽ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ ነው ሁለቱ የቀድሞ ፕሬዚዳንቶች ፓርቲያቸውን ለማገዝ እና ለመቀስቀስ የተገኙት።

እ.ኤ.አ. በ 2016 ትራምፕ ዋይት ሃውስን ለማግኘት የዚሁ ግዛት ድል ረድቷቸዋል። በመቀጠልም በ 2020 የጆ ባይደን የትውልድ ግዛት የሆነችውን ፔንሲልቫኒያን ዴሞክራቶች 2 በመቶ በሚሆን የድምጽ ብልጫ አሸንፈው ተረክበዋታል።

ጆ ባይደን በፊላደልፊያ ቅዳሜ ዕለት ተገኝተው ቅስቀሳቸውን ባደረጉበት ወቅትም "ወደ ቤቴ በመመለሴ ደስ ብሎኛል" ብለዋል። ፓርቲያቸው ላቀረባቸው ዕጩም ድጋፋቸውን ለግሰዋል።

ዲሞክራቶች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አብላጫ ድምጽ የማያገኙ ከሆነ የጤና መድህን ብሎም የጽንስ ማቋረጥ መብቶች ላይ ተጨማሪ እገዳ እንዲጣል ማስቻል እንደሆነም ተናግረዋል።

የምርጫው ውጤት ትንበያዎች እንደሚያሳዩት ዴሞክራቶች በኮንግረስ የበላይነትን አያገኙም። ይህንንም ተከትሎ ቢያንስ በሴኔት የበላይነትን ለማግኘት ከፍተኛ ትንቅንቅ እያደረጉ ናቸው።

"በዚች የአሜሪካ የልብ ምት በሆነችው ግዛት ውስጥ መስቀለኛ መንገድ ላይ እንገኛለን" ሲሉ ጆ ባይደን ተናግረዋል። አክለውም ለዲሞክራቶች ድምጽ መስጠት ማለት ለሴቶች ጤና፣ በጦር መሳሪያ ቁጥጥር ብሎም ለጤና አገልግሎት ድምጽ መስጠት ነው ሲሉም አክለዋል።

አንድ የግዛቲቱ ነዋሪ የትኛውንም ፓርቲ ይደግፉ የፕሬዚዳንቶቹ መገኘት ነዋሪው ወጥቶ እንዲመርጥ ያስችላል የሚል ተስፋ እንዳላቸው ለቢቢሲ ተናግረዋል።

ነገር ግን ፕሬዚዳንቶቹን ለመመልከት ከወጡት ነዋሪዎች መካከል የተወሰኑ አባማን ለማየት መምጣታቸውን እና ባይደን ለብቻቸው ቢሆኑ ኖሮ ግን እንደማይመጡ ተናግረዋል።

በምርጫ ዘመን አጋማሽ ላይ የሚደረገው ይህ 'የሚድ ተርም' ምርጫ በስልጣን ላይ ያለው ፕሬዚዳንት ላይ የሚደረግ ሕዝበ ውሳኔ ተደርጎ ይታያል። የጆ ባይደን ተቀባይነት 40 በመቶ ላይ እንዳለ በሚነገርበት በዚህ ወቅት ሪፐብሊካኑ የኑሮ ውድነት እና ስደትን የመሳሰሉ ምክንያቶችን በማንሳት ፕሬዚዳንቱ ላይ ቅስቀሳቸውን እንዲያጧጡፉም ረድቷቸዋል።

ትራምፕ በበኩላቸው ዲሞክራቶች በዋሽንግተን የሚቆዩ ከሆነ ለተጨማሪ ወንጀሎች እንዲሁም ላልተገደበ የስደተኞች ፍሰት ያጋልጣሉ ሲሉ ቀስቅሰዋል።

"ለቤተሰባችሁ ደህንነት እና ጥበቃ የምትፈልጉ ከሆነ እያንዳንዱን ዴሞክራት በድምጻችሁ ከወንበሩ ማስነሳት አለባችሁ" ብለዋል።

"ያለው ምርጫ አንድ ብቻ ነው። የአሜሪካን መውደቅ የምትፈልጉ ከሆነ ድምጻችሁን ለአክራሪ ዴሞክራቶች ስጡ። የአገራችንን መውደም የማትፈልጉ ከሆነ ግን ሪፐብሊካንን ምረጡ" ሲሉ ትራምፕ ቀስቅሰዋል።

እንዲሁም በ 2024 ለሚደረገው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ሊወዳደሩ እንደሚችሉም ጠቁመዋል። እንዲሁም በድጋሚ የአሜሪካ የምርጫ ስርአት የተጭበረበረ ነው የሚለውን የሃሰት ክሳቸውን ማቅረባቸውን ቀጥለዋል።

አንድ የዶናልድ ትራምፕ ደጋፊ የቀድሞው ፕሬዚዳንት "ህይወትን ያለ ጭቆና እና ምን ማድረግ እንዳለብን ሳይነገረን እንድንኖር ረድተውናል" በሚል ለድጋፍ መውጣቱን ተናግሯል።

በርካታ መራጮች በፍርሃት እና በሃሰት ቅስቀሳዎች ታጅበው ከሁለት ቀናት በኋላ በሚካሄደው የግማሽ አመት ምርጫ ይሳተፋሉ። ይህም የአሜሪካን የምርጫ ስርአት ታማኝነት የሚፈተሽበት ነውም ብለው ያምናሉ ሲል ቢቢሲ አስነብቧል።

## አምስተኛ ደረጃ የድርድር ሽያጭ ማስታወቂያ

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጅማ ዲስትሪክት ስምና አድራሻቸው ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የተዘረዘሩት ተበዳሪዎች ለሰጠው ብድር አመላለስ በመያዣነት የያዘውን የመያዣ ንብረቶች ባሉበት ሁኔታ በድርድር ሽያጭ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የተበዳሪው/የመያዣ ሰጪው ስም/ | ንብረቱ የሚገኝበት አድራሻ | የሚሸጠው ንብረት አይነት | የመሬት ስፋት/ሄክታ/ | የለማው መሬት ሄክታ/ | የጨረታ ሽያጭ መነሻ ዋጋ / ብር | የድርድር ሽያጭ ሳጥኑ የሚከፈትበት ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጋምበር እርሻና አጠቃላይ ንግድ ድርጅት ኃ/የተ/የግ/ማኅበር | በጋምቤላ ክልል፣ አኝዋ ዞን፣ ደሣ ወረዳ፣ ጊዱ ቀበሌ ወስጥ | ግንባታዎች፣ ተሽከርካሪ፣ የእርሻ መሣሪያዎችና የለማ መሬት | 811 | 159.177 | 5,685,787.47 | ህዳር 27 ቀን 2015 ዓ.ም ከ4፡00-6፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ |
| 2 | አሸናፊ ገ/መስቀል እርሻ ልማት | በጋምቤላ ክልል፣ አኝዋ፣ ዞን፣ ዲማ ወረዳ፣ አቻኛ ቀበሌ | ግንባታዎች፣ የለማ መሬትና የእርሻ መሣሪያዎች | 1000 | 397.181 | 7,981,607.85 | |
| 3 | ደብሪች አስመጪና ላኪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | | | 1000 | 422.192 | 8,828,659.40 | |
| 4 | ኤዲ የእርሻ ሥራ ሽርክና ማኅበር | በጋንቤላ ክልል፣ አኝዋ፣ ዞን ዲማ ወረዳ አኩላ ቀበሌ | ግንባታዎች የለማ መሬትና የእርሻ መሣሪያዎች | 1500 | 525.94 | 15,054,420.80 | |
| 5 | ሁንዴ ሊሊሳ እርሻ ልማት ኃ/የተ/የግ/ማኅበር | | | 1500 | 225.6 | 6,277,429.50 | |
| 6 | ሽምበሊና እርሻ ልማት ኃ/የተ/የግ/ማህበር | በጋንቤላ ክልል አኝዋ ዞን ዲማ ወረዳ ጊዱ ቀበሌ | ግንባታዎች የለማ መሬትና የእርሻ መሣሪያዎች | 500 | 427.077 | 6,787,687.67 | |
| 7 | ጉዑሽ ገ/ስላሴ እርሻ ልማት | | | 500 | 207.3 | 6,434,690.51 | |
| 8 | ዲማሮዝ እርሻ ልማት ኃ/የተ/የግ/ማ | በጋንቤላ ክልል አኝዋ ዞን ዲማ ወረዳ ጊዱ ቀበሌ | ግንባታዎች የለማ መሬትና የእርሻ መሣሪያዎች | 500 | 250.43 | 5,610,893.44 | |
| 9 | ዲማጌድ የተቀናጀ እርሻ ልማት ኃ/የተ/የግ/ማ | | | 500 | 205.431 | 4,971,007.98 | |
| 10 | ግንበወርቅ ገብረማያም እርሻ ልማት | በጋንቤላ ክልል አኝዋ ዞን ዲማ ወረዳ አኩላ ቀበሌ | ግንባታዎች የለማ መሬትና የእርሻ መሣሪያዎች | 1000 | 227.603 | 6,507,013.25 | |
| 11 | ሃዱሽ አምባዬ እርሻ ልማት | | | 1000 | 351.76 | 8,235,396.75 | |
| 12 | ገ/ማርያም አብረሃ እርሻ ልማት | | | 500 | 165.4 | 5,290,089.93 | |
| 13 | አድኃርሳ እርሻ ልማት ኃ/የተ/የግ/ማህበር | በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/ምዕ/ኦሞ ዞን ሜኒትሻሻ ወረዳ ኩጁሙጉት ቀበሌ | ግንባታዎች የለማ መሬትና የእርሻ መሣሪያዎች | 299.569 | 125.229 | 3,217,924.27 | |
| 14 | ጌታቸው ለገሰ እርሻ ልማት | በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/ምዕ/ኦሞ ዞን ሚኒት ሻሻ ወረዳ ጎሪነሱ ቀበሌ | | 300.52 | 130.116 | 3,191,530.44 | |
| 15 | አመርከዝ አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማህበር | በጋንቤላ ክልል አኝዋ ዞን ዲማ ወረዳ መርከዝ ቀበሌ | | 500 | 73.082 | 3,926,530.04 | |

### ማሳሰቢያ

1. ተጫራቾች የጨረታውን መነሻ ዋጋ 1/4 ኛ (አንድ አራተኛ) በባንክ ክፍያ ማዘዣ /CPO/ ብቻ በማስያዝ መጫረት ይችላሉ፡፡
2. ተጫራቾች የዋጋ ማቅረቢያ ማመልከቻቸው ላይ 1ኛ ለፕሮጀክቱ የሚያቀርቡትን ዋጋ 2ኛ ለንብረቱ የሚከፍሉትን የቅድሚያ ክፍያ መጠን 3ኛ ቀሪ ክፍያውን ከፍለው የሚያጠናቅቁበትን ጊዜ 4ኛ ለቀሪ ዋጋ አከፋፈል ከሚገዙት ንብረት በተጨማሪ የሚያቀርቡት የመያዣ ዓይነት፣ የመያዣው ግምት እና የሚገኝበት ቦታ 5ኛ በድርድር መግዛት ለፈለጉት ንብረት ተበዳሪ መያዣ ሰጪ ስም በግልፅ በመጻፍ እስከ ህዳር 21 ቀን 2015 ዓ.ም ከቀኑ 10:00ሰዓት) ድረስ በጅማ ዲስትሪክት ጽ/ቤት ለዚሁ አላማ በተዘጋጀ የድርድር ሽያጭ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል:
3. አሸናፊ የሆነው ተጫራች ያሸነፈበትን ቀሪ ገንዘብ በ15 /በአስራ አምስት/ ተከታታይ ቀናት ውስጥ አጠቃሎ ካልከፈለ ያስያዘው ገንዘብ ለባንኩ ገቢ ሆኖ ሐራጁ ይሰረዛል፡፡ በተጨማሪ ንብረቱ በድጋሚ ለሐራጅ ሲቀርብ በሚታየው የዋጋ ልዩነት ይጠየቃል፡፡
4. ሽያጩ ከላይ በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት በጅማ ዲስትሪክት ጽ/ቤት ውስጥ ሲከፈት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በቦታው በመገኘት ሂደቱን መከታተል ይችላሉ፡፡
5. አሸናፊው ተጫራች ያስያዘው ገንዘብ ከግዢው ዋጋ ጋር የሚታሰብ ሲሆን ለተሸነፉት ያስያዙት ገንዘብ ይመለሳል፡፡
6. ገዢው ፕሮጀክቱን በገዛበት ዋጋ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ 15% (አስራ አምስት በመቶ) ጨምሮ ሌሎች ገዢ እንዲከፍላቸው በሕግ የተወሰነ ታክስና ግብሮችን፣ የስም ማዛወሪያ ክፍያን ጨምሮ ገዢው /የጨረታ አሸናፊው/ ይከፍላል፡፡
7. የድርጅቱ ተሽከርካሪዎች እና የእርሻ መሣሪያዎች የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ያልተከፈለባቸው ከሆኑ ገዢው ከቀረጥ ነጻ መብት ሊኖረው አሊያም በመንግስት የሚፈለገውን ቀረጥ ለመክፈል ይገደዳል፡፡
8. ባንኩ ለጨረታ የቀረበውን ንብረት የሚሸጠው ከተቻለ ሙሉ በሙሉ በጥሬ ገንዘብ ወይም አሸናፊው በባንኩ ብድር ፖሊስ መሠረት አስፈላጊውን መስፈርቶች ካሟላና የፕሮጀክቱን ሥራ የሚያስቀጥል ከሆነ ንብረቱን በከፊል ብድር ለመግዛት መጠየቅ ይችላል፡፡
9. ዝርዝርና ተጨማሪ መረጃን በተመለከተ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ጅማ ዲስትሪክት በአካል በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር 047-111-09-08 ወይም 047-111-0016 ደውሎ ማግኘት ይቻላል፡፡ ፕሮጀክቶቹን መጐብኘት የሚፈልጉ ካሉ ከጅማ ዲስትሪክት ጋር አስቀድሞ ቀጠሮ በመያዝ መመልከት ይቻላል፡፡
10. ባንኩ የተሻለ መንድ ካገኘ ሽያጩን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**ጅማ ዲስትሪክት የኢትዮጵያ ልማት ባንክ**

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

ሰኞ
አዲስ ዘመን
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የኬንያውያን የስፖርት አበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነትና ስጋት

ብርሃን ፈይሳ

በስፖርት ክብርንና ድልን ለማግኘት አቋራጭ መንገድን መከተል በተለይ በአትሌቲክስ ስፖርት ጎልቶ ይታያል። ታዲያ በዚህ ስፖርት በተሻለ ውጤታማ የሆኑ አገራት በዓለም አቀፍ የጸረ አበረታች ቅመሞች ተቆጣጣሪ ተቋማት በአይነቁራኛ ነው የሚጠበቁት። በአትሌቲክስ ስፖርት በተለይም በረጅም ርቀቶች የበላይነቱን የተቆጣጠሩት የምስራቅ አፍሪካ አገራት አትሌቶችም ለዚህ ጉዳይ ተጋላጭ መሆናቸው ይነገራል። በእርግጥም ተጠቃሚነቱ በተለያዩ ጊዜያት በመረጋገጡ ክትትሉም ተጠናክሮ ቀጥሏል።

ከምስራቅ አፍሪካዊያኑ የአትሌቲክስ አገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ስትሆን በ2010 ዓ.ም ስድስት አትሌቶች ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ለቅጣት መዳረጋቸውን የኢትዮጵያ ጸረ አበረታች ቅመሞች ባለስልጣን የተገኘው መረጃ ያሳያል። ከ2011 ዓ.ም-2014 ዓ.ም ባሉት እያንዳንዱ ዓመታት ደግሞ ሶስት ሶስት አትሌቶች ተጠቃሚ መሆናቸው ተረጋግጧል። ይህ ቁጥር እንደ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ቢሆንም ከሌላው ዓለም አንጻር ከስጋት ቀጣና የወጣ ነው። ይህ ሊሆን የቻለውም አገሪቷ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥታ የሰራችበት በመሆኑ በአህጉርም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተምሳሌት አድርጓታል።

በአንጻሩ የምንጊዜም የኢትዮጵያ ተፎካካሪ የሆነችው ኬንያ በአበረታች ቅመሞች ማጥ መውጣት አልቻለችም። ይኸውም ንጹህ ተወዳዳሪነትን ተግባራዊ እያደረጉ ላሉት አትሌቶች ውጤት እንዲያጡ በባዕድ ነገር እገዛ የሚሮጡት ደግሞ የማይገባቸውን ድል እንዲያገኙ ማድረጉ አሳሳቢ ነው። ኬንያ አሁን ያለችበት ሁኔታ ከአትሌቲክስ ስፖርት ሙሉ ለሙሉ ከተወገደችው ሩሲያ ልምድ ያልወሰደና ወደ ቅጣት የመንደርደር ሁኔታ የሚታይበት መሆኑም ግልጽ ነው። በዚህ የፈረንጆች ዓመት ብቻ በአበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት ተጠያቂ የሆኑ ኬንያውያን አትሌቶች ቁጥር 20 መድረሱን አፍሪካን አትሌቲክስ ዩናይትድ የተባለ ድረገጽ ያስነብባል።

በዓለም አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የአበረታች ቅመሞች ላይ ከሚሰራው አካል (AIU) የተገኘው ማስረጃ እንደሚያመላክተው ከሆነ፤ በቅርቡ እንኳን ሁለት አትሌቶች ባልተገባ ሁኔታ መሮጣቸው ተረጋግጧል። የመጀመሪያዋ አትሌት ያለፈው ዓመት የቦስተን ማራቶን አሸናፊ የነበረችው ዲያና ኪፕዮኬ ስትሆን፤ የተከለከለ መድሃኒት መጠቀሟ እንዲሁም ይህንን ለመሸፈንም የተሳሳተ መረጃ በመስጠቷ ከድሏ ማግስት ነው የተረጋገጠባት። ቤቲ ሌምፖስ ደግሞ ባለፈው የፈረንጆቹ ዓመት የፓሪስ ግማሽ ማራቶን አሸናፊ ስትሆን አትሌቷ ርቀቱን ሮጦ ለመጨረስ የፈጀባት ጊዜም 65:46 ነበር። አትሌቷ ያልተገባ መድሃኒት ከመጠቀሟ ባለፈ የተሳሳተ መረጃ መስጠቷ ተረጋግጦባት ለቅጣት ተዳርጋለች።

በተያዘው ዓመት ብቻ ሌሎች ሶስት አትሌቶችም በተመሳሳይ ሁኔታ ዓለም አቀፉ የጸረ አበረታች ቅመሞች ኤጀንሲ የከለከላቸውን መድሃኒቶች ተጠቅመው በመገኘታቸው ለሶስት ሶስት ዓመታት ዕገዳ መዳረጋቸውን መረጃው ያመላክታል። የፍራንስ 24 ዘገባ ደግሞ 25 ኬንያውያን አትሌቶች በአበረታች ንጥረነገሮች ተጠቃሚነታቸው ተረጋግጦባቸው ለቅጣት መዳረጋቸውን ነው ያስነበበው። እንደ መረጃው ከሆነም 19 የሚሆኑት በዚህ ዓመት ተጠቅመው የተገኙ ናቸው።



ከዚህ ጋር ተያይዞም የዓለም የማራቶን ክብረወሰን ባለቤቱና ዕውቁ ኬንያዊ አትሌት ኢሉድ ኪፕቾጌ ሁኔታውን «አሳፋሪ» ሲል ነበር የገለጸው። ከኬንያ አትሌቲክስ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መካከል አንዱ የሆኑት በርናባስ ኮሪር ሁኔታውን በጥንቃቄ እየተመለከቱት መሆኑን ነው የገለጹት። የቀድሞው አትሌት ኬንያ የሩሲያ አትሌቲክስ ባቀናበት መንገድ እየተጓዘች ስለመሆኑም ነው ያስጠነቀቁት።

በዚህ ዓመት በኬንያ ከተመዘገቡት የስፖርት አበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት ቅሌት በተለይ የታየው በጎዳና ላይ ሩጫ አትሌቶች ነው። ታዲያ ይህ ጉዳይ የሚያሳየው አትሌቶች ከእነዚህ ውድድሮች በሚያገኟቸው ከፍተኛ መጠን ላለው የገንዘብ ሽልማት ሲሉ ለተጠቃሚነት እንደሚዳረጉ ነው። የኬንያ ጸረ አበረታች ቅመሞች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ኃላፊ የሆኑት ሳራ ሺቡትስ፤ አብዛኛዎቹ አትሌቶች ከደሃ ቤተሰብ የተገኙ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ። በመሆኑም በዓለም አቀፉ የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ተቋርጦ የቆየው ውድድር ዳግም መመለሱ አትሌቶች ለገንዘብ ሲሉ ተገቢ ያልሆነ ነገር ውስጥ እንዲገኙ ያደረጋቸው መሆኑንም ነው የገለጹት። በመሆኑም ኤች አይ ቪ ኤድስን ለመከላከል የተደረገው ዓይነት ርብርብ የአበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነትን ለመግታት የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት እንዳለበትም ነው ኃላፊዋ የገለፁት።

ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር
ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# በሳይበር ደህንነት ውስጥ የሕግና የሕግ አውጭ አካላት ሚና

ይበል ካሳ

የሳይበር ደህንነትን በማስጠበቅ ሂደት ውስጥ ለአገራት ፈታኝ ከሆኑ ጉዳዮች መካከል ከሕግ ጋር የተያያዘው አንዱና ዋነኛው ነው። ለዚሁ ተግዳሮት መፈጠር ዋነኛው መንስኤ የሚመጣውም ከራሱ ከምህዳሩ ባህሪይ ነው። የመጀመሪያው ነገር ከተለመደው የዓለማችን ምህዳር በተለየ የሳይበር ምህዳር ምናባዊና ድንበር የለሽ በመሆኑ ከሳይበር ደህንነት ጋር በተያያዘ የሚወጡ ሕጎችን ለመፈጸምና ለማስፈጸም እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ ነው። የምህዳሩን ደህንነት ለማስጠበቅ የሚያግዝ ሕግ አውጥቶ ለመተግበር የአንድ አገር የተናጠል ጥረት ብቻ አይበቃም። ሥራው የግድ የሁሉንም የምህዳሩ ተጠቃሚ አገሮች የጋራ ትብብርና ኃላፊነት ይጠይቃል። ለምን ቢባል ከሳይበር ምህዳር አኳያ በድንበር የተከፋፈሉ በርካታ አገራትን ያቀፈ ዓለም የለም፤ ያለምንም ድንበር ሁሉም አገሮች አንድ ሆነው የሚኖሩበት አንድ ዓለም ብቻ ነው ያለው።

በመሆኑም በነባራዊው ዓለም አንድ አገር በሌላ አገር ላይ ወይንም አንድ በሌላ አገር የሚኖር ግለሰብ ወይም ቡድን ምህዳሩን በመጠቀም በሌላ አገር መንግሥት፣ ግለሰብ ወይንም ተቋም ላይ የሳይበር ወንጀል ቢፈጽም በመጀመሪያ ወንጀሉ ከየት እንደተፈጸመ ለማወቅ ያስቸግራል። በሁለተኛ ደረጃ ቦታው የት እንደሆነ ቢታወቅ እንኳን ጥቃት የፈጸመውን አካል በህግ ተጠያቂ ለማድረግና ወንጀለኛውን ለመያዝ የግዴታ የአገራቱን ትብብር ይጠይቃል።

በሌላ በኩል የኢንፎርሜሽን ኮምዩኒኬሽን እንዲሁም የአውታረ መረብ ቴክኖሎጂው በከፍተኛ ደረጃ እያደገ መምጣቱን ተከትሎ ድንበር የለሹ ምህዳር የፈጠረውን ምቹ ሁኔታ በመጠቀም የሚፈጸመው ጥቃትና ወንጀልም በዚያው ልክ በአሳሳቢ ደረጃ እየጨመረ መጥቷል። በዚህ መንገድ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚፈጸመው የሳይበር ጥቃት ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ በመምጣቱና የብሔራዊ ደህንነትና ሉዓላዊነት ስጋት የመሆን ደረጃ ላይ ደርሷል። እናም ምህዳሩን በህግ ለማስተዳደር የቱንም ያህል አስቸጋሪ ቢሆንም የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅና የአገርንና የሕዝብን ብሔራዊ ደህንነት ለመጠበቅና ሉዓላዊነትን ለማስከበር ህግ የግዴታ አስፈላጊ መሆኑ ዘመኑ ከፈጠራቸው ትልልቅ ተቃርኖዎች መካከል አንዱና ዋነኛው እንዲሆን አድርጎታል።

በመሆኑም ምንም እንኳን የሳይበር ወንጀል ድንበር የማይገድበው ዓለም አቀፍ ወንጀል ስለመሆኑ ዓለም አቀፍ ስምምነት ቢኖርም ወንጀሉን ለመዳኘት የሚያስችል ዓለም አቀፍ ሕግ ግን እስካሁን ድረስ ባለመኖሩ አገራት የራሳቸውን ህግ እያወጡ በነባራዊው የግዛት ክልላቸው በመፈጸምና በማስፈጸም ላይ ይገኛሉ። በዚህ ረገድ ከዓለማችን አገራት 154ቱ ወይንም ሰማንያ በመቶ የሚሆኑት የሳይበር ወንጀልን ለመከላከል የሚያስችል ህግ አውጥተው በመተግበር ላይ ይገኛሉ። የምህዳሩ ከፍተኛ ተጠቃሚ ከሆነው የአውሮፓ ክፍለ ዓለም እንደዚሁ 93 በመቶ የሚሆኑት የራሳቸው የሆነ የሳይበር ህግ ያላቸው መሆናቸውን መረጃዎች ያመላክታሉ።

ኢትዮጵያም ዘግይታም ቢሆን የሳይበር ጥቃትን በወንጀል የሚደነግግ ህግ ካወጡ ሀገራት መካከል የገባች ሲሆን ይህም ህግ በኢትዮጵያ "የኮምፒውተር ወንጀል" በሚል የሚታወቅ ሲሆን ለመጀመሪያ ጊዜ የተደነገገው በ1996 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የወንጀል ህግ መሆኑን የፍትሕ ሚንስቴር መረጃ ያመላክታል። ህጉ ከአንቀጽ 706 እስከ 711 በዝርዝር ተደንግጎ ይገኛል። ይሁን እንጅ በ1996 ዓ.ም የወጣው ይህ ህግ ብቻውን በየዜው እተወሳሰበ የመጣውን የሳይበር ወንጀል ለመቆጣጠር የሚያስችል ባለመሆኑ በአዲስ መልክ ራሱን ችሎ በአዋጅ እንዲደራጅ ለማድረግ እንደገና በ2008 ዓ.ም በአዋጅ ቁጥር 958/2008 ተደንግጎ ወጥቷል።

ይህም ኮምፒውተርን ዒላማ ያደረጉ ወንጀሎችን ማለትም ህገወጥ ደራሽነት፣ ህገ ወጥ ጠለፋ፣ በኮምፒውተር ስርዓት ጣልቃ መግባት፣ በኮምፒውተር ዳታ ላይ ጉዳት ማድረስ እና ከኮምፒዩተር መሣሪያና ዳታ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን የሚመለከት ነው። ዓላማውም ከዚህ ጋር በተያያዘ ኮምፒዩተርና የኮምፒዩተር ሥርዓትን ኢላማ ያደረጉ ወንጀሎችን ከመቆጣጠርና ከመከላከል በዚህም የሳይበር ደህንነትን ማለትም የመረጃ ሚስጥራዊነትን፣ ምሉእነትንና ተደራሽነትን ማስጠበቅና ማረጋገጥ ላይ ያተኮረ ነው።

ከዚህ በተጨማሪም እንደአገር የሳይበር ደህንነት ፖሊሲ ማዘጋጀት የሳይበር ጥቃትንና ወንጀልን ለመከላከልና የአገርን ብሔራዊ ደህንነትና ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ሲሆን ኢትዮጵያም ለሳይበር ጥቃት ፈጣን ምላሽ መስጠት የሚያስችልና ዘመኑን የሚመጥን የተሻሻለ የሳይበር ደህንነት ረቂቅ ፖሊሲ ባለፈው ዓመት ማዘጋጀቷ ይታወቃል። በፖሊሲው ውስጥም ተቋማት ተቋማዊ የአሠራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት በራሳቸው መንገድ የሳይበር ጥቃትን እንዲከላከሉ የሚያስችል አሠራር መካተቱን ይታወሳል።

ህጎችን ማውጣት ብቻ ሳይሆን የሚወጡ ህጎችን በአግባቡ መተግበርም ግድ ይላል። "የተቀናጀ የሳይበር ደህንነት ለአገር ሉዓላዊነት" በሚል መሪ ሃሳብ ከጥቅምት 1 ቀን እስከ 30 ቀን 2015 ዓ.ም እየተከበረ በሚገኘውና የዘንድሮው ሦስተኛው የሳይበር ደህንነት አራተኛ ሳምንት መርሃ ግብር ላይ ተገኝተው መልዕክት ያስተላለፉት የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ አገኘሁ ተሻገር ያረጋገጡትም ይህንኑ ነው። አፈ ጉባኤው በመልክዕክታቸው የአገርን ብሔራዊ ደህንነትና ሉዓላዊነትን ለማስጠበቅ የሚወጡ ህጎች ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኙ የህግ አውጭ አካላት፤ የሕዝብ ተወካዮችና ፌደሬሽን ምክር ቤቶች በትኩረት ሊሠሩ እንደሚገባ ተናግረዋል። ለዚህም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከታተሉዋቸውና የሚቆጣጠሩዋቸው ተቋማት የሳይበር ደህንነት ጉዳይን ዋነኛ የትኩረት መስካቸውና ስትራቴጂክ ተቋማዊ ጉዳያቸው አድርገው መምራት የሚገባቸው መሆኑንም አመላክተዋል። ለተፈጻሚነቱም የህግ አስፈጻሚና ህግ ተርጓሚ አካላት ከህግ አውጭው ጋር በጋራ ተቀናጅተው መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

ከዚህ በተጨማሪም የሳይበር ደህንነትን ለማስጠበቅ የሚወጡ ሕጎች ዘርፉ የሁሉንም የባለድርሻ አካላት ትብብር የሚጠይቅ በመሆኑ ይህንኑ ግምት ውስጥ በማስገባት በአገር ውስጥ ከሚገኙ ልዩ ልዩ የመንግስትና የግሉ ዘርፍ ተቋማት በአሻገር ከሌሎች አገራት፣ አኅጉራትና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር በትብብር ለመሥራት በሚያስችል መልኩ መዘጋጀትና መተግበር የሚገባ መሆኑን በዘርፉ ጥናት ያደረጉ የህግ ባለሙያዎች ይመክራሉ።